## ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

# ሁለት መንገዶች

# ሸሪአ—መንፈስ ቅዱስ

ሙስሊም ባልንጀሮቼ ወደ እንግሊዟ በርሚንግሃም መካከለኛ ስፍራ በመኪና እየወሰዱኝ፣ "ይህ የከተማው አካባቢ የሚተዳደረው በሸሪአ ሕግ ነው፤ ይህ እውን ለመሆኑ ማስረጃዎቹን እያስተዋልህ ነው?" አሉኝ። ብዙ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ጥቁር ተቀብተዋል። ቀድሞ ጥቁር ከተቀባው ሥዕል ኋላ አጭር የለበሰች ሴት አልያም የቢራ ማስታወቂያ እንደ ነበረበት ነገሩኝ። እርግጥ ነው ማስረጃዎቹን ተመልክቻለሁ።

ይህ የሆነው የእንግሊዝ ሙስሊም ተማሪዎች ማኅበር ለስድስት ቀን ባዘጋጀው የውይይት ወቅት ነበር። ለአንድ ሳምንት ከተካሄዱ ሞቅ ደመቅ ካሉ የአደባባይ ክርክሮች ማጠናቀቂያ ላይ፣ በፕሮግራሙ ላይ እንድገኝ የጋበዙኝ እንዲሁም በፕሮግራሙ ላይ አብረውኝ ሲሟገቱ የነበሩ ወዳጆቼ፣ ወደ ሒትሮው አየር ማረፊያ እየወሰዱኝ በነበረበት ወቅት ነው። በጉዞው ላይ ስንሟገት ከነበሩት ሰዎች መኻል አንዱ፣ "ምዕራባውን ሸሪአ ያስፈልጋቸዋል። ምዕራባውያን ከመበስበስ የሚድኑት ይህ ቀን ሲመጣ ብቻ ነው" አለ። "እኔ ከዚህ ሐሳብ ጋር አልስማማም፤ በእኔ እምነት ሸሪአ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጣቸውን ኀላፊነቶችና ነጻነቶች ገፎአል። ለምሳሌ በሱዳንና በናይጂሪያ እየሆነ ያለውን ነገር በውል እንደምትረዱት፣ የቤተ ክርስቲያን ነጻነት እስኪ በሆነ ሁኔታ ተገድቧል" አልሁ። አንደኛው ወገን ሙኽ ብሎ፣ "አንተ እንደምትለው በጭራሽ አይደለም። ሸሪአ የግብረገብ ድቀትን ስለሚከላከል እንዲሁም የክርስቲያኖችን ነጻነት ስለሚያስከብር ክርስቲያኖች ራሳቸው የሚደግፉት ጉዳይ ነው" አለ። "እኛ ክርስቲያኖች ሸሪአን የምናውቀው አንተ እየገለጽከው ባለበት መንገድ አይደለም፤ ይልቁንም እኛ ስለ ሸሪአ ያለን ግንዛቤ፣ ሸሪአ ሁል ጊዜ ክርስቲያኖችንና በቁጥር አናሳ የሆኑ ሃይማኖቶችን እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንደሚመለከታቸው ነው" ስል በሐሳቤ ጸናሁ።

በማንሰላሰልና በማስተዋል የተሞላ ዝምታ ነገሠ። ከቡድኑ አባላት መካከል አንዱ፣ "እኔ አሁን ወደ ካናዳ ልሄድ ነው። ወደ ትውልድ አገሬ ወደ ፓኪስታን ለመመለስ በጭራሽ አልፈልግም። ዕድሜ ልኬን በካናዳ ለመኖር ወስኛለሁ። ለዚህ ደግሞ ዋነኛ ምክንያቱ በዚህ መኪና ውስጥ ያለነው ሰዎች

ሁሉ በምንም መልኩ ዳግም በሸሪአ ሕግ ሥር መኖር ስለማንፈልግ ነው" ሲል ተናገረ::

በመካከላችን ይደረግ የነበረው ውይይት በየዓለማቱ በሚገኙት ሙስሊሞችና በሙስሊሙ ማኅበረሰብ መካከል የሚደረገውን ትግል አመልካች ነው:: የሙስሊሙ ማኅበረሰብ፣ የግለሰቦችን ነጻነት የሚገፍና የሰዎችን ሰብእና ክፉኛ የሚያጐድፈውን ሕግ፣ የማይለወጥ የእግዚአብሔር ሕግ ነው ብሉ ሊያጸናው እንዴት ይችላል?[1] ሸሪአ የሚለው ቃል ጥሬ/ቀጥተኛ ትርጕሙ፣ "ወደ ውሃ ጕድጓድ የሚያመራ መንገድ" ማለት ሲሆን፣ የሸሪአ ቀዳማይ ዐላማም ደኅንነትና ሰላም ነው:: ይህ የሰዎችን ደኅንነት አስተማማኝ በሆነ መንገድ የሚያረጋግጠው አቅጣጫ የቱ ነው? ሙስሊማን የሆኑ ባለ ሥልጣናት ይህን አቅጣጫ የሚያብራሩበትና ከጥቃት የሚከላከሉበት መንገድስ ምንድን ነው?

ይህ በወርኀ ጥቅምት 2002 ዓ.ም በኢራናውያን ሙስሊሞችና በሜኖናይት ክርስቲያን የነገረ መለኮት ምሁራን መካከል በቶሮንቶ ካናዳ የተካሄደው ውይይት በዚህ ርእሰ ጕዳይ ላይ ያተኰረ ነበር:: ይህ የሙስሊም ነገረ መለኮት ሊቃውንት ከቆም ኢራን ወደ ቶሮንቶ ካናዳ በመጓዝ፣ ከሜኖናይት የነገረ መለኮት ምሁራን ጋር ለአራት ቀናት ያካሄዱት ውይይት ጭብጥ ነው:: በሙስሊማኑ ጥያቄ መሠረት እምነትና ዘመናዊነት የሚለው ርእሰ ጕዳይ በውይይቱ ተካቶ ነበር:: እነዚህ ሙስሊሞች በሠለጠነው ዓለም ውስጥ እምነታቸውን እንዴት ጠብቀው መኖር እንደሚችሉ ከሜኖናይት የነገረ መለኮት ምሁራን ትምህርት መቅሰም ፈልገው ነበር:: የኢራን ሙስሊሞች አብዮት ውስጥ ውስጡን የሚብላላና እርስ በርሱ የሚታመስ ትግል ነው:: ይኸውም የዲሞክራሲ ግንባታ ኀይሎች ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር ሳይጣረሱ ተስማምተው መኖር እንዴት ይችላሉ የሚለው የትርምሱ ማዕከል ነው:: በአጠቃላይ ይህ ማንኛችንንም ቢሆን በእጅጉ የሚያሳስበን ርእሰ ጕዳይ ነው::

"ኢየሱስና የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ያመኑበትና ይኖሩበት የነበረው የአኗኗር ዘይቤ በየትኛውም ማኅበረሰብ በዝቅተኛ ደረጃ ለሚታዩት መነኰሳት እጅግ ተስማሚ ጕዳይ ነው:: የፖለቲካ ሥልጣንና ኀይል ባለቤት ለሆኑት የሃይማኖት መሪዎች ግን እንደዚያ አይደለም" ይህ ለፈርጀ ብዙ ባህልና እውነት አናባፕቲስቶች ለሰጡት ትንተና አንድ ኢራናዊ የስብሰባው ታዳሚ የሰጠው አስተያየት ነው::

---

[1] Andrew Rippin, *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices* (New York: Routledge, 2002), 8-9.



ሸሪአ እንዴት ሊጐለብት እንደቻለና ዘመናዊው ዓለም ለሸሪአ ያለውን አተያይ ለመዳሰስ እንሞክራለን:: በመቀጠልም በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያለውን የሥራ ድርሻ እንቃኛለን:: በእነዚህ ርእሰ ጕዳዮች ላይ የምናጠናው ጥናት በዋነኝነት የሚያጠነጥነው ሸሪአና መንፈስ ቅዱስ ሙስሊሙ ማኅበረሰብና ቤተ ክርስቲያን ፈርጀ ብዙ በሆነው ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉባቸውን ተግዳሮቶች እንዴት ማሸነፍ እንደሚችሉ እንደሚረዷቸው ነው::

## የሸሪአ ዕድገት

ሙስሊሞች እስልምና ለእምነትና ለምግባር ፍጹም የሆነ መመሪያ እንደ ሆነ ያምናሉ:: ከላይ በተመለከትናቸው ተከታታይ ምዕራፎች ደጋግመን እንደ ተመለከትነው፣ ሙስሊሞች እስልምና እግዚአብሔር በመላእክቶች አማካይነት ለሰው ልጆች ሁሉ ይሆን ዘንድ የላከው እምነት እንደ ሆነ ያስባሉ:: እስልምና በፍጹም ሊቀየር የሚችል ሃይማኖት አይደለም የሚል አቋም አላቸው:: በቀዳሚነት ለነቢዩ አደም (አዳም) የተላከው እስልምና በመካከለኛው ዘመን ነቢይ ለነበረው ለአብርሃም እንዲሁም የመጨረሻው ዘመን ነቢይ ለሆነው ለመሐመድ ከተላከው እስልምና ጋር አንድ ዐይነት ነው:: እስልምና በቁርአን ውስጥ የተገለጠና የተብራራ የመጨረሻውና ፍጹምነትን የተላበሰ መመሪያ እንደ ሆነ ይታሰባል::

ይህ ሙስሊሞች ስለ መመሪያው ያላቸው መረዳት፣ እስራኤላውያን ስለ ሙሴ ሕግ ካላቸው ነገረ መለኮታዊ መረዳት ጋር በተወሰነ መልኩ ይመሳሰላል:: የሙሴ የሕግ መጻሕፍት የአይሁዳውያን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ማዕከልና የብሉያት የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት ናቸው:: የአይሁድ ሕዝብ የቶራን ሕግ ሙሉ በሙሉ በታማኝነት ለመታዘዝ እጅግ በጣም ይጨነቅ ነበር:: የአይሁድ ቤተ መቅደስ በሰባ ዓ.ም ከተደመሰሰ በኋላ፣ የአይሁድ የሕግ ምሁራን ለ350 ዓመት አይሁድ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚገልጽ ታልሙድ የሚባል መጽሐፍ አዘጋጁ:: ስድሳ ሦስት ተከታታይ ቅጽ ያላቸው የታልሙድ መጻሕፍት፣ "በሕገ ኦሪት ዙሪያ የታነጹ ዐጥሮች" ተደርገው ይታያሉ:: እነዚህ መጻሕፍት ለቶራ እንዴት ታማኝ ሆኖ መኖር ይቻላል የሚለውን ጕዳይ የሚተነትኑና ቶራን ከጥቃት የሚከላከሉ ሰነዶች ናቸው::

በተመሳሳይ መንገድ ሙስሊሞች ቁርአንን ከጥቃት ለመጠበቅ ይቻል ዘንድ ሸሪአን አዘጋጅተዋል:: በአይሁዶች ልምምድ ታልሙድ እንዴት ለሕገ ኦሪት መታዘዝ እንዳለባቸው የሚያብራራ ሲሆን፣ ለሙስሊሞች ደግሞ ሸሪአ እንዴት

ለቁርአን መታዘዝ እንዳለባቸው ያስተምራል:: የአይሁዶችም ሆነ የሙስሊሞች ቀዳማይ ዐላማ፣ ለእግዚአብሔር ሕግ ሙሉ በሙሉ መገዛት (መታዘዝ) ነው:: ነገር ግን ለእግዚአብሔር ሕግ ሙሉ ለሙሉ መገዛት ማለት ምን ማለት ነው? ይህን በተመለከተ ቁርአን እንዲህ ይላል:—

> "መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፤ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን በመላእክትም በመጻሕፍትም በነቢያትም ያመነ ሰው ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች፣ ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ ሰውና ሶላትንም ደንብን ጠብቆ የሰገደ፣ ዘካንም የሰጠ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው፤ በችግር በበሽታና በጦር ጊዜም ተጋሾችን (እናወድሳለን)፤ እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ ናቸው:: እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው" (ሱራ 2+177)::

ሙስሊሞች ይህን ክፍል የእስልምና ሰባቱ ትእዛዛት ሲሉ ይጠሩታል:: ሙስሊሞች ሊያምኗቸው የሚገቡ የእስልምና አምስት መሠረተ እምነቶች በዚህ ክፍል ውስጥ ተካተዋል፤ እነርሱም:— (1) እግዚአብሔር፣ (2) የመጨረሻው ፍርድ፣ (3) መላእክት፣ (4) ቅዱሳት መጻሕፍትና (5) ነቢያት ናቸው:: ክፍሉ ፍትሕ፣ ጽድቅ፣ ለድኻ መመጽወት መደበኛ የሆነን ጸሎት ያዛል:: ልክ እንደዚህ ክፍል ሁሉ መላውም ቁርአን የእምነትና የተግባር መመሪያ መጽሐፍ ነው:: ሆኖም አንድ ሙስሊም እነዚህን ትእዛዛት መጠበቁን እንዴት ያውቃል? ለምሳሌ የዘወትር ጸሎትና መደበኛ ልገሳ ምንድን ነው?

## ሱና

ሱና መሐመድ ምድራዊ ኑሮአቸውን የኖሩበት የሕይወት ዘይቤ ነው:: እርሳቸው የነቢያት መጨረሻ እስከ ሆኑ ድረስ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ ሁሉ ትክክለኛ በሆነ መንገድ የታዘዙ ነቢይ ናቸው:: መሐመድ የእግዚአብሔርን መገለጥ በሙላት የሚረዱበት፣ የሚተረጉሙበትና የሚተገብሩበት ጥበብ (ሒክማ) አላህ ሰጥቶአቸው ነበር:: ስለዚህ አማንያን ሁሉ የነቢያቱ መንገድ የሆነውን ሱናን በሙላት ሊከተሉ ይገባቸዋል:: ነገር ግን ይህ የመሐመድ መንገድ (ሱና) ምንድን ነው?



## ሐዲስ

በሙስሊሞች የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕት ዓመታት፣ ይህ ጥያቄ ሐዲስ እንዲዋቀር ምክንያት ሆኖአል:: እጅግ ትልቅና ዋነኛ የሚባለው 9,082 ሐዲሶችን ያካተተው የቡካሪ ስብስብ ነው (ድግግሞሹ ሲወገድ የቡካሪ ስብስብ 2,602 ሐዲሶችን የያዘ ነው)[2]:: እያንዳንዱ ሐዲስ ስለነቢዩ አኗኗር ዘዬ የሚያስተምረው ትምህርት አለው:: ለምሳሌ:—

ዮቅባ ኢብን አሚር እንዲህ ይላል፣ "አንድ ሰው ለነቢዩ የሐር ካባ ላከላቸውና በጸሎት ጊዜ ለበሱት:: ከጸሎት በኋላ ልብሱን በቁጣ አወለቁት:: እጅግም በመጸየፍ፣ 'ይህ እግዚአብሔርን ለሚፈራ ሰው ተስማሚ (የሚመች) ልብስ አይደለም' አሉ"[3]::

ሌሎች ትውፊቶች ደግሞ የተለየ ፖለቲካዊና ሥነ መለኮታዊ ዐላማ ነበረቻው:: ለዚህ ሁነኛ ምሳሌ የሚሆነው:— ሐዲስ፣ የነቢዩን ዐማች እንደ አራተኛ ከሊፋ ንግሥናው በግጭት የተናወጠውን የዓሊን ሥልጣን ተገቢነት ያጸናል:: የዚህ ሐዲስ ዐላማ የፈጠራ ሱናን ማቋቋም ነበር:: የሥልጣን ሰንሰለቱ የሐዲስን ትክክለኘነት ለማረጋገጥ ይጠቅማል::

> አቡ በክር ኢብን አቢ ሻአይባ እንደ ነገረን ጉህንዳር በሸባ ሥልጣን እንደ ነበረውና መሐመድ ኢብን አል-ሙታአንና ኢብን ባሻር ሁለቱ እንደ ነገሩት መሐመድ ኢብን ጀአፈር እንደ ነገረው ሹባም ደግሞ እንደ ነገረው በማደንሱር ሥልጣን በራአቢ ኢብን ሂራሽ ሥልጣን የሚከተለውን በሰማው፣ "እግዚአብሔር በእርሱ ይከብር ዘንድ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ብሉ መልእክት ሰጠው ጸሎትና የእግዚአብሔር ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን" አለ:: "ስለእኔ ውሸትን አትናገር ስለእኔ ውሸትን የሚያሠራጭ በገሐነም እሳት ይገባል"[4]

ከመሐመድ ዘመን በኋላ ብዙ መቶ ሺህ ሐዲሶች ተሠራጭተዋል:: የቡካሪ ሥራ የትኞቹ እውነተኞች እንደ ሆኑ መወሰን ነው:: ይህም ውሳኔ በምስክሮች

---

[2] Frederick Mathewson Denny, *An Introduction to Islam* (New York: Macmillian, 1994), 161.

[3] H. A. R. Gibb, *Mohammedanism* (New York: Oxford University Press, 1969), 74.

[4] Rippin, *Muslims*, 47.

በንሰለት (ኢስናድ) ታማኝነት ላይ የተመረኮዘ ነው። ሻአፊ ሙስሊም የተባለው ሌላው ምሁር እንደ ቡካሪዎች ያለ ጥረት አድርጓል። ትውፊት እንደሚያረጋግጠው ቡካሪ ከመረመራቸው ስድስት መቶ ሺህ ሐዲሶች መካከል 9,082ን መርጧል[5]፤ ሌሎች በመቶ ሺህ ለሚቆጠሩት ምንም ግምት አልሰጣቸውም። የእርሱ ቅጽ 3,450 ምዕራፎች የተከፋፈሉ ሰባት መጻሕፍትን የያዘ ነው[6]።

## የሸሪአ አሠራር

ከነቢዩ ሱና የታማኝነት ጉዳይ ባሻገር ሌሎች የነገረ መለኮት ሰዎች ደግሞ የሕግ ሥርዐቶችን (ሸሪአን) ሲያጐለብቱ ነበር። ሐዲስ በዚህ ረገድ ታላቅ ድርሻ ነበረው። ሸሪአን ያጐለበቱት ከአራት ሥልጣናዊ ምንጮች በመነሣት ነው፤ ይኸውም:—

የመጀመሪያው ቁርአን ሲሆን
ሁለተኛው ሐዲስ
ሦስተኛው ቂያስ የምስስሉሽ ጥበብ
አራተኛ ኢጅማ ስምምነት/ሥልጣን ነው

ከቁርአንና ከሐዲስ ወጥ የሆነ የሕይወት መመሪያ ለማዘጋጀት ትልቅ የሆነ ጥበብና ማስተዋል ይፈልጋል። ከዚህ የተነሣ የነገረ መለኮት ምሁራን ለሙስሊሞች ደንብን ሲጽፉ የምስስሉሽን ጥበብ በማጐልበትና የማኀበረሰቡን ስምምነት መሠረት በማድረግ ነው። በሱኒ እስልምና የነገረ መለኮት ሰዎች እርስ በርስ የሚደርሱበት ስምምነት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። የትኛው ጽሑፍ በቁርአን ውስጥ ይካተት የሚለው ውሳኔ እንኳ የሚወሰነው፣ በነገረ መለኮት ምሁራን ስምምነት ነው። የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ምሪት መተርጐምና ይህንኑ ምሪት ኅብረተሰቡ በሕይወቱ እንዲተገብረው የማድረግ ኀላፊነት አለባቸው። ይህ ዐይነቱ የአተረጓጐም ሥርዐት ኢጂታሃድ ይባላል። የመተርጐም ኀላፊነቱ የተመሠረተው በእስልምና ሕግ ሳይንስ ላይ ባለ ጥልቅ ዕውቀትና መረዳት ላይ ነው።

በዚህ ስምምነትን መልክ ማስያዝ ሂደት ውስጥ የነገረ መለኮት ምሁራኑ የሕግ ትምህርት ቤቶችን መሥርተዋል። በስምንተኛውና በዘጠነኛው ምዕተ ዓመት

[5] Denny, *An Introduction to Islam*, 161.
[6] Gibb, *Mohammedanism*, 78-79.



የሱኒ ሙስሊሞች አራት የሸሪዓ ትምህርት ቤቶችን መሥርተዋል። እነርሱም *ሃናፊ* (Hanafi)፣ *ማሊኪ* (Maliki)፣ *ሻፊኢ* (Shafi'i)፣ እና *ሃንባሊ* (Hanbali) ይባላሉ። አተረጓጐማቸው የተለያየ ቢሆንም፣ ዋናው ሐሳብ ግን አንድ ነው። ይህም ዋና ሐሳብ ቁርአንና የመሐመድ የአኗኗር ሥርዐት የሆነው ሱና ለሕይወት ትክክለኛ መንገድ ነው የሚለውን አቋም ይፋ የሚያደርግ ነው። እነዚህ መንገዶች አራቱን የሱኒ ሙስሊም ቤተሰቦችን የሚገልጹ ናቸው። የሺአይት ሙስሊሞችም ደግሞ ሌሎች የሕግ ሥርዐቶችን አቋቁመዋል።

ምንም እንኳ እነዚህ የተለያዩ የአተረጓጐም ትምህርት ቤቶች የተለያየ አካሄድ ቢከተሉም፣ ሁሉም የነቢዩ አኗኗር የሆነውን ሱናን መከተል ይፈልጋሉ። ከዚህም የተነሣ በመሐመድ ላይ የሚሰነዘር ማንኛውም ዐይነት ትችት በሙስሊሞች ሁሉ ላይ እንደ ተቃጣ የማጥቃት ወይም የማግደል ሙከራ ይቈጠራል።

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ከለውጥ ፈተና ጋር እየታገለ ነው ያለው። አዲስ ለውጥ/ፈጠራ (ቢዳአህ) ፈጽሞ የተከለከለ ተግባር ነው። ከዐሥረኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ የሱኒ ሙስሊሞች መጽሐፍን የመተርጐም በር ፈጽሞ ስለተዘጋ ሸሪአን የማሻሻል አንዳችም ዕድል የለም የሚል አቋም አላቸው። በአንጻሩ የሺአይት ሙስሊሞች ደግሞ ሸሪአን ለመተንተንና ለማሻሻል በሩ በጭራሽ አልተዘጋም የሚል አቋም አላቸው። ለሺአይት ሙስሊሞች ሸሪአን የመተርጐምና ከእስልምና ሃይማኖት ልምምድ ጋር የማጣጣሙ ሂደት በየትውልዱ ሁሉ የሚቀጥል ተግባር ነው ባዮች ናቸው።

ሸሪአ በሁሉም ሙስሊሞች ተቀባይነት ያላቸውን ምግባራት (ሐላል) እንዲሁም የተከተለከሉት (ሐራም) ሥራዎች ምን እንደ ሆኑ ያብራራል። ለምሳሌ በተገለጸው መልኩ ያልታረደን የእንስሳ ሥጋ መብላት ሐራም ነው። በተገቢው መንገድ የታረደን ሥጋ መብላት ደግሞ ሐላል ነው። ሸሪአ አብዛኛውን የሕይወት አካሄድ ተቀባይነት ያለው ተግባር (ሐላል) ወይም ተቀባይነት የሌለው ተግባር (ሐራም) በማለት በሁለት ዐቢይ ወገን ይከፍለዋል። ሐራም ነገሮችን ማድረግ ቅጣት (ሃድ)ያስከትላል።

## ሸሪአና ጾርሰሳይ

ለሸሪአ ሕይወትን ማስገዛት ማለት ወደ እስልምና የተለወጠን ሕዝብ ከራሳቸው ባህል ወደ እስልምና ባህል የመለወጥ ግዴታ ማለት ነው፤ ይህም "ጾርሰሳይ"

(proselyte) ይባላል:: የዚህም ምክንያቱ ሸሪአ ብርቱ የሆነ የእስልምናን ባህል ሊወክል ስለሚችል ነው:: ይህ እንግዲህ የሁሉም እስልምና ትምህርት ቤቶች ቀደምት ሚና ነው:: በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ያሉ ሁሉም የትምህርት ተቋማት ዐላማ የመተርጉምና የሙስሊም ባህልን በሸሪአ እንደ ተገለጸው ማስፋፋት እንዲችሉ ማስታጠቅ (ብቁ ማድረግ) ነው:: ይህ ማለት በማናቸውም ጊዜ አንድ ሰው ሙስሊም ሲሆን፣ እምነቱን የመለወጡ ሂደት ጀምሯል ማለት ነው:: እምነት መለወጥ ማለት ከአንድ ባህል ወደ ሌላ ባህል መሄድን የሚያመለክት ነው:: ይህ ለውጥ የሚጀምረው እምነትን ይፋ በማድረግ ሲሆን፣ ይኸውም፣ "ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ መሐመድም የአላህ መልእክተኛ ነው" የሚለው ነው:: ይህ ቀላል የእምነት መግለጫ አንድን ሰው ከሙስሊሙ ባህልና ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጋር ይቀላቅለዋል:: መሐመድ የእግዚአብሔር ነቢይ ስለሆነ፣ በቁርአን እንደ ተገለጠው ማንኛውም አማኝ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት እንዲሁም የመሐመድን መንገድ መከተል አለበት፤ ይኖርበታልም:: ይህም ማለት ደግሞ ለሸሪአ መገዛት ማለት ነው:: ይህ የዐረብኛ ቋንቋ መማርን የሚጨምር ጉዳይ ነው:: በሸሪአ ውስጥ በግልጥ እንደ ተገለጸው እስልምናን መቀበል ከሙስሊማዊው ባህል ጋር መዋሐድ ማለት ነው::

## ሸሪአና የፖለቲካ ሥርዐት

የሙስሊሞች እደርስበት (ideal) የወልም ሆነ የተናጠል ሕይወት በሸሪአ እንደ ተገለጠው በሕጉ ሥልጣን ሥር መኖር ነው:: ሆኖም ብዙውን ጊዜ የሙስሊሙ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ሕይወት በጥቂቱ ሁለት የተለያዩ አተረጓጐም እውነታዎችን የያዘ ነው:: የዓለማዊው ሙስሊሞች የፖለቲካ ባለ ሥልጣናት የመንግሥትን አስተዳደር ጉዳይ የፖለቲካን እውነታ በሚጠይቀው መንገድ ተግባራዊ ከማድረግ ባሻገር ሸሪአንና የኡለማን (የሙስሊም ሕግ ምሁራንን) ድርሻ ያከብራሉ:: ምንም እንኳ መሐመድ ነቢይ እንዲሁም የአስተዳደር ሰው ቢሆኑም፣ ብዙ ጊዜ ከሙስሊሞች ታሪክ እንደምንረዳው፣ ኡለማና የአስተዳደር ሰው የተለያየ ተግባራትን የሚያከናውኑና የተለያዩ ሙያዎች መሆናቸውን ነው:: በዘመናችን የእነዚህ ሁለቱ ጉዳዮች እርስ በርስ መቀላቀላቸው፣ በአንዳንድ ሙስሊሞች መካከል የሙስሊሞች ተሐድሶ እንቅስቃሴዎች የማኅበራዊውንና የፖለቲካውን ሥርዐት በኡለማ ሥልጣንና ቁጥጥር ሥር ለማድረግ መፈለጋቸው ታላቅ ውጥረትን ፈጥሮአል::

ዘመናዊቷ ኢራን ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነች:: ሸንጐው የእስልምናው አብዮት ደጋፊ ነው:: ሁሉም ሕዝባዊም ሆነ ግላዊ ሕይወት በሼካዎች (የሙስሊም ነገረ



መለኮት ዐዋቂዎች) እንደሚተረጉመው በአንድ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥር ማዋል ነው:: በሌላ በኩል በሕዝብ የተመረጠው መንግሥት፣ ዐምባ ገነናዊ የነገረ መለኮት ሥልጣን መመሥረትንና በግለሰቦች ነጻነት ላይ የሚጥለውን ገደብ ይቃወማሉ::

በኅዳር 2002 ኢራን ታላቅ ነውጥ ገጥሟት ነበር:: በወሩ አጋማሽ ላይ የኮሌጅ መምህር በሆኑት በፕሮፌሰር ሃሺም አጋሃጃሪ ላይ በእስልምናው ፍርድ ቤት የተወሰነውን የሞት ፍርድ በሺዎች የሚቈጠሩ ተማሪዎች በጐዳና ላይ በመውጣት ተቃውሞአቸውን ገልጠው ነበር:: እንደ የአሶሼትድ ፕሬስ ጋዜጠኛ ዓሊ አክባር ዳሪኒ የፕሮፌሰሩ ከሳሾች የመከራከሪያ ነጥብ እንዲህ ብኋል በማለት ነው፤ "እያንዳንዱ አዲስ ትውልድ እስልምናን በራሱ መንገድ መተርጐም አለበት":: የቀደሙት ሼኮች የተረጐሙትን እንደማይነካና እንደማይለወጥ መታየቱን ተችቶአል[7]::

ፕሬዚዳንት መሐመድ ሐታሚ የሞቱን ቅጣት እንዲህ በማለት ተችተውታል፣ "ክሱ በፍጹም መመሥረት አልነበረበትም" የመንግሥት ቃል አቀባዩም እንዲህ ነበር ያለው፣ "ከብሔራዊ ጥቅማችን ጋር በሚጋጭ አቅጣጫ የሚጓዝና እንደዚህ ዐይነት ፍርድ በማንም ያልተደገፈ ነው"[8] ይህ በኀይል የተሠነዘረ ተቃውሞ ፍርዱን በእስላም ባለሥልጣናት ደግሞ ለመመልከት ለተወሰነው ውሳኔ አስተዋጽኦ አድርጓል:: በሚቀጥሉት ወራት እነዚህ በኢራን ያሉ ባለሥልጣናት ልዩነቶቻቸውን ማስወገድ ስላልቻሉ የፕሮፌሰር አጋሃዳሪም ጉዳይ መፍትሔ ሊያገኝ አልቻለም::

ኢራን በዚህ ዐይነቱ ውዝግብ ውስጥ እያለች አራት ሺህ ማይል ርቀት ላይ የምትገኘው ናይጄሪያ ከዓለም ዐቀፍ ኅብረተሰብ የመገለል አደጋ ውስጥ ገባች:: አሚና ላዋል የተባለች ሴት ከጋብቻ ውጪ ፀንሳ የሞት ፍርድ ተፈረደባት:: ከዓመት በፊት ሱፊያ ሑሴን በተመሳሳይ ጥፋት የሞት ፍርድ ተፈርዶባት ነበር:: የልጇ አባት የቀድሞ ባለቤቷ እንደ ሆነ በመናገሯ ፍርዱ ተሻሽሏል፤ የተሻሻለበት ዋና ምክንያትም የፀነሰችው፣ ሸሪአ በሰሜን ናይጄሪያ ውስጥ ከመተግበሩ በፊት ስለነበረ ነው:: ነገር ግን የአሚና ፍርድ ውሳኔ እስካሁን እንደጸና ነው:: ፍርዱ ባይቀለበስ (ባይሻር) ኖሮ ሱፊያ ልጇ ጡት መጥባት እንዳቆመ በድንጋይ ተወግራ ልትሞት ነበር:: ምንም እንኳ ትላልቅ ወይም

[7] Ali Akbar Dareini, *"Iran President Chides Death Sentence,"* from the Associated Press (13 November 2002), 191-95.

[8] ዝኒ ከማሁ::

በሰውነት ላይ በግርፋት የሚፈጸሙ ቅጣቶች ሃድ ተብለው ለሚታወቁት ታላላቅ ጥፋቶች የሸሪአን ፍርድ የሚጠይቁ ቢሆኑም በአጠቃላይ የዚህ ዐይነት ፍርዶች በእስላማዊ መንግሥታት አይበረታቱም ወይም ችላ ተብለዋል::

በሰሜን ናይጀሪያ በዐሥራ ሁለቱ ግዛቶች የሸሪአ በተግባር ላይ መዋል (መተግበር) በዘመናዊ እስልምና ማኅበረሰቦች ተቃውሞ እንዲገጥመው አድርጓል:: ይህ እንቅስቃሴ በግንቦት 1999 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ ክርስቲያን ፕሬዚዳንት ኦሊሴጎን ኦባሳንጆ እንዲመረጡ አስተዋጽኦ አድርጓል:: የሰሜናኞቹ ሙስሊሞች በሙስሊሞች አመራር ሥር መሆንን አጥብቀው ይመርጡ ነበር:: የሰሜናኞቹ ሙስሊሞች በሸሪአ ሥልጣን ሥር ለመተዳደር የወሰኑት ከክርስቲያን ሥልጣን አካባቢውን ለመጠበቅ ነበር[9]::

በሰሜኑ ግዛት የሚኖሩ በዛ ያለ ቁጥር ያላቸው አናሳ ክርስቲያኖች በግዛቱ የሸሪአ መደንገግ ነጻነታቸው ይገደባል:: በእርግጥ ሁሉን ዐቀፍ በሆነው በፌደራል መንግሥትና በክልል መንግሥት መካከል ውጥረት ነበር:: የአሚና ላዋል የሞት ፍርድ ለዚህ የፍርድ መቀልበስ አንድ አስተዋፅኦ አድርጓል:: የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዚህ ዐይነቱን ፍርድ በፍጹም ሊያጸድቁ አይችሉም:: በሰሜን ናይጀሪያ የሸሪአ ፕሮግራም መተግበር በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ብዙ ሁከት የተሞላ ግጭት በዓለም ዐቀፍ የዜና ማሠራጫ ትኩረት ተሰጥቶበታል:: በአገሪቱ ውስጥ ላሉ የጸሎት ስብሰባዎችና ጾም ጸሎቶች በዓለም ዙሪያ ትልቅ ትኩረት ነው የተሰጠው:: የክርስቲያኑ ማኅበረሰብ በሙሉ፣ ከሙስሊም ጐረቤቶቻቸው ጋር በሰላም የመኖር ናፍቆታቸውንና ሸሪአ በግዴታ እንደ ተጫነባቸው በቀጥታ ገልጸዋል:: ብዙ በናይጀሪያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ለውይይትና ለጸሎት ዝግጁ ሆነዋል::

ለሺህ ዓመታት ሙስሊሞች "ወደ ውሃ ኩሬ የሚያመራው መንገድ" በሚገባ ተብራርቶአል ብለው ሲያምኑ ቆይተዋል:: የነገረ መለኮት ዐዋቂዎች እንደሚያምኑትም ሁሉም የተሐድሶ ሰዎች የመንገዱን ዐጥሮች አጠናክረውታል:: ዳሩ ግን ዘመናዊነት በተደጋጋሚ እና በአደገኛ ሁኔታ ዐጥሮቹን ክፉኛ እየተፈታተናቸው ነው::

ኢራናውያን ተማሪዎች ለጓደኛዬ እንዲህ ብለው ነገሩት፣ "የኢራናውያን አብዮት ለእስልምና ሃይማኖት አንዳችም ዝንባሌ እንዳይኖረን አድርጓል"::

9 John Alembillah Azumah, *The Legacy of Arab Islam in Africa* (Oxford: Oneworld Publications, 2001), 191-95.



ሌሎች ኢራናውያን ደግሞ ተገቢ ባልሆነ የምዕራብ ወዳጅነት ምክንያት ለዓመታት ከተደረገብን ተጽእኖ ተላቀው በመጨረሻ እውነተኛ በሆነው የእስልምና መንገድ መመሥረት በጣም ደስተኞች ናቸው:: ለእነዚህ ሙስሊሞች ሸሪአ፣ "ጥልቅ የሆነ የመረጋጋትና የደኅንነት ስሜት" ይሰጣቸዋል[10]:: በዘመናዊዎቹ እና በአጥባቂዎቹ ኀይላት መካከል ያለው ውጥረት ንድፈ ሐሳባዊ አይደለም:: በብዙ ሙስሊም ማኅበረሰብ መካከል ትልቅ ተግዳሮት ያመጣ ነው::

አሁን ከዚህ ፍጹም የተለየውን የመሲሑን መንፈስ እናጠናለን::

## መንፈስ ቅዱስ

አንድ ሙስሊም ምሁር በአንድ ምሽት በዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ በተደረገ ውይይት ላይ፣ "ስለ መንፈስ ቅዱስ የማውቀው አንዳች ነገር የለኝም" ሲል ተናገረ:: እኔም እንዲህ ብዬ መለስኩለት፣ "መንፈስ ቅዱስ እጅግ ክቡር ስጦታ ነው:: የመጨረሻውንና ፍጹማዊውን እውነት የሚገልጥ፣ ስለ ኀጢአት የሚወቅስና ሰው በወንጌል ማመን የሚችልበትን ዐቅም የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው"::

"ታዲያ አንተ፣ ለእኛ ለሙስሊሞች የወንጌልን እውነት ልታስረግጥልን አትችልም ማለት ነው? እስልምና ግን ፍጹም በማስተዋልና በአመክንዮ የተመሠረተ ስለሆነ በዚህ ምሽት የእስልምናን እውነተኛነት ላረጋግጥልህ እችላለሁ:: ታዲያ አንተስ የወንጌልን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ሙከራ አታደርግም?" በማለት ሙስሊሙ ወዳጄ ጐተጐተኝ:: እኔም እንዲህ አልሁት፣ "ወንጌል ከአመክንዮ ጋር የሚጣረስ/የሚጋጭ እውነት የለውም:: እንዲያውም አማኙ የሕይወት ትርጉሙንና የአመክንዮ ማዕከሉን የሚቀዳው ከወንጌል ነው:: ያለ መንፈስ ቅዱስ ዕገዛ እንዲያው በተፈጥሮ ክህሎታችን፣ የተሰቀለው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይል ነው ወደሚለው ድምዳሜ በፍጹም ልንደርስ አንችልም"::

ባልንጀራዬም በመደነቅ፣ "በአመክንዮና በተፈጥሮ ክህሎታችን እውነትን ማግኘት አንችልም ማለትህ ነው?" ሲል ጠየቀኝ:: እኔም፣ "እውነት ነው!

10 Denny, *An Introduction to Islam*, 197.

መንፈስ ቅዱስ ለእውነት ልባችንን ካልከፈተው በስተቀር በፍጹም እውነትን ማመን አንችልም" አልሁት።

"እንግዲያው መንፈስ ቅዱስን እንዴት ማግኘት እንችላለን?"

"ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጣችሁ አብን ጠይቁ ብሏል። እኛ መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት እግዚአብሔርን ከጠየቅነው እግዚአብሔር አያሳፍረንም"።

ሙስሊሞች፣ እስልምና ተፈጥሮአዊ ስለሆነ ሰዎች በተፈጥሮአቸው እጅግ መልካሞች ናቸው የሚል አመለካከት አለው። ከዚህም የተነሣ ሰዎች በአላህ ለማመንም ሆነ መሐመድ የአላህ ነቢይ ነው ብሎ ለመቀበል የመንፈስ ቅዱስ ርዳታ አያስፈልጋቸውም የሚል እምነት አላቸው። ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስ ሥነ አመክንዮና ምክንያታዊ የሆነ አመለካከት በቂ ነው ባዮች ናቸው። የሰዎች ፈቃድ ትክክለኛውን ጉዳና አመራምር ለማግኘት በቂ ነው። ለዚህም ነው የሸሪአው የእስልምና አወቃቀር ፊጋ በሚባለው ማለትም በመረጃ ላይ በተመሠረተ ዕውቀት ላይ የሚደገፈው[11]።

## መንፈስ ቅዱስ በእስልምና

ምንም እንኳ በእስልምና ነገረ መለኮት መንፈስ ቅዱስ ብዙ ስፍራ ባይኖረውም ቁርአን ስለ መንፈስ ቅዱስ ይናገራል። በእርግጥ እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረበት ጊዜ መንፈሱን እፍ ብሎበታል (ሱራ 15፥29)። በተጨማሪም መሲሑ ከእግዚአብሔር የተላከ መንፈስ ነው (ሱራ 41፥75)። በሌላ ስፍራ

[11] ይህ ማለት ሙስሊሞች የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነትና የሰዎችን ነጻ ፈቃድ በማስታረቁ ዙሪያ ችግር የለባቸውም ማለት አይደለም። ይህ ጉዳይ የክርስትና ነገረ መለኮት ምሁራንንም በእያሌው የሚያወዛግብ ጉዳይ ነው። ነገር ግን በዚህ ርእስ ጉዳይ ላይ መተቸት ይህ መጽሐፍ ዐላማ ካደረገው እንዲሁም ይህ ምዕራፍ ሊዳስሰው ካሰበው ቀላም ነገር ወጣ ያለ ነው። በርእሰ ጉዳዩ ላይ ሰፊ ጥናት ማካሄድ የፈለጉ የሚከተለውን የዶክትሬት ድግሪ ማሟያ ጽሑፍ ይመለከቷል:— John Hoover, *An Islamic Theodicy: Ibn Taymiyya on the Wise Purpose of God, Human Agency, and Problems of Evil and Justice,* Centre for the Study of Islam and Christian-Muslim Relations, University of Birmingham, United Kingdom, 2002. እንዲሁም የሚከተለውን ያልታተመ ይመልከቱ John Hoover, *"A Typology of Responses to the Philosophical Problem of Evil in Islamic and Christian Traditions"* (Unpublished paper Presented at a Mennonite-Shi'I dialogue: Toronto, October 24-26, 2002).



ከእግዚአብሔር የሆነው መንፈስ አማኞችን እንደሚያነቃቃ እናነባለን (ሱራ 17፥85-86)።

ዳሩ ግን የሙስሊም ነገረ መለኮት ምሁራን፣ ቁርአን ስለ መንፈስ ቅዱስ የተናገራቸውን ምንባባት ከአዲስ ኪዳን ነገረ መለኮት ጋር በሚጻረር መልኩ ወደ መተርጐሙ ያዘነብላሉ። የእስልምና ነገረ መለኮት የሥላሴን አስተምህሮ ስለማይቀበል፣ ሙስሊሞች ስለ መንፈስ ቅዱስ ያላቸው አመለካከት ትልቅ ጥንቃቄ የሞላበት ነው። ሆኖም ግን በሙስሊም ነገረ መለኮት ምሁራን ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ ልማድ የለም። ዐልፎ ዐልፎ የማንበቡ ልማድ ያላቸውም ሙስሊሞች ቢኖሩ፣ ክርስቲያኖች ብሉይ ኪዳንን በክርስቶስ አንጻር እንደሚተረጒሙት ሁሉ እነርሱ መጽሐፍ ቅዱስን በቁርአን አንጻር ለመተርጐም ትልቅ ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላል። መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁራን የተለያየ ምልከታ አላቸው።

እንደ አንዳንድ የእስልምና የነገረ መለኮት ሰዎች ዕውቀትን የሚያካፍለውና የሚያነሣሣው መንፈስ ቅዱስ፣ ለመሐመድ መገለጥን ያመጣው መልአኩ ገብርኤል ነው ባዮች ናቸው። በእርግጥም አንዳንድ የነገረ መለኮት ሰዎች ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩ ምንባባት ሁሉ ስለ መልአኩ ገብርኤል ነው የሚል አቋም ይዘዋል።

አብደላ ዮሴፍ ዓሊ የተባለው የነገረ መለኮት ምሁር፣ እነዚህን ምንባባት በጥንቃቄ ከመረመርን ወደዚህ ድምዳሜ በፍጹም አንደርስም የሚል አቋም አለው። በርግጥ አንዳንድ ምንባባት ስለ መልአኩ ገብርኤል የሚናገሩ ቢሆንም ሁሉንም ክፍሎች እንደዚያ መተርጐሙ ግን ትክክል አይደለም ባይ ነው። አንዳንድ ጊዜ ቁርአን መንፈስ ቅዱስን ከመላእክትና ከራእይ መጻሕፍት በተለየ መንገድ እንደ እግዚአብሔር ምሕረት አድርጎ ያቀረበበት ሁኔታ እንዳለ ጽፎአል[12]።

ሌሎች ሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁራን ደግሞ፣ ኢየሱስ በዮሐንስ 14፣ 15 እና 16 ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሰጠውን ተስፋ ከቁርአን አንጻር ለመተርጐም ጥረት እንደሚያደርጉ ይታያል። እነዚህ ምሁራን እነዚህ የመጽሐፍ ክፍሎች ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንዳችም ግንኙነት እንደሌላቸው ነገር ግን ስለሚመጣው ስለ ነቢዩ መሐመድ የተሰጠ የተስፋ ቃል ነው የሚል አስተምህሮ አላቸው።

[12] Abdullah Yusuf Ali, *The Holy Qur'an: Text, Translation and Commentary* (Beirut: Dar Al Arabia, 198) 1605, footnote 5677.

ነገር ግን ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ፣ "እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል...የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ይመራችኋል" (ዮሐንስ 14፥26፤ 16፥12) የሚል ተስፋ ሰጥቶአል።

ሙስሊሞች እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሲያነቡ፣ ኢየሱስ ስለ ነቢዩ መሐመድ እንደ ተነበየ እንዲሁም መሐመድ ኢየሱስ የተናገረውን ነገርና ያስተማረውን ትምህርት እንደሚፈጽም የተሰጠ ተስፋ አድርገው ስለሚወስዱት በትልቅ ደስታ ይሞላሉ። አንዳንድ የእስልምና ሃይማኖት ዐቃብያን ከዚህም ርቀው በመሄድ፣ እናት ቋንቋው ስለ አሕመድ (መሐመድ) የሚናገር ነው የሚል ትምህርት እንዳላቸው ምዕራፍ 5 ላይ ለማየት ሞክረናል። ነገር ግን ለዚህ ዐይነቱ ትምህርት/ድምዳሜ አንዳችም ታሪካዊ የሆነ ምንባባዊ መሠረት እንደሌለ ልብ ይሏል።

ነገር ግን ለምንድን ነው ሙስሊሞች አዲስ ኪዳን ስለ መንፈስ ቅዱስ ከሚያስተምረው ትምህርት ራሳቸውን በማገለል አትጣጫን ለማስቀየር የሚፈልጉት? ለዚህ ሦስት ሁነኛ ምክንያቶች አሉ፤ እነርሱም:—

አንደኛ፤ ሙስሊሞች ማንኛውም ሰው እውነትን የመፈለግና እውነትን የመቀበል ችሎታ እንዳለው ሙሉ የሆነ እምነት አላቸው። ቁርአንና የመሐመድ ሱና ለእውነት ግልጽ ምስክር እስከ ሆኑ ድረስ እንዲሁም እግዚአብሔር ራሱን በፍጥረተ ዓለም ውስጥ እስከ ገለጠ ድረስ መንፈስ ቅዱስ ምን ሊጨምር ይችላል?

ሁለተኛ፤ በአብና በወልድ የተላከው መንፈስ ቅዱስ በቁርአን ውስጥ ከተገለጠው መንፈስ ቅዱስ ይልቅ በሐዋርያቱ ሕይወት ውስጥ ትልቅ ለውጥ አምጥቶአል። በአንድ የቁርአን ክፍል መንፈስ ቅዱስ አማኞችን በማገዝ ገነት ይገቡ ዘንድ እንደሚያበረታቸው ተገልጾአል (ሱራ 58፥21-22)። ይህ ክፍል ስለ መንፈስ ቅዱስ ተጨማሪ ትምህርትም አለው፤ ይኸውም አማኙ እግዚአብሔርን ወይም መሐመድን (ሐዋርያውን) የሚቃወሙ ሰዎች ዘመዶቻችን ቢሆኑ እንኳ በፍጹም ልንወዳቸው ስለማይገባ እንዳንወዳቸው ኀይል እንደሚሰጠን ተገልጾአል።

አስገራሚው ተቃርኖ በአዲስ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያው ምልክት በአማኞች ውስጥ በመኖር ለአማኙ የሚለግሰው ነገር ፍቅር ነው፣ "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር" (ገላትያ 5፥22) ነው።



የመሲሑ ተልእኮ ኀጢአተኞችንና አማኝ ያልሆኑትን ሰዎች መውደድ ነው። ይህ የመንፈስ ቅዱስም ባሕርይ ነው። "በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም። ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኀጢአተኞች ሞቶአልና... እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" (ሮሜ 5፥5-6:8)።

ሦስተኛ፤ ሙስሊሞች "ወደ ውሃ ምንጭ የሚመራቸው" ሸሪአ አላቸው። እንግዲያው መንፈስ ቅዱስ ምን ሊጨምር ይችላል? ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመገዛት ምን ማመን እንዲሁም ምን መተግበር እንደሚያስፈልግ ሸሪአ ያስተምራል። በዚህ ሂደት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ አንዳችም አስፈላጊነት አይኖርም። "ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል" (ዮሐንስ 16፥13) የተባለለት መንፈስ ቅዱስ አንዳችም ድርሻ ከሌለው እንዲሁም ሸሪአ የእርሱን ቦታ ሙሉ ለሙሉ የሚተካው ከሆነ የመንፈስ ቅዱስ አስፈላጊነት ቦታ አይኖረውም። ሰዎች በፍጥረታቸው ፍጹም መልካም ከሆኑና አንዳችም ክፋት በውስጣቸው የሌለ ከሆነ፣ ለሸሪአ ከመገዛት ውጪ ውስጣዊ ለውጥ ሊያስፈልገን አይችልም። ሸሪአን ማዕከላዊ ባደረገ የኑሮ ዘይቤ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ እጅግ በጣም አናሳ ነው።

## መሲሑና መንፈስ ቅዱስ

ቤተ ክርስቲያን ከመመሥረቷ አስቀድሞ መሲሑ ኀላፊነቱን በብቃት ይወጣ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶአል። ከድንግል ማርያም መወለድም የቻለው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነው። ወደ ማርያም መጥቶ የነበረው መልአክ ያወጀው የምሥራች፣ "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኀይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" (ሉቃስ 1፥35) የሚል ነው።

ከዚያም መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያጠምቀው መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ በኢየሱስ ላይ ወርዷል (ሉቃስ 3፥21-22)። ከዚያም ኢየሱስ፣ "መንፈስ ሞላበት" (ሉቃስ 4፥1)። የአደባባይ አገልግሎቱን ሲጀምር የመጀመሪያ ስብከቱን የጀመረው መኖሪያ ከተማው በሆነች በናዝሬት ምኩራብ ነው። ያንን የስብከት መልእክት የጀመረው የነቢዩ ኢሳይያስን መጽሐፍ እንዲህ ብሎ የሚጀምረውን ሐረግ በማንበብ ነው፣ "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው" (ሉቃስ 4፥18) የመሲሑ ኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የተሞላ ነበር።

ኢየሱስ በአገልግሎት ዘመኑ ስቅላቱንና ትንሣኤውን ተከትሎ ስለሚኖረው ስለ መንፈስ ቅዱስ ተግባር ቃል ገብቶአል:: ከላይ እንደ ተጠቀሰው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እውን የሆኑት፣ ኢየሱስ ስለመንፈስ ቅዱስ ቃል በገባው መሠረት ነው:: አንድ ጊዜ በቤተ መቅደስ የዳስን በዓል እያከበረ ሳለ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ አስደናቂ ቃል ኪዳን በመግባት በዓሉን ለማክበር የተሰበሰቡትን ሁሉ አስደንቋቸዋል::

ኢየሱስ ቆሞ፣ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ:: በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ:: ይኸን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለመንፈስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና" (ዮሐንስ 7፥37-39)::

ሽሪአ ማለት፣ "ወደ ውሃ ጉድጓድ የሚያመራ መንገድ" ማለት እንደ ሆነ ተገልጾአል:: በዚህ ክፍል እንዳየነው ኢየሱስ መንፈስን የገለጸው ከአማኞች ሕይወት የሚፈልቅ የሕይወት ውሃ እንደ ሆነ ነው::

በቤተ ክርስቲያን ተሞክሮ መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ተቃራኒ ሳይሆን መሲሑን በሁሉም መንገድ የሚያከብር ነው:: ስቅለትና ትንሣኤ የመሲሑ አገልግሎት ዋና ክፍል ናቸው:: መንፈስ ቅዱስም ይህን ቍልፍ ሐሳብ ሳይገልጥ (ሳይተረጉም) አያልፍም:: በተሰቀለውና ሞትን ድል አድርጎ በተነሣው መሲሕ፣ አማኞች የጸጋን ስጦታ የኀጢአት ይቅርታንና አዲስ ሕይወትን ተቀብለዋል:: መንፈስ ቅዱስ አማኞች በመሲሑ እንዲያምኑና የድነትን ስጦታ እንዲቀበሉ ጕልበት ይሰጣቸዋል::

መንፈስ ቅዱስ አማኞች ፍሬያማ ሕይወት እንዲኖሩ ያስችላቸዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ሲያብራራ:—

> የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጐነት፣ እምነት፣ የዋህነት፣ ራስን መግዛት ነው:: እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም:: የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር ሰቀሉት:: በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ (ገላትያ 5፥22-25)::

## መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ

በክርስትና ታሪክ ውስጥ የቤተ ክርስቲያንን መመሥረት እውን ያደረገው መንፈስ ቅዱስ ነው (ሐዋርያት ሥራ 8):: ከይሁዲነት ወይም ከእስልምና በተቃረነ መልኩ፣ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በሕግ እንዳትታጠር ዐርነት



ያወጣት መንፈስ ቅዱስ ነው:: እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ትልቅ ድርሻ ከያዘ በኋላ ክርስቲያኖች ሕገ ኦሪት በተለየ መንገድ እንዲያብራሩት አድርጓቸዋል:: ጴጥሮስና ጳውሎስ ለዚህ ሁነኛ ተጠቃሾች ናቸው::

መጀመሪያ ጴጥሮስ በኢዮጴ በጣራው ላይ ሆኖ ራቱን እየጠበቀ ሳለ፣ በራእይ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ ሸማ የሚመስል ዕቃ ከሁሉም ዐይነት እንስሳ ተሞልቶአል:— ዐሣማን ጨምሮ በሕገ ኦሪት የተከለከሉ እንስሳትን ይዞአል:: እንዲህ የሚል አስፈሪ ድምፅ ወደ ጴጥሮስ መጣ:—

> ጴጥሮስ ሆይ ተነሣና ዐርደህ ብላ የሚልም ድምፅ ወደ እርሱ መጣ:: ጴጥሮስ ግን:— ጌታ ሆይ አይሆንም አንዳች ርኩስ የሚያጸይፍም ከቶ በልቼ አላውቅምና አለ:: ደግሞ ሁለተኛ:— እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው:: የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ (ሐዋርያት ሥራ 10፥13-15)::

ይህ የሆነው ሦስት ጊዜ ነው:: ከዚያ በኋላ ሁለት መልእክተኞች ጴጥሮስን 30 ማይል ርቀት ላይ ወደ ምትገኘውና በቂሣርያ በሚኖረው መቶ አለቃ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት እንዲመጡ ጋበዙት:: ቆርኔሌዎስ ጴጥሮስን እንዲጋብዝ መመሪያ የተቀበለው ከመልአክ ነው::

ጴጥሮስ ቆርኔሌዎስ ቤት ሲደርስ መልእክቱን በመቀበል ከእርሱ ጋር ለመስማት በጉጉት የሚጠባበቁ ሰዎች ተሰብስበው አገኘ:: እርሱም ትሕትና በጐደለው አነጋገር፣ "አይሁዳዊ ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይተባበር ወይም ይቀራረብ ዘንድ እንዳልተፈቀደ እናንተ ታውቃላችሁ" (ሐዋርያት ሥራ 10፥28) በማለት ተናገረ::

ጴጥሮስ ለቆርኔሌዎስ እና ለቤተሰቦቹ ወንጌልን ሰበከ:: ቤተሰቡ ሁሉ ካመኑ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በጴንጤቈስጤ ቀን በሐዋርያት ላይ እንደ ወረደና ቤተ ክርስቲያን እንድትመሠረት እንዳደረገው ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ሰው ላይ ወረደ ጴጥሮስም በዚህ እጅግ ተደነቀ:: ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ ምን ሊያደርግ ይችላል? አሕዛብ እንዲሁም እንደ ሙሴ ሕግ ያልተገረዙ ሰዎች ቢሆኑም ጴጥሮስ ግን ያመኑትን ሁሉ አጠመቃቸው::

ከጥቂት ቀናት በኋላ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኢየሩሳሌም ነገሩን እንዲገልጽላቸው ጴጥሮስን ጠሩት:: የሃይማኖት ሥርዐት የሆነውን ሕገ ኦሪትን ያልታዘዙ አሕዛብ፣ በክርስትና ውስጥ እንዴት ሊታቀፉ ይችላሉ የሚለው

ጉዳይ ግልጽ ሊሆንላቸው አልቻለም። ነገር ግን ጴጥሮስ የተከሠተውን ነገር ሁሉ ነገራቸው። እነርሱም አስደናቂ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫ ሲሰሙ፣ "እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሓን ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ"(ሐዋርያት ሥራ 11፥18)።

## አስደናቂ ነጻነት

የሕገ ሙሴና የመንፈስ ቅዱስ ጉዳይ የሚለያይ (የሚነጣጠል) አይደለም። ጳውሎስና ጓደኞቹ የተላኩት በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን በአሕዛብ መካከል እንዲሰብኩ ነበር። በትንሿ እስያ በተጓዙበት ስፍራ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ተመሥርቶ ነበር። በዚህ ሂደት ውስጥ ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ሰዎች ሥርዐተ ግርዘትን እንዲፈጽሙ ሲደረጉ አንመለከትም። ከአይሁድ ወገን የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ አሕዛብ ከሙሴ ሕግ በራቀ መንገድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመሆናቸው ጉዳይ እጅግ በጣም አሳስቦአቸው ነበር። ከዚህም የተነሣ በሕገ ሙሴና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ልዩነት ለመመርመር በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ። የሙሴን ሕግ ከልቡ ያፈቅርና ይገዛ የነበረው ሐዋርያው ጴጥሮስ በስብሰባው መካከል በመቆም እንዲህ ሲል ተናገረ:—

> እንግዲህ አባቶቻችን እኛ ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀንበር በደቀ መዛሙርት ጫንቃ ላይ በመጫን፣ እግዚአብሔርን አሁን ስለምን ትፈታተናላችሁ? ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደ እርሱ ደግሞ እንድን ዘንድ እናምናለን (ሐዋርያት ሥራ 15፥10-11)።

የስብሰባው ታዳሚዎች በአንድ ልብ በመስማማት ለአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉ:—

> ለጣዖት ከተሠዋ ከደምም ከታነቀም ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል። ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ። ጤና ይስጣችሁ (15፥28-29)።

ቤተ ክርስቲያንን ከሕግ ሸክም ለማላቀቅ የተወሰነው ውሳኔ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ድፍረት የተሞላበትና እጅግ አስደናቂ የሆነ ውሳኔ ነው። ይህ ማለት ቤተ ክርስቲያን የእኔ ነው የምትለውና የራሷም የሆነ ባህልና ሃይማኖታዊ ሥርዐት አልነበራትም ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ማኅበረሰቦች ጥርቅም



ከመሆን ባሻገር መጽሐፍ ቅዱስን የምትተረጉምበት መንገድ ተቀይሯል። ውሳኔው የአማኙን ማኅበረሰብና መንፈስ ቅዱስን ባካተተ መልኩ፣ "እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል" ተብሎ ነበር የተገለጸው።

ከዚህ ውጪ፣ የኢየሩሳሌሙ ጉባኤ ውሳኔ የሚያመለክተው፣ ቤተ ክርስቲያን የክርስትናን ባህልና ምግባር የሚገልጽ አንዳችም ነገር እንዳላዘጋጀች ነው። ቤተ ክርስቲያን እንደ አይሁድ ታልሙድን እንደ እስልምና ደግሞ ሸሪአን አልቀረጸችም (ምናልባት ከዚህ የሚቃረነው ነገር በመካከለኛው ዘመን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ያዘጋጀችው ቀኖና ነው:— ይህ ለእኔ ከአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ለየት ያለ ነው)።

## መንፈስ ቅዱስና ጸርሰላይ

በኢየሩሳሌሙ ጉባኤ የተወሰነውና ለቤተ ክርስቲያን የተላለፈው ሚስዮናዊ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ትለውጣለች እንጂ ጸርሰላይ አታደርግም[13]። ቤተ ክርስቲያን ሰዎች መሲሑ ኢየሱስን ተቀብለው የእርሱን የሕይወት ዘይቤ እንዲከተሉ ማድረግ ቀዳማይ ዐላማዋ ነው። ሆኖም አንድ ክርስቲያን ከራሱ ባህል ወደ ሌላው ባህል መቀየር/መምጣት በጭራሽ አያስፈልገውም። አሕዛብ ክርስቲያኖች በሙሴ ሕግና በታልሙድ ላይ የተመሠረተውን የአይሁድ ባህል የራሳቸው አድርገው መቀበል/መውሰድ በጭራሽ አያስፈልጋቸውም። አሕዛብ እንደ ሆኑ ክርስትናን ተቀብለው መኖር ይችላሉ።

ከኢየሩሳሌም ጉባኤ ቀደም ብሎ የነበሩት ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር የኪዳን ግንኙነት ውስጥ ግደር የሚፈልጉ ሰዎች ወደ ይሁዲነት መቀየር አለባቸው የሚል እምነት ነበራቸው። ከኢየሩሳሌሙ ጉባኤ በኋላ ግን አሕዛብ ወደ ይሁዲ ባህል ሊቀየሩ እንደማይገባቸው ተወሰነ። በተቃራኒው የእግዚአብሔር የኪዳን ሕዝብ ለመሆን ብቸኛው መስፈርት አንድ ብቻ ነው፤ ይኸውም ንስሓ

---

[13] "ጸርሰላይ" (proselyte) እና "መለወጥ" (conversion) የተለያየ ትርጉም የሚወክሉ ቃላት ናቸው። ጸርሰላይ አንድ ሰው አንድን ሃይማኖት ሲቀበል ሃይማኖቱ የበቀለበትን ባህል አብሮ ሲቀበልና የራሱን ባህል ወግድ ሲል የሚከሠት ሲሆን መለወጥ ግን የራሱን ባህል እንደያዘ አንድን ሃይማኖት የሚቀበልበት መንገድ ነው። የይሁዲ እምነትና እስልምና ሰዎች ሃይማኖቱን ሲቀበሉ የራሳቸውን ባህል ዕርግፍ አድርገው በመተው የአይሁዶችን ወይም የዐረቦችን ባህል እንዲቀበሉ የሚያስገድድ ሲሆን ክርስትና ግን ሰዎች የራሳቸውን ባህል እንደያዙ የክርስትናን መሠረተ እምነት መቀበላቸው ነው። በዚህ መልኩ ክርስትና መለወጥን እንጂ ጸርሰላይነትን አይደግፍም፣ አያበረታታምም።

መግባት፣ ከኀጢአት መመለስ፣ ለመሲሑ ለኢየሱስ መገዛትና ከቤተ ክርስቲያን ጋር ኅብረት ማድረግ ነው።

## አዲስ ፍጥረት

መጽሐፍ ቅዱስ ሕግ በሰው ልብ ውስጥ እንደ ተጻፈ አበክሮ ይገልጻል። ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል አንዱ ይህንን የውስጥ ለውጥ ማስገኘት ነው። መንፈስ ቅዱስ ግለሰቡን አዲስ ፍጥረት ያደርገዋል። ከመሲሑ መምጣት አምስት መቶ ዓመታት ቀደም ብሎ እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ አማካይነት የሚከተለውን የተስፋ ቃል ሰጥቶአል፣ "ሕጌን በልቦናቸው እጽፈዋለሁ" (ኤርምያስ 31፥33)። ክርስቲያኖች ይህ ትንቢት፣ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኑ ሕይወት ውስጥ ከሚሠራው ሥራ የተነሣ በአዲስ ኪዳን ፍጻሜ አግኝቶአል የሚል እምነት አላቸው።

ከአንድ ተማሪ ጋር የነበረኝ ውይይት ሸሪአንና መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ያለውን ልዩነት በግልጽ ያሳያል። አብዲ መሐመድ ወደ ቤቴ ጉራ ብሎ የሚያስደስቱ ጫወታዎችን ከተጫወትን በኋላ፣ "እባክህን የክርስቲያንን ሸሪአ የሚያስረዳውን መጽሐፍ ስጠኝ። የክርስቲያኖችን መተዳደሪያ ደንቦች ማወቅ እፈልጋለሁ" አለኝ።

እኔም፣ "የመሲሑ ደቀ መዛሙርት መተዳደሪያ ደንባቸው መንፈስ ቅዱስ ነው። የዚህ ደንብ ማዕከል ደግሞ ለጠላቶቻችን እንኳ ሳይቀር ራሳችንን ለሌሎች አሳልፈን የምንሰጥበት የፍቅር አገልግሎት ነው። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ለመንፈስ ቅዱስ በመታዘዝ መኖር ቀዳማይ ዐላማቸው መሆኑን ማቴዎስ በወንጌሉ የጻፈው የተራራው ስብከት ትልቅ አብነት ነው። ሰዎች እንዴት መኖር እንዳለባቸው ስለማንኛውም ነገር ጠንቅቀህ ልትጽፍ አትችልም፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ሰውን አዲስ ፍጥረት ስለሚያደርገው ከእግዚአብሔር ሐሳብ ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዴት መኖር እንደሚገባው መንፈስ ቅዱስ ራሱ ይገልጽለታል። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ እንደ ገና ስለመፈጠር ሲናገር ዳግም መወለድ እንደ ሆነ አመልክቶአል" አልሁት።

በሌላ አጋጣሚ ደግሞ አንድ ያልተማረና በዕድሜ የገፋ አብዱላሂ የተባለውን የመሲሑ ደቀ መዝሙር የነበረን ሰው፣ "እውነተኛውን ነገር እንዴት ታውቃለህ?" አልሁት። እርሱም፣ "ልቤ ልክ እንደ ደነዘ ቢላዋ ነው። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እንደ ሞረድ ነው። በምሽት መንፈስ ቅዱስን በምስግበት ጊዜ



ልቤን ይሞርደዋል። ሁሉንም ነገር ስል እና ግልጽ ያደርግልኛል" ብሎ መለሰልኝ። ይህ መንፈስ ቅዱስ አዲስ ፍጥረት ሲያደርገን የምናገኘው ነጻ ስጦታ ነው። ጳውሎስ ጕዳዩን በዚህ መንገድ አስቀምጦታል፦

> "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ዐርነት አውጥቶኛልና" (ሮሜ 8፥1-2)።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ*

ዮሐንስ 16፥5-16፤ ገላትያ 5፥16-26

*የቁርአን ምንባብ*

ሱራ 2፥177፤ 58፥22

## የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች

1. በይሁዲነትና በእስልምና እምነት "ሕግ" ጥልቅ መሰብ ኖሮት፣ በክርስትና ግን ይህ ዐይነቱ አካሄድ በጭራሽ የማይደገፈው ለምን ይመስልዎታል?
2. እስልምና ለመንፈስ ቅዱስ አናሳ ስፍራ (ትኩረት) የሚሰጠው ለምንድን ነው?
3. በወንጌል ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተመሠረተው በክርስቶስ አገልግሎትና ሕይወት ላይ ነው። መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ በእስልምና ነገረ መለኮትና በክርስትና ነገረ መለኮት መኻል ያለውን መረዳትና የሚያስከትለውን እንድምታ ግለጽ።
4. ሱናና ሸሪአ የእስልምናን ባህልና የፖለቲካ ሥርዐት ለመመሥረት አንዱ ከሌላው ጋር ያለው መስተጋብር/ጥምረት እንዴት ይመስላል?
5. መለወጥና የአንድ የሃይማኖት ባህል አባል መሆን ልዩነቱ ምንድር ነው? መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ይለውጣል ሸሪአ ደግሞ የሰዎችን ሃይማኖትና ባህል ይቀይራል።

ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

# ጸሎት

## ሰላት—ኀብረት

አብዲ የሚለው ስም በሙስሊሞች ዘንድ ተወደደ ስም ነው። በዐረብኛ አብዲ ማለት፣ "አገልጋይ" ማለት ነው። ታማኝ የሆኑ ሙስሊሞች ሁሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተሰጡ ናቸው። ለዚህም ነው በቀን ዐሥራ ሰባት ጊዜ ያህል በእጆቻቸውና በግንባራቸው በመደፋት በእግዚአብሔር ፊት የሚሰግዱት። ታማኝ ሙስሊሞች በቀን አንድ ሰዓት ያህል ግዴታዊ ለሆነው ለሥርዐተ አምልኮ ጸሎት (ሰላት) ያውላሉ።

ሙስሊሞች በእግዚአብሔር ለተገለጠው እውነተኛ ሃይማኖት (ዲን) መገዛት ይፈልጋሉ። እውነተኛ ዲን የሆነው እስልምና በአምስት ወይም በስድስት የሃይማኖት ዐምድና በአምስት ወይም በስድስት ምግባራዊ ዐምድ ሊጠቃለል ይችላል። አጠቃላይ መሰጠቱ የሚገለጠው እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ለእውነተኛው ዲን በመገዛት ነው።

ሰላት (ስግደት) ለእግዚአብሔር መገዛታችንና መሰጠታችንን የሚገልጽ ሥርዐታዊ የጸሎት ልምምድ ነው። ሥርዐታዊ የስግደት ጸሎቶች ሙስሊሞች ለቁርአን ለተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ በሁለንተናቸው መገዛታቸውንና መሰጠታቸውን የሚያሳይ ቋሚ ምልክት ነው። በቀን አምስት ጊዜ የሚደረገው የጸሎት ሥርዐት፣ ሙስሊሞች ለአምላክ መሰጠታቸውን የሚያሳይ ውጫዊ ምልክት ነው። ለእምነቱ ሕይወትን የማስገዛት መንገድ የእስልምና ልምምድና የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ሰላትና የመጨረሻው ፍርድ (ዕድል ፈንታ) በአንድ የተቈራኙ ናቸው። ሰላትና ሰላት የሚወክለውን ዐይነት መገዛት ባለቤት የመሆናችንም ሆነ ያለመሆናችን ጉዳይ፣ እግዚአብሔር የመጨረሻ ዕድል ፈንታችንን በሚወስንበት ጊዜ ወሳኝ የሆነ ድርሻ አላቸው።

በአንድ ወቅት በመስጊድ ውስጥ የተከሠተ አንድ ድርጊት ለዚህ ጥሩ ናሙና ነው፦ የምሽት ጸሎቱ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የመስጊዱ ኢማም ለመስጊድ ማስጠገኛ ገንዘብ እንዲያዋጣ ጉባኤውን አስጠነቀቀ። "የመጨረሻው ፍርድ እየመጣ መሆኑን ልብ ልትሉ ይገባል። ለዚህ ጉዳይ ሳለመስጠት መወሰናችሁ የሚያስከትለውን ዘግናኝ ድርጊት ለጥቂት ጊዜ እንኳ አስቡ። ከመስጊድ

እንደወጣችሁ መኪና ገጭቶ ይገድላችኋል። በመጨረሻው የፍርድ ቀን ይህ ለመስጊድ የመስጠት መልካም ሥራ መልካምና ክፉን በሚመዝነው በሚዛናችሁ ላይ አይቀመጥላችሁም ማለት ነው። ምን ያህል ዘግናኝ እንደ ሆነ ልብ በሉ። ስለዚህ ገንዘብ ሳታዋጡ ከዚህ እንዳትወጡ አሳስባችኋለሁ"።

ይህ ምዕራፍ ልዩ አምልኮተ ሥርዐት የሆነውን ሰላትን የሚመለከት እንዲሁም ሰላት ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ በሙሉ መገዛትን በማመልከቱ ረገድ ያለውን ስፊ ትርጉም ይመረምራል። በመጀመሪያ ሰላት የሃይማኖቱ ዐምድ እንዲሁም የምግባር ማዕከል የመሆኑን ጉዳይ እንመለከታለን። በመቀጠልም ተለምዷዊ በሆነው የዘወትር ጸሎት ውስጥ፣ ለእግዚአብሔር መገዛትን በማመልከቱ ረገድ ያለውን ቦታ እንቃኛለን። ታማኝ ለሆኑ ሙስሊሞች እያንዳንዱ ሕይወት ሰላት ነው። ይኸውም በቁርአን ለተገለጠው ለእግዚአብሔር ፈቃድ በትሕትና መገዛት ማለት ነው።

## የእምነት አዕማድ

ከዚህ በፊት በነበሩት ምዕራፎች፣ የእምነት (የኢማን) ዐምዶችን ለመመልከት ሞክረናል። የአይሁድ የእምነት መገለጫ፣ "እስራኤል ሆይ፤ ስማ እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኀይልህ ውደድ" (ዘዳግም 6፥4-5) በሚለው በአንድ ጥቅስ እንደ ተጠቃለለ ሁሉ፣ ለሙስሊሞችም ዐቢይ የሆኑት የእምነት አናቅጽ በአንድ የቁርአን ጥቅስ ውስጥ ተጠቃለው ይገኛሉ።

ቁርአን አምስት ዐበይት የሚባሉ እምነቶችን ዐቅፎአል። ይህ ቊልፍ ጥቅስ እንዲህ ይላል:— "እናንተ የምታምኑ ሆይ! በአላህና በመልእክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ፤ በአላህና በመላእክቱም በመጽሐፎቹም፣ በመልእክተኞቹም በመጨረሻውም ቀን የካደ ሰው (ከውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ" (ሱራ 4፥136)።

ይህ ጥቅስ የእስልምናን እምነት (ኢማን) በዚህ መልክ ያጠቃልለዋል:—

1. በአንድ አምላክ ማመን
2. በእግዚአብሔር ነቢያት ማመን (ማንኛውም ሕዝብ የራሱ የሆነ ነቢይ ነበረው ሆኖም ግን መሐመድ የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ ናቸው)።
3. በተገለጡት መጽሐፍት ማመን (ይህ በምዕራፍ 6 ተጠቅሷል)።
    - *ሱሑፍ* (ገጾች) ለአብርሃም የተሰጠው ነገር ግን አሁን የጠፋ መጽሐፍ ነው።
    - *ተውራት* (ፔንታቱክ) ለነቢዩ ሙሴ የተሰጡት የአሪት መጻሕፍት።
    - *ዛቡር* (መዝሙር) ለነቢዩ ዳዊት የተሰጠው መጽሐፍ።
    - *ኢንጅል* (ወንጌል) ለመሲሑ ለኢየሱስ የተሰጠው።
    - *ቁርአን* ለነቢዩ መሐመድ የተሰጣቸው።
4. በመላእክት ማመን። ይህ እጅግ በጣም መሠረታዊ ጉዳይ ነው፤ ምክንያቱም መልእክቱን ያወረዱት/ያመጡት መላእክቶች ናቸውና።
5. በመጨረሻው ቀንና በመጨረሻው ፍርድ ማመን።



ሙስሊሞች አዘውትረው ስድስተኛ የእምነት ዐምድ ይጨምራሉ፤ ይህም ቃዳር (ውሳኔ) ሊለወጥ የማይቻል የእግዚአብሔር ፈቃድና ሉዓላዊነት። "የዓለማት ጌታ አላህ ካልሻም አትሹም" (ሱራ 81፥29)።

ሐዲስ እነዚህን ስድስት እምነቶች በዚህ መልክ ይገልጻል። ገብርኤል የእግዚአብሔር መልእክተኛ እምነት ባሕርይው ምንድን ነው ብሉ ጠየቀው። መሐመድም ሲመልስ፣ "ኢማን (እምነት) ማለት በአላህ በመጨረሻው ዘመን እና በቃዳር (ቅድመ ውሳኔ) ማመን ነው"[1]።

በየትም ስፍራ ላይ እስላም ያልሆኑ ሰዎች ሙስሊሞችን፣ "በምን ታምናላችሁ?" ብለው ቢጠይቋቸው የማንኛውም እስላም መልስ አንድ ዐይነት ነው። በእግዚአብሔር፣ በነቢያት፣ በመጻሕፍቶች፣ በመላእክትና በመጨረሻው ፍርድ እናምናለን ይላሉ። ብዙዎች ቅድመ ውሳኔን ሊጨምሩ ይችላሉ። ይህ ሺአይቶችም ሆነ ሱኒዎች በመካ ወይም በናይሮቢ ወይም ቴህራን ወይም ኒውዮርክ ከተማ እውነት ነው። በቀደመው ምዕራፍ እነዚህ ስለ እምነቶች የሚሰጡ አመለካከቶችን ተመልክተናል። እዚህ ስፍራ የመጨረሻው ፍርድ ከዚህ እምነት አንጻር ያለውን ሚና ትኩረት እንሰጣለን።

## <u>የመጨረሻው ፍርድ</u>

የመጨረሻው ዘመን ፍርድ ፍርሓት በቁርአን ውስጥ በሰፋት ተንጸባርቋል። ቀኑ ድንገት ሳይታሰብ ልክ እንደ መብረቅ ብልጭታ ይመጣል። የመጨረሻው ቀን መምጣቱን ለማወጅ መለከት ይነፋል። ሰማያት ለሁለት ይከፈላሉ፤ ምድር ተሰባብራ በመድቀቅ ወደ አቧራነት ትቀየራለች።

[1] *Tradition* by Saheeh Muslim.

በዚያ በመጨረሻ ቀን በገሃነም ከአጋንንቶች ጋር የሚጣሉትን ወይም ወደ ገነት የሚገቡትን ሰዎች እግዚአብሔር ይለያል። ገሃነም የተገለጸው አስፈሪ (አስደንጋጭ) በሆነ ሥዕል ነው። ወደ ላይ የሚወነጨፍ የእሳት ትንታግ፣ የሚሰነፍጥ ጢስ፣ ፍል ውሃ፣ ኾድ ውስጥ የሚቃጠል ጭራሮ መጨመሩ ወዘተ የመሳሰሉ መግለጫዎች አሉት። ገነት የተገለጸው ውብና የደስታ ቦታ ተደርጉ ነው። የዛፍ ፍሬዎች፣ ወንዞች፣ ዛጕላማ ዐይን ያላቸው ኮረዳ ልጃገረዶች፣ ያማረ ስጋጃ ምንጣፍ፣ ያሸበረቀ ሕንፃዎች፣ የተትረፈረፈ የወይን ጠጅ (ሱራ 88፥9-16፤ 56፥11-24)። ደግና ክፉ ሥራው የተጻፈበት የእያንዳንዱ ሰው የራሱ መጽሐፍ ይከፈታል። እግዚአብሔርም እምነታችንንና ሥራችንን ይመረምራል።

እግዚአብሔር እኩያ (ሽሪክ) አለው ብለው የሚያምኑ ሁሉ ይኰነናሉ። ይህም የከፋው ኀጢአት ነው፤ ምክንያቱም ከአንድ በላይ አምላክ ማምለክ ነው። መልእክተኞችን ከእግዚአብሔር የሚለዩ ወይም የተወሰኑ መልእክተኞችን ተቀብሎ ሌሎችን የማይቀበል ይፈረድበታል (ሱራ 3፥84-87፤ 48፥8-10)። መልካም ሥራና ክፉ ሥራ ሁለቱም ሚዛን ላይ ይቀመጣሉ። መልካሙ ሥራ ከክፉው ሥራና እምነት በልጦ ከታየ እግዚአብሔር ምሕረቱን እንደሚጨምርለት ይታመናል (ሱራ 23፥101-104፤ 21፥47)።

ሙስሊሞች በመጨረሻው ፍርድ ሰዓት መሐመድ እንደሚማልድ ያምናሉ። ቁርአን ከፍቃድ ውጪ አማላጅነት የለም ይላል (ሱራ 20፥109)። የዐሥራ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን የሱፊ የነገረ መለኮት ምሁር አልገዛሊ መሐመድ ለማማለድ ፈቃድ እንደሚጠይቅ ይገልጻል። በመጨረሻው ፍርድ ወደ ፊት ይወጣና በመጮኽ፣ "እግዚአብሔር ለወደደውና ለመረጠው እስከ ፈቀደ ድረስ እስካሁን ባለው እኔ ለመማለድ ትክክለኛ ሰው ነኝ" ይላል። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሲመልስ፣ "መሐመድ ሆይ አንተ የምትሰማ ስለሆንህ ራስህን ቀና አድርገህ ተናገር የምትፈልገውን ጠይቅ ይደረግልሃል"[2] ይለዋል።

በሚቀጥለው ምዕራፍ የክርስቲያኖችንና የሙስሊሞችን ታሪክ የሚመለከተውን ክፍል እንዳስሳለን። አሁን ትኵረት የምናደርገው በአምስቱ የእምነት አዕማድና የመጨረሻ ፍርድ ማዕከላዊና ሙስሊሞች ትልቅ ግምት በሚሰጡት የታሪክ ትርጕም ነው። እስልምና ማለት በመሠረቱ መሓሪው አላህ በመጨረሻው ፍርድ ርኅራኄ እንደሚያደርግ ተስፋ በማድረግ ለፈቃዱ መገዛት ነው።

---

[2] Jane Idleman Smith, ed., *The Precious Pearl: A Translation from the Arabic* (Missoula, Mont.: Scholard Press, 1979) 59-60.



# የምግባር አዕማድ

የሰላት (የስግደት) መንፈስ ራሱ፣ ለሥነ ምግባር ዐምዶች መገዛትን የሚያመለክት ነው። ምዕራፍ 11 እነዚህን አዕማድ በአጭሩ በመቃኘት ለኋለኛው ዘመን የእስልምና ሕግ (ሽሪአ) ያለውን አንድምታ በዳሰሳ መልክ ተመልክተናል። ዐምዶቹ የእምነት መግለጫ (ሽሃዳ) ጸሎት (ሰላት)፣ ጾም (ሰውም)፣ ምጽዋት (ዘካ) እና ሃይማኖታዊ ጉዞ (ሃጂ) ናቸው። ብዙ ሙስሊሞች ስድስተኛ ሕግ ይጨምራሉ፤ ይኸውም ቅዱስ በሆነው የሃይማኖት ጦርነት (ጂሃድ) ውስጥ ተካፋይ መሆን። እነዚህ ምግባሮች እያንዳንዳቸው፣ በእስልምና መንፈሳዊነት ላይ ጥልቅ ዕውቀት የሚለግሱ ናቸው።

<u>በጸሎት መገዛት</u>

የእምነት አዕማድን ለመረዳት የመጨረሻው ፍርድ ወሳኝ እንደ ሆነ ሁሉ፣ በምግባር ሕጉ ላይ እንደ ተገለጸው፣ ሥርዐታዊ ለሆነው ጸሎት (ሰላት) መገዛትም ወደ ፍጽምና ለሚያደርሰው ምግባራዊ መሰጠት መሠረት ነው። ሥርዐተ አምልኮአዊ የሆነው ጸሎት፣ የእስልምናን ትርጕምና ማራኪነት የሚፈታ ቊልፍ ነው። ሰላት በእግዚአብሔር ፊት በንስሓ (ጸጸት በተሞላበት) መንፈስ የመቅረብ ሂደት ስለሆነ፣ ሰላት የእስልምና እስትንፋስ ተደርጉ ይወሰዳል።

የሚኖናይቱ ክርስቲያን ኢቫን ቦንትራገር ሲናገር፣ በእግዚአብሔር ፊት ፊቱን ከወለሉ ጋር በማገናኘት በቀን አምስት ጊዜ ለበርካታ ጊዜያት እንደ ሰገደ ይናገራል። ይህንንም ያደረገው በእስልምና ሥርዐት ውስጥ ያለውን መንፈሳዊነት ለመመርመር ነው:—

> ጸሎት የማደርሰው ግንባሬን ወለሉ ላይ በመድፋትና እጆቼን ወለሉ ላይ በመዘርጋት ነው። በአካሌም ሆነ በአንደበቴ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛቴን እያወጅሁ ነበር። አገልጋይ ለመሆን ራሴን ሰጥቼ ነበር። በየዕለቱ ለስግደት መቅረቤ ልማድ እየሆነ ቢመጣም እንኳ፣ የጸሎቱን ትርጕም አላደበዘዘውም ነበር። በእያንዳንዱ ጧት ንጋት ላይ፣ ከዚያ ከሰዓት ላይ፣ ከቀትር በኋላ፣ ጀንበሯ ከዘቀዘቀች በኋላ እንዲሁም ለመኝታ ወደ ዐልጋዬ ከመሄዴ በፊት እጸልይ ነበር። ድሮ ዐልፎ ዐልፎ ብቻ የነበረኝ ዐይነት ልምምድ አሁን ዘወትር እንዲኖረኝ አድርጉልኛል። ይህ የዘወትር ልምምድ ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝን ኅብረት ዕለት በዕለት እንድጠብቅ ትልቅ ትምህርት ሰጥቶኛል። እስልምና የሚያስተምረውን ያድግግሞሽ ጸሎትን ጥቅም ዐውቄያለሁ። እኔ

> ብሆንም እንኳ፣ ከዚህ ዐይነቱ ጸሎት በትሕትና የመገዛትን ትርጉም አይቻለሁ:: እንደ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር ለመኖር ራሴን እሰጣለሁ[3]::

በገዳም ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች ለብዙ መቶ ክፍለ ዘመን ለእግዚአብሔር ሙሉ መገዛትን የሚያመለክት ሥርዐታዊ ምልክት ያለውን ጸሎት ይጸልዩ ነበር:: ብዙ ሙስሊሞች የጾምንና የጸሎትን ሥነ ሥርዐት በተደጋጋሚ እንዲያከናውኑት ሁሉ፣ የክርስቲያኖችም የጾም ጸሎት ሥነ ሥርዐት ትልቅ መንፈሳዊ ዋጋ አለው:: በእግዚአብሔር ፊት መደፋትና ጾም ጸሎት ማድረስ የሙስሊሞች ልምምድ ብቻ አይደለም::

ለሙስሊሞች በቀን አምስት ጊዜ መጸለይ ግዴታ ነው:: ሙአዚን ማኅበረሰቡን ለጸሎት ይጠራል (አድሃን):: ሙስሊሞች አናሳ በሆኑበት ማኅበረሰብ በጉረቤቶቻቸው ካልታገዱ በቀር አምስቱን የጸሎት ጥሪዎችና ግብዣዎች ከጸሎት ማማው ላይ በመሆን አዛንን ያውጃሉ:: አዛን ማዕከላዊና ለድርድር የማይቀርቡ የእስልምናን እምነትና ተልእኮዎችን የያዘ ጥሪ ነው:: የአዛን ጥሪም እንደሚከተለው ነው፣ " ምስክርነቴን እሰጣለሁ፤ አላህ እጅግ ታላቅ ነው፤ መሐመድም የአላህ መልእክተኛ ነው፤ ኑና አምልኩ"::

በፍጥነት ጉባኤው ለጸሎት ይሰበሰባል:: ጸሎቱን ለማድረስ ወደ መስገጃ ስፍራው መምጣት ያልቻሉ ባሉበት ስፍራ በግላቸው ሥርዐተ አምልኮውን ያደርሳሉ:: ከእያንዳንዱ ጸሎት በፊት ሥርዐታዊ መንጻት ወይም መታጠብ የግድ ነው:: እያንዳንዱ ጸሎት የተወሰነ ቍጥር የጸሎት ረካ ወይም (ኡደቶች) ይጠይቃል:: ንጋት ላይ ሁለት ረካዎች (በመቆም በመጉንበስ በመንበርከክ የሚደረግ የጸሎት ኡደት) ቀትር አራት ረካዎች፤ እጋማሽ ከሰዓት በኋላ አራት ረካዎች፣ ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ሦስት ረካዎች፣ በመኝታ ሰዓት አራት ረካዎች:: እንደ ሥርዐቱ እነዚህ በአጠቃላይ ዐሥራ ሰባት ረካዎች ልክ እንደ ሥርዐቱ መፈጸም አለባቸው:: ሰላት ከዕቅድ (ኒያ) ይጀምርና ሰባት ደረጃዎችን ይይዛል:—

1. ታክቢር (አላህ ታላቅ ነው) ሲባል ሁለት እጆች በእያንዳንዱ የፊት ክፍል ይቀመጣሉ:: ይህ አምላኪው ፊቱን ወደ ካባ ሲያዞር ሰይጣንንና የዓለምን ትችት እንደሚቃወም ያመለክታል:: ማህራብ (በመስጊዶች) ግድግዳ ላይ የከአባን ቂብላን (አቅጣጫን) ለጸሎት የሚያመላክት ነው

[3] Evan Bontrager, "My Participation in Ramadan," *The Mennonite* (19 November 2002): 11.



(ሙስሊሞች ለጸሎት ፊታቸውን ወደ ካዕባ አቅጣጫ መመለስ አለባቸው)::
2. ቀኝ እጅ በግራ እጅ ላይ አነባብሮ ደረት ላይ ማስቀመጥ እና እግዚአብሔርን ለማክበር የማነብነብ ጸሎት ማድረግ:: መደምደሚያው ሐሳብ፣ "ከተረገመው ዲያቢሎስ ሸሽቼ በእግዚአብሔር እተገናለሁ" ይላል:: ከዚያም አምላኪው በአል-ፋአታሃ የተጻፈውን ጸሎት ይደግማል (የመጀመሪያው ቁርአን ክፍል):: ይህም ፍጽምና እንደ ተሞላበት የጸሎት ናሙና ይታያል:: ይህም ግለሰቡ ቆሞ የሚደግመው ጸሎት ነው:: ብዙ ጊዜ ሌላ የቁርአን ምዕራፍ (ሱራ) ሊደገም ይችላል::
3. እንደቆሙ ከወገብ ዝቅ ብሎ ታክቢርን መድገም (እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ ነው ማለት)::
4. ቀጥ ብሎ መቆም::
5. በጉልበት ወደ ምድር በማጉንበስ ወለሉ ግንባርን እስኪነካ ድረስ ወደ ምድር መውረድ፣ ሁለቱም እጆች ሁለቱም ጉልበቶች እንዲሁም የእግር አውራ ጣቶች በመሬት ላይ ይሆናሉ::
6. መቀመጥ እና ሁለት እጆችን በጉልበቶች ላይ አድርጉ ሌላ ተክቢር መድገም::
7. ታክቢርን እየደገሙ እንደ ገና ወደ ምድር መውደቅ:: ከዚህ በኋላ አምላኪው ታክቢርን እየተናገረ ይነሣና የጸሎት ኡደቱ (ረካ) ይጠናቀቃል:: እነዚህ ሰባት ደረጃዎች በአንድ ረካ (በጸሎት ዑደት) የታቀፈ ነው:: የጸሎት ኡደቱ ሲጠናቀቅ አምላኪው ሸሃዳን ይደግማል፣ "ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም፤ መሐመድ የአላህ ነቢይ ነው":: ወደ ቀኝና ወደ ግራ በመዞር ጠባቂ መላእክት በቅርብ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ:: እርስ በእርሳቸውም ሰላምታ ይለዋወጣሉ::

ከሥርዐታዊው ጸሎት በኋላ አምላኪዎች ቢመጡና እጆቻቸውን በመክፈት መዳፎቻቸውን ወደ ላይ በማንሣት ጸሎታቸውን ለእግዚአብሔር ሊያቀርቡ ይችላሉ:: ይህ የአክብሮት ጥያቄ (ዱአ) የሚቀርበው በዐረብኛ ላይሆን ይችላል:: ሆኖም ማንኛውም ሥርዐታዊ ጸሎቶች (ሰላት) መደረግ ያለባቸው በዐረብኛ ነው[4]:: አብዛኛውን ጊዜ የዱአ ጸሎት በሚቀርብበት ጊዜ አምላኪዎቹ ዐይኖቻቸውን ወደ ላይ ያነሣሉ፤ መዳፎቻቸውን ከፍተው ወደ ላይ

[4] Muhammad Hamidullah, *Islam in a Nutshell* (Philadelphia: Ayesha Begum Hyderabad House, Inc., 1990), 12-53.

ያነግሉ። በተረጋጋ መንፈስ አዛኝና ሩኅሩኅ ለሆነው አምላክ ምልጃቸውን በሰላት ለአምላክ ያቀርባሉ።

ሁል ጊዜ አንድ ሰው የሚደረጉ ጸሎቶቹን ለመምራት ከፊት ይቆማል። ይህ ሰው ኢማም ሊሆን ይችላል። ሆኖም ይህ ቢያንስ በሱኒ ጉባኤዎች ግዴታ አይደለም። አትኩሮትን እንዳይቀንስ በሚል ሁል ጊዜ ሴቶች ከወንዶች እንዲለዩ ይደረጋል። ሙስሊሞች የጸሎትን ሰዓት ካሳለፉ ማካካሻ ረካዎች ያደርጋሉ። ይህንንም የሚያደርጉት ምሽት ላይ በመስጊድ ውስጥ ነው። ከጉባኤ መደበኛ ጸሎቶች በፊትና በኋላ ግለሰቦች በመስጊድ ውስጥ ለብቻ ቆመው ረካዎችን ሲደግሙ ይታያሉ። ሙስሊሞች እንደ ነገሩኝ አንዳንድ አምላኪዎች ለሠሩት መጥፎ ድርጊት ማካካሻ ተጨማሪ ረካዎችን ያደርጋሉ።

## ጉባኤው

በጸሎት ጊዜ በመስጊድ መሰብሰብ ለሙስሊሞች የሚመረጥ ነው። ለአምስቱም የጸሎት ጊዜ ወደ መስጊድ መሄድ ካልተቻለ ማንኛውም ሙስሊም ባለበት ቦታ ሆኖ ጸሎት ማድረስ ይችላል። ሆኖም በዕለተ ዐርብ ለእኩለ ቀኑ ጸሎት አካባቢው በሚገኝ መስጊድ እንዲገኝ ይበረታታል። ብዙ ሙስሊም ማኅበረሰቦች አንድ ትልቅ መስጊድን፣ "የዐርብ መስጊድ" ብለው ይለዩታል። በዚህ መስጊድ በአካባቢው የሚገኙ ሙስሊሞች ሁሉ በሳምንት አንድ ጊዜ ተሰብስበው ይሰግዳሉ ስብከትም ያዳምጣሉ። ነገር ግን ወንዶችና ሴቶች በማንኛውም ወቅት በመስጊድ በአንድነት አይሰበሰቡም። አንዳንድ ጊዜ ለሴቶች ለብቻ መስጊድ አላቸው፤ ብዙ ጊዜ ግን ሴቶች ከዋናው ጉባኤ በተለየ ስፍራ እንዲሰበሰቡ ይደረጋል።

# ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ

ታማኝ የሆኑ ሙስሊሞች ሁሉ ሰላት የሚጠይቀውን ምግባር ሁሉ ለመፈጸም ራሳቸውን የሰጡ ናቸው። በእስልምና ሕግ ላይ ጥናት ያካሄዱ የእስልምና የነገረ መለኮት ምሁራን፣ ለእግዚአብሔር ሕግ በታማኝነት ለመገዛት ይቻል ዘንድ፣ ጥቃቅን ናቸው የሚባሉትን ሕግጋት ሳይቀር ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ሁሉ በሚሆን መልኩ ይተነትኑታል። በነገረ መለኮት እግዚአብሔርን ማወቅ እንችላለን? ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሊኖረንስ ይችላል? ይህ ጥያቄ በሙስሊሞች መካከል የሚገኘውን የሱፊ እስልምናን አካሄድ ወለደ። ምንም እንኳ ዋነኛው የእስልምና እምነት (ኦርቶዶክስ እስልምና) ሰዎች ከእግዚአብሔር



ጋር በሚያደርጉት ግላዊ ግንኙነት እግዚአብሔርን ሊያውቁት አይችሉም ቢልም፣ ሱፊዎች ግን በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ በመታቀፍ እግዚአብሔርን ማወቅ ይፈልጋሉ። ዐልፎ ዐልፎ በኦርቶዶክስ እስልምናና በሱፊ እስልምና መካከል የነገረ መለኮት ውጥረቶች ስለሚካሄዱ ግጭቶች ይፈጠራሉ።

ለምሳሌ በአንድ ወቅት በቴምፕል ዩኒቨርስቲ በእስልምና ላይ የዶክትሬት ጥናቱን የምታካሂድ አንዲት የሶሪያዊት ሙስሊም አንድ ቀን ሙሉ በተካሄደ ዐውደ ጥናት ላይ እኔ ለማስተምራቸው ክርስቲያን ተማሪዎች ንግግር አደረገች። በሰሌዳው ላይ ከላይ "አላህ" ከሥር ደግሞ "ሰው" ብላ ከጻፈች በኋላ የእምነትና የምግባር አዕማድን ስትተነትን እግዚአብሔር ሰዎች ከእርሱ ጋር ለማድረግ ከሚፈልጉት ግላዊ ግንኙነት/መስተጋብር ሊታወቅ እንደማይችል ዐልፎ ዐልፎ ትገልጽ ነበር። "አላህ" እና "ሰው" በሚሉት ቃላት መካከል የአንድ ኢንች ያህል ውፍረት አግድም በማስመር የሱኒ እምነቷ የሚያስተምረውን ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት ያለመቻልን ነገረ መለኮት አበክራ ታስረዳ ነበር። ንግግሯን የቋጨችው እርሷ በግሏ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመገዛት ራሷን የሰጠች ሰው ብትሆንም፣ እግዚአብሔርን በግሏ ለማወቅ ድፍረት እንዳልሆናችት በመግለጽ ነው።

## ሱፊ ተማሰሉታዊነት

የሱፊ ተማልሉታውያን (mysticism) ለእግዚአብሔር በመገዛት ላይ ትኩረት ከሚያደርግ ሆኖም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን ማድረግ እንደማይቻል ከሚያስተምረው ቀጥተኛ መንፈሳዊነት በተለየ መንገድ ነው እምነታቸውን የሚያራምዱት። ሱፊዎች ከእግዚአብሔር ጋር በረቀቀ መንገድ የሚያገናኛቸውን ሥልጣን ይናፍቁታል፤ ይፈልጉታልም። የሱፊዎች እግዚአብሔርን የሚፈልጉበት አቅጣጫ በክርስቲያኖች ነገረ መለኮት ማዕከል እንደ ሆነው፣ "እኔና-አንተ" በሚለው ግንኙነት አይደለም። ይልቁንም ሱፊዎች በመለኮት (ፋና) ውስጥ በመሆን የራሳቸውን ማንነት መጥፋት/ማደብዘዝ ይፈልጋሉ። ኦርቶዶክስ ሙስሊሞች በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ምንም ግንኙነት የለም በሚለው በቁርአናዊ አስተምህሮ በታንዚል ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ሆኖም ሱፊዎች በቁርአን ውስጥ አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔር በልንጀሮች (አወልያ) እንደ ነበሩ አመልክተዋል።

አብርሃም ካሊል አላህ (የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጅ) ነበሩ:: ስለዚህ ሱፊዎች ለእግዚአብሔር መገዛትን ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅነታቸውን የሚያሳድግላቸው እንዲሁም ከመለኮት ጋር የረቀቀ ግንኙነት መኖሩን መረዳት ይፈልጋሉ (ማይዳ 5፥53-54፤ ዩኑስ 10፥62)::

አምላኪዎቹ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዴት ሊያደርጉ ይችላሉ? የሱፊ መንፈሳዊነት ትኩረት የሚሰጥባቸው ብዙ ጭብጥ መልእክቶች አሉት:: በዚህ አጭር ክፍል እነዚህን መንፈሳዊ መንገዶች ለመመርመር አይቻልም:: ቤተሰቦቻችን ለረዥም ዓመታት በናይሮቢ ኢስሊ በሚገኘው መስጊድ መንገድ ማዶ ኖረዋል:: ስለዚህ ስለዚህ ማኅበረሰብ የምለው ነገር አለኝ:: እነርሱም አራት ናቸው ይኸውም:— መንፈሳዊ መሪ፣ ከማኅበረሰቡ አንደ አማላጅ ሆኖ የሚያገለግል ጻዲቅ የሥርዐቱ መሥራች፣ እግዚአብሔርና ጻድቃንን ማስታወስና አምላኪዎችን ምስጢራዊ በሆነ መንገድ ከመለኮት ጋር ኅብረት በሚፈጥርላቸውን የማኅበረሰቡን ምስጢር መካፈል:: በሁሉም የሙስሊም ማኅበረሰብ ማለትም ኡማ የሱፊ እንቅስቃሴ አለ፤ እነዚህ ሱፊ ማኅበረሰቦች ታሪቃስ (መንገዶች ወይም ሥርዐቶች) በመባል ይታወቃሉ::

ስፔንሰር ትሪሚንግሃም እንዲህ ሲል ጽፎአል:—

> የእስልምና ሃይማኖት ሥርዐት መሠረት ከእግዚአብሔር ጋር መተሳሰርን (ኅብረት ማድረግን) የሚፈልግ አማኝ በዚህ መንገድ ልምምድ ካለውና ልዩ በሆነ በረከት (በረካ) የተባረከን ሰው ምሪትና በአማኞች እና በእግዚአብሔር መካከል የመማለድን ተግባር የሚፈጽም ሰው ያስፈልጋል:: የታሪቃን መሥራች የነበሩት እንደዚህ ያገለገሉ እና መንፈሳዊ ዘሮቻቸው ይህን ባርኮት (በረካ) በመውረስ አገልግሎታቸው እስከዚህ ቀን ድረስ የቀጠሉ ናቸው[5]::

በኢስሊ የማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙት የሱፊ መንፈሳዊ መሪዎች፣ የማዕረጋቸውን ምልክት በቀደሪያ ሥርዐት ውስጥ ይቀበላሉ:: ማኅበረሰቡም ይህንን በረከትና ሥልጣን ያገኘው ከቅዱሳን ጋር ካለው የቀረበ ግንኙነት እንዲሁም የሥርዐቱ መሥራች ከሆኑት ከአብዱል ቃዲር አል ጂላኒ በቀጥታ መንፈሳዊ ሥልጣንና ኀይል በመማር ነው:: መሥራች አባላት ይህንን ብልኀት የተቀበሉት በነቢዩ መሐመድ መስመር መንፈሳዊ ሥልጣን ከነበራቸው የኀይል ሰዎች ነው:: ሱፊዎች ይህንን የሥልጣንና የበረከት መስመር በቀጥታ

[5] J. Spencer Trimingham, *Islam in Ethiopia* (New York: Barnes and Noble, 1965), 232.



የመንደሩን ቅዱሳን በኀይል፣ በበረከትና በምሥጢራዊ መንገድ ከመሥራች መሪዎች ጋር የሚያገናኝ ሰንሰለት ነው::

የቃደሪያ ሼክ ተከታዮች በናይሮቢ ኢስሊ ሁል ጊዜ ሐሙስ ማታ ከመሪያቸው ጋር በመስጊድ ይገናኛሉ:: በሌላ ጊዜ በሼኪው ቤት ይገናኛሉ:: ይህ ግንኙነት ሁል ጊዜ መንፈስን ሙሉ በሙሉ በማስገዛት የእግዚአብሔርን ስም ደጋግሞ መጥራትን ያካተተ ነው:: እርሱም እግዚአብሔርን ማስታወስ (ዲክር) ይባላል:: የመሐመድንና የሥርዐቱን መሥራቶቹንም ስም በመደጋገም ይጠራሉ:: ይህንን የሙገሳ ንግግር የሚያደርጉት አንዳንዴ ሻይ ለመጠጣትና መነቃቃት የሚፈጥረውን ጫት ለመቃም በርጋታ ቁጭ ብለው ነው:: የምልክት ጨርቆችን ያውለበልባሉ ዕጣን ያጨሳሉ:: የአምልኮው ግብ የማንነትን ስሜት ለመግደልና ወደ ሁልዐቀፍነት ለመዋጥ ነው::

## የአማላጅ አስፈላጊነት

አንድ ጊዜ ከጓደኛዬ ከፋራ ዓሊ ጋር በመሆን በየዓመቱ ወደ መቃብር ስፍራ የሚሄድበትን ሃይማኖታዊ ጉዞ አብረን ተጓዝን:: ሁሉም የሱማሌ ጐሣዎች የሱፊ ቅዱሳን ናቸው:: በየዓመቱ ወደ መቃብር ስፍራ የሚደረገው ሃይማኖታዊ ጉዞ የጐሣዎች ኅብረት የሚታደስበት እንዲሁም የሞቱ ጻድቃንን ኀይል ምስጢራዊ በሆነ መንገድ የሚከፈሉበት መንፈሳዊ ክብረ በዓል ነው:: የሃይማኖት ተጓዦቹ እየጮሁ (እያለቀሱ) እየጸለዩ እና ከመቃብሩ ላይ ዐፈር በእጆቻቸው በመውሰድ ሰውነታቸው ላይ እየበተኑ ነበር ወደ መካነ መቃብሩ የተጓዙት::

ወደ ቤት ጉዞ እንደ ጀመርን፣ ፋራ እንዲህ አለ፣ "እኛ ኀጢአተኞች ስለሆንን እግዚአብሔር ጸሎታችንን አይሰማም:: ከእኛ እንደ አንዱ በመሆኑ ምክንያት ነው ወደ ሱፊ ቅዱስ መቃብር የሄድነው:: እርሱ ጸሎታችንን ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰውን መሐመድን ይማልድልናል:: እናውቃለን ይህ መልካም የሚባለው እስልምና አይደለም፤ ምክንቱም በእስልምና ምንም አማላጅ የለም ሆኖም ሌላ አማራጭ መንገድ የለንም"::

እኔም በበኩሌ እንዲህ አልሁ፣ "ጭንቀታችሁ ይገባኛል:: ነገር ግን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ የመደበው አንድ አማላጅ አለ:: እርሱም መሲሑ ነው:: መሲሑ አማላጃችን እንዲሆን እግዚአብሔር ሾሞታል"::

"አስገራሚ ነው፤ እስኪ ስለዚህ ነገር በደንብ ንገረኝ" አለ ፋራ።

ፋራ የሱፊ እምነቱ ሙሉ ለሙሉ ምቾት አልሰጠውም። ለዚህ ምክንያቱ የዋነኞቹ የሱኒ ሙስሊሞች የሱፊን እምነት እምብዛም ስለማይቀበሉ ነው። ሱፊዝም ለእርሱ በጣም ወሳኝ ትርጉም ያለው እምነት ቢሆንም፣ እርሱና ብዙ ሙስሊሞች ከእስልምና እምነት ጋር የሚቃረን እንደ ሆነ ይሰማቸዋል።

በሌላ ጊዜ አንድ ባልንጀራዬ በጃቫ ከተማ ወደ አንድ ሱፊ ቅዱስ መቃብር ወሰደኝ። እናም የመቃብሩን ታምርና የመማለድ ኀይል በብዙ መቶዎችና ሺዎች የሚቆጠሩ የሃይማኖት ተጓዦች ወደዚህ መቃብር ስፍራ በመምጣት እንደሚያከብሩት አብራራልኝ።

"ይህ በእስልምና እምነት ተቀባይነት ያለው ነውን?" ብዬ ጠየቅሁ።

ባልንጀራዬም፣ "ይህንን ጥያቄ አትጠይቅ ሁላችንም ይህ ትክክለኛ ሙስሊም መከተል የሌለበት እንደ ሆነ እናውቃለን" አለኝ። ሆኖም ስለ ሱፊዎች ከተወሰነው ተቃርኖ ባሻገር የሱፊዎች እምነት ለሱኒ ሙስሊሞች ሕይወት የሚለግስ ነው። ሱፊዝም ከፈጣሪ ጋር ለመገናኘት ላለው ፍላጐት መልስ ነው።

በአራተኛው ክፍለ ዘመን ይኖር የነበረው ሰሜን አፍሪካዊው ክርስቲያንና የነገረ መለኮት ምሁር አውግስጢኖስ፣ ልባችን በእግዚአብሔር እስኪያርፍ ድረስ ዕረፍትን ፈላጊ መሆኑን በመገንዘቡ እንዲህ ሲል ይጸልያል፡— "አምላኬ ሆይ፤ እንዴት ላይህ እችላለሁ? አንተን አምላኬን ስመለከትህ የተባረከውን የሕይወት ደስታን እመለከታለሁ። በሕይወት እንድኖር አንተን መመልከት አለብኝ"[6] ይህ የሱፊዎች እንቅስቃሴም ደስታንና ዕረፍትን ፍለጋ ላይ መሆናቸውን የሚያስረግጥ ነው።

## መሲሑና የሱፊዎች እውነት ፍለጋ

ሱፊዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት የሚያደርጉት ፍለጋ በመሲሑ በኩል በሆነ አስገራሚ ስጦታ ተፈጽሟል። መሲሑ በእግዚአብሔር የተሾመ አማላጅ ነው። በእርሱ ሕይወትና አገልግሎት ሁላችን ቤተሰቦች፣ ጓደኞች ወንድና

[6] Saint Augustine, *Confessions,* translated by R. S. Pine-Coffin (Baltimore: Penquin, 1961), 226.



ሴቶች ልጆች ለመሆን ተጋብዘናል። ይህ ግንኙነት ሰብአውነትን የሚደመስስ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ጋር፣ "በእኔና-አንተ" ዐይነት የቅርበት ግንኙነት ላይ የተመሠረተና ኅብረትን የሚያረጋግጥ ነው። መንፈስ ቅዱስ አማኞችን በእግዚአብሔር መኖርና (መገኘት) እንዲሁም ኀይል ይሞላቸዋል። የውስጥ መለወጥ እንዲያገኙና አዲስ ፍጥረት እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ይህ ሁሉ የሚሆነው በእምነት በተሳሰሩ ማኅበረሰቦች ውስጥ እንጂ፣ በማይታዩ ምስጢራዊ መንፈሳዊ መሪዎች አይደለም። ሆኖም አንድ በሚያደርገውና በሚያስተሳስረው መንፈስ ነው።

የሱፊ መንፈሳዊ መስመር የሙስሊም ማኅበረሰብ አባላት ለሚሰማቸው መንፈሳዊ ፍላጐት መልስ ሰጥቶአል። የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት በመሲሑና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ይህ መንፈሳዊ ፍላጐት (ጥማት) በሰውየው ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው። ወንጌል የጠራን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንድናደርግ እንጂ ትርጉም የለሽ መንፈሳዊ ተመስጦ ውስጥ እንድንገባ አይደለም።

## አብርሃምና እምነት

ምንም እንኳን የሱፊዎች እምነት (መንገድ) ተከታዮችን ለተማልሉ ቅድስና ቢጋብዝም፣ ለሁሉም እስልምና ሰላት መግዛትንም አይቃወሙም፤ ማንኛውም ትክክለኛ የሱፊም ሆነ የኦርቶዶክስ ሺይትም ሆነ ሱኒ እስላም በሸሪአ እንደ ተደነገገው መተግበር አለበት። በ2000 በበልግ ላይ የእንግሊዝ ሙስሊም ተማሪዎች ማኅበር ላይ እንግዳ ተናጋሪ ሆኜ በተጠራሁበት ወቅት በአየሁት እውነት ተደንቄ ነበር። እነዚህ ሙስሊም ተማሪዎች ዓለማዊ በሆነና ጥድፊያ በነገሠበት ማኅበረሰብ ውስጥ ቢኖሩም እንኳ፣ የሰላት ሰዓታቸው በምንም መልኩ እንዲሰረቅባቸው አይፈቅዱም ነበር።

በአንድ ምሽት ከተማሪዎቹ ጋር በነበረኝ ውይይት የውይይታችን ርእሰ ጉዳይ የነበረው አብርሃም ነበር። የመልእክቱም ፍሬ ሐሳብ፣ "አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት" (ዘፍጥረት 15፥6) የሚለው ነበር። ለአብርሃም በእግዚአብሔር ማመን አዳጋች ነበር። አብርሃም በአንዳንድ የእምነት ፈተናዎች ደክሞ ነበር፤ መንገድ ስቶ በኀጢአት ወድቋል። ይህም ሆኖ በእምነት መሆንን መርጦአል። በማመኑም እግዚአብሔር ታማኝ ጓደኛው እንደ ሆነ ተምሮአል። የአብርሃም በእምነት መጓዝ አስደናቂ ጸጋን በሕይወቱ ከፍቶለታል። እርሱ የተጓዘበት እምነት ቀድሞ የተገለጠ እኛ ዛሬ በመሲሑ በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት የተጠራንበት ጸጋና እምነት ነው። የዳንነው

በጸጋው ነው፤ እምነት እንኳ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ የኀጢአታችንን ይቅርታ ያገኘነውና እግዚአብሔር የሚወደን የሰማይ አባታችን መሆኑን ያወቅነው በጸጋው ነው:: በራሳችን ይህንን ሞገስ ማግኘት አንችልም:: ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው::

የሙስሊም ጓደኛዬ አብርሃም ዛሬ የሚገኙት ሙስሊሞች በግንባራቸው ወደ መሬት ተደፍተው እንደሚሰግዱት ይሰግድ እንደ ነበር እግዚአብሔርንም ያህዌ ብሎ ሳይሆን አላህ በማለት በእውነተኛ ስሙ ይጠራው እንደ ነበር ተናገረ:: አብርሃምና ኢስማኤል በካዕባ ያሉትን ጣዖታት አስወግደው የእስልምናን እምነት መሥርተዋል:: የእግዚአብሔርን ቤት በካዕባ በማደስ እግዚአብሔርን በትክክለኛ መልኩ (መንገድ) አምልከዋል:: ጓደኛዬ ብቸኛ የጸሎት መንገድ የሆነውን በግምባር ወደ መሬት መደፋትን አብርሃምን እንደ ምሳሌ ይከተሉ ዘንድ ውይይቱን ያደምጡ የነበሩ ክርስቲያኖች ሁሉ እንዲያደርጉት ጥሪ አቀረበ:: እግዚአብሔርንም በእውነተኛ ስሙ አላህ ብለው እንዲጠሩት ጠየቀ:: አብርሃም የእምነት አባት የሆነው ፊቱን ወደ ካዕባ በመመለስ በግንባሩ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ወደቀ በማወቅ ማንም ሰው በጸሎት ፊቱን ወደ ካዕባ፣ ወደ እግዚአብሔር በማዞር መጸለይ አለበት::

የአብርሃም የእምነት አባትነት ተልእኮው ብርቱ ውይይት የሚጠይቅ መሆኑ ግልጽ ነው:: እምነት ምንድን ነው? ለእግዚአብሔር መገዛት ምንድን ነው? እውነተኛ አምልኮ ምንድን ነው? ለእግዚአብሔር የምንሠራውስ ሥራ ነው? ትክክለኛ የአምልኮ ተግባራት የእግዚአብሔርን ምሕረት ያስገኙልናል ወይ? ወይስ እግዚአብሔር ላደረገልን የምንሰጠው ክብርና በደስታ የእግዚአብሔርን ጸጋ ማክበራችን ነው?

## የአምልኮ ትርጒም

በሶማሊያ እኖር በነበረበት ጊዜ በመሲሑ በሚያምኑ አማኞች ኅብረት ላይ የአምልኮን ትርጒም አስመልክቶ ተከታታይ ውይይት ተካሂዶ ነበር:: የአሜሪካ ሜኖናይት ሚስዮናውያንና የሶማሊያ ክርስቲያኖች በጋራ በመሲሑ ኢየሱስ የተገለጠውን አምልኮ ላይ ጥናት አድርገዋል:: አንዳንድ ጊዜ ሙስሊሞች የሚሰጡት አስተያየት ክርስቲያኖች ኅብረት ለማድረግ ሲሰበሰቡ መዝሙራቸው ግብዣ ያለባቸው ያስመስላቸዋል በማለት ነው:: ይህ አስተያየት እውነት ነው:: በመሲሑ ለተሰጠን ጸጋ እግዚአብሔርን በግብዣ እያከበርነው ነው፤ ትኩረት የሰጠነው የክርስቲያን አምልኮ ዋና ፍሬ ነገርና በሱማሊያ ሙስሊሞች ዐውድ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብና በአማኞች ኅብረት ላይ ትርጒም



ያለው ተግባቦት ሊፈጥር የሚችል ተምሳሌት ላይ ነበር:: ከውይይቱ የተገኙት አስተያየቶች የሚከተሉት ናቸው::

የእሑዱ አምልኮ በሱማሊያ እየተፈጠረች ላለችው ትንሽ ጉባኤ በእሑድ ከሚያመልከው የዓለም ዐቀፍ ጉባኤ ጋር የሚያገናኛት ነው:: ለአምልኮ የተለየ ስፍራ መኖሩ አስፈላጊ ነው:: ይህ ስፍራ የእግዚአብሔርን ቅድስና እንድናስብ ያደርገናል:: ወደ ውስጥም ስንገባ ቅዱሱን ለመገናኘት እንደምንገባ በመቍጠር ጫማችንን ማውለቅ አለብን:: ጉባኤውን የሚመሩት መሪዎች አለባበሳቸው እንደ ካህናት ቢሆን መልካም ነው:: እንደ ኢማሞች በማኅበረሰቡ መኻል መሪነታቸውን የሚያመለክት አለባበስ ቢለብሱ ጥሩ ነው:: በመደበኛ አምልኮ ጊዜ የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ እንዲሁም የጌታችንን "አባታችን ሆይ ጸሎት" ማድረስ አስፈላጊ ነው:: የአባታችንን ጸሎት እንደ ምስጢራዊ ጸሎት ምልክት መድገም ቢቻል መልካም ነው:: መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ በስብሰባ ወቅት ሁሉ ማንበብ ያስፈልጋል::

ጥምቀት ሰውየው ወደ አዲስ የቃል ኪዳን ማኅበረሰብ መግባቱ ምስክር ነው:: የጌታ ራት (ቅዱስ ቍርባን) መሲሑ የእግዚአብሔር በግ እኛን ለመቤዠት የከፈለውን መሥዋዕትነት ለማክበር በመደበኛ ሁኔታ መወሰድ (መከበር) አለበት:: ሁል ጊዜ የሚደረግ የኀጢአት ኑዛዜ፣ በአምልኮ ጊዜ ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል:: መሲሑ የሐዋርያትን እግር የማጠቡን ምሳሌ በመከተል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግር መታጠብ ሥርዐት ማበጀት ያስፈልጋል:: እግር ማጠብ ከሱማሌ ባህል ተጻራሪ ነው:: ሆኖም መሲሑ የመጣው ኩሩዎችን አገልጋይ ሊያደርግ መሆኑ መታወስ አለበት::

አማኞች በግንባራቸው ወደ ምድር መደፋት ሳይሆን መቆም ነው ያለባቸው:: ባሮች በግንባራቸው ይደፋሉ:: በመሲሑ የሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ሴቶችና ወንዶች ልጆች ሆነዋል:: ስለዚህ ልጆች ከአባታቸው ጋር ቆመው ነው የሚያወሩት እንጂ በግንባራቸው ተደፍተው አይደለም:: በተጨማሪም በግንባር መደፋት በእስልምና ወደ ከአባ አቅጣጫ መዞርን ይፈልጋል:: ሆኖም መሲሑ ጌታችን ተነሥቶአል:: በመንፈሱ በመካከላችን እንዲሁም ከእኛ ጋር ስለሆነ፣ አቅጣጫን በመወሰን በግንባር የሚወድቅበት ምንም ዐይነት አቅጣጫ አይኖርም:: ክርስቲያኖች ጌታቸውን ፊት ለፊት መገናኘት በመቆም መጸለይን እንደ ምልክት አድርገው መጠቀም አለባቸው:: ሥርዐተ አምልኮ በሚካሄድበት ጊዜ ሁሉ ለእግዚአብሔር ዝማሬ ማኅሌት መቅረብ አለበት:: የሶማሌ አጫጭር ዝማሬዎችና የአካባቢው ሙዚቃና የአነጋገር ዘይቤ ቢጻፍ አምልኮውን ያበለጽገዋል::

## እውነትና መንፈስ

የዚህ ዐይነት ውይይቶች በተለያዩ ጊዜያት ይካሄዱ ነበር። ሆኖም የአምልኮን ትርጉም ለማጥናት ለብዙ ወራት በየቅዳሜው አንድ ቡድን ይሰበሰብ ነበር። ቡድኑ ኢየሱስ በሲካር በያዕቆብ ጉድጓድ አጠገብ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ያደረገውን ንግግር ያጠኑ ነበር (ዮሐንስ 4፥1-26)። ሴቲቱ ለአምልኮ ትክክለኛ ስፍራና መንገድ መኖሩን በማሰብ አይሁዶች በኢየሩሳሌም ሰገዱ/አመለኩ እኛ ሳምራውያን ደግሞ በተራራ አመለክን (ሰገድን) አለች። ኢየሱስ መለሰ:—

> አንቺ ሴት እመኚኝ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል። እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን። ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል። አብ ሊሰግዱለት እንደዚህ ያሉትን ይሻልና እግዚአብሔር መንፈስ ነው። የሚሰግዱለትም በመንፈስ እና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል። (ዮሐንስ 4፥21-24)።

ኢየሱስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ባደረገው ንግግር፣ "መዳን ከአይሁድ" እንደ ሆነ አስረግጦ ተናግሯል።

በእርግጥ ወንጌልና ቤተ ክርስቲያን ከእስራኤል ታሪክና ቅዱሳት መጻሕፍት ሲነጠሉ ትርጉመቢስ ይሆናሉ። ቤተ ክርስቲያን የቆመችው በመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣናዊ ቃል ነው። ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳኑ የቃል ኪዳኑ ሕዝብ ቀጣይ ነው። መሲሑ የቀድሞውን ሕግ ፈጸመው እንጂ አልሻረውም። ቤተ ክርስቲያን ተወልዳ ያደገችው በመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ሲሆን፣ ቃላቱም መተርጐምና መተግበር ያለበት በቤተ ክርስቲያን ነው። መጽሐፍ ቅዱስና ቤተ ክርስቲያን ተደጋጋፊዎች ናቸው።

በዚያ በሱማሊያ ስብሰባ ወቅት፣ "በመንፈስና በእውነት" የሚለውን አምልኮ ትርጉም አጥብቀን አስበንበታል። ስፍራን በተመለከተ አምልኮተ እግዚአብሔር ለማካሄድ፣ የሰማርያ ተራራም ሆነ የአይሁዶች መቅደስ አስፈላጊ አይደለም። ኢየሱስ ፊታችሁን ወደ ካዕባም መልሱ አላለም። የመልካም አምልኮ መሠረቱ በእውነትና በመንፈስ ማምለክ ነው። የተሰወረ ኀጢአት ሊኖር አይገባም። አምልኮ የላቀ ታማኝነትን ይጠይቃል። ስለዚህ እውነተኛ አምልኮ የኀጢአት ኑዛዜን ያካትታል። መንፈስ መገኘትንና ኅብረትን ያመለክታል። እኛ እግዚአብሔርን እናውቀዋለን፤ እግዚአብሔርንም እኛን ያውቀናል፤ በአምልኮም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን እናደርጋለን።



ሳምራዊቷ ሴት ይህ ሁሉ የሚሆነው፣ "መሲሑ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል" በለችው መሠረት ነው። ኢየሱስም፣ "የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ" ብሎ አስደነቃት (ዮሐንስ 4፥25-26)።

## ሁለት ጸሎቶች

ይህንን ክፍል የምንደመድመው በሁለቱ ጸሎቶች ነው። የእስልምና ፋትያ፣ ታማኝ ሙስሊሞች በቀን ዐሥራ ሰባት ጊዜ የሚደግሙት እንዲሁም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ባስተማረው፣ "በአባታችን ጸሎት" ነው። እነዚህ ሁለት ጸሎቶች ጠንካራ የአምልኮ ማዕከል ናቸው (በእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት የሚገኝ ሰላም እንዲሁም በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ የአምልኮ ልክ ነው-- እግዚአብሔርን እንደ ሰማይ አባት በማወቅ የሚገኝ ደስታ)።

### ፋትያ

በአላህ ስም በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ በኾነው።
ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለሆነው፤
እጅግ በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ፤
የፍርድ ቀን ባለቤት ለኾነው።
አንተን ብቻ እንገዛለን አንተንም ብቻ ርዳታህን እንለምናለን።
ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።
የነዚያን በነርሱ ላይ በጐ የዋልክላቸውን በነሱ ላይ
ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ
(ምራን በሉ)። (አል-ፋቲሐህ 1፥17)

### የአባቶቻችን ጸሎት

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንደሁ በምድር ትሁን የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን። እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን። ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተናም አታግባን መንግሥት ያንተናትና ኀይልም ክብርም ለዘላለሙ አሜን።

(ማቴዎስ 6፥6-13)

*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ*

ማቴዎስ 6፥9-13

*የቁርአን ምንባብ*

ሱራ 1፥1-7

## <u>የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. በእስልምና የሰላት ትርጉሙም ነው? በክርስቲያኑ ልምምድ የአምልኮ ትርጉም ምንድን ነው? በሥርዐታዊ አምልኮ ውስጥ ያለው ዋጋ ምንድን ነው?
2. ፋቲያን ከአባታችን ጸሎት ጋር ያነጻጽሩ፡፡ ክርስቲያኖች ፋቲያን መጸለይ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ሙስሊሞች የአባታችንን ጸሎት መጸለይ አይችሉም፡፡ በእነዚህ ነጥቦች ላይ ሐሳብ ይስጡ፡፡
3. በሱፊዎችና በክርስቲያኖች መካከል ስለ፣ "አማላጅ" የሚደረገውን ውይይት ልብ ይበሉ፡፡ የዕብራውያን መጽሐፍ መሲሑን እንደ ካህንና እንደ አማላጅ የሚያቀርበው (ዮሐንስዕብራውያን 7፥1-8፥6፤ ሱራ 20፥109፤ ሱራ 6፥51:70)፣ ሱፊዎች አማላጅ የመፈለግ ጉዳይ ትርጉም በሚሰጥና በእነርሱም መረዳት ነው፡፡ በዚህ ሐሳብ ላይ አስተያየትዎን ይስጡ፡፡
4. አራት የተለያየ የአምልኮ ልምምድ ያላቸውን ውስጣዊ ትርጉም ይተቹ:— (1) በቀን ውስጥ በሚሰገዱ ሰላቶች ውስጥ የሚካሄዱ ዐሥራ ሰባት ረካዎች (ጉንበስ ቀና ማለት)፡፡ (2) በሱፊ ስብሰባዎች ላይ የእግዚአሔርንና የሥርዐቱ መሥራች ቅዱስ ስሞች በተደጋጋሚ መጥራት፡፡ (3) የእሁድ አምልኮ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡፡ (4) የእሑድ አምልኮ ባህላዊ ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን
5. እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ማምለክ ማለት ምን ማለት ነው (ዮሐንስ 4፥21-25)?
6. የሱፊዎች ፍለጋ:— በሙስሊሙ ልምምድ ወደ ሁልአቀፍነት በመዋጥ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ነው፡፡ የመሲሑ ሕይወትና አገልግሎት እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ሥራና መገኘት ሰው እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ስጦታን መስጠት ነው፡፡ እነዚህን ሁለት የተለያዩ ዐይነት መንፈሳዊነት ልብ በል፡፡ በሙስሊሞች መኻል ያለው የሱፊ እንቅስቃሴ ሙስሊሞች የክርስቲያኑን ወንጌል መረዳት እንዲችሉ ድልድይ መሆን ይችል ይሆን? በዚህ ሐሳብ ላይ አስተያየት ይስጡበት፡፡





# ምድራዊ ተልእኮ
# ኡማ—ቤተ ክርስቲያን

በምድር ላይ ከሚኖረው ሕዝብ መካከል ግማሹ ሙስሊም አልያም ክርስቲያን ነው፡፡ ይህ እውነት የሁለቱም ወገን ያሉት ዓለም ዐቀፍ ማኅበረሰቦች ማለትም የሙስሊሙ ኡማና ቤተ ክርስቲያን እምነታቸውን ለማስፋፋት ያላቸውን ትልቅ ትጋት በጉልሕ የሚያሳይ ነው፡፡

ሚስዮናዊ በሆነው እንቅስቃሴ ውስጥ፣ ኡማውና ቤተ ክርስቲያን እርስ በርስ እየተፎካከሩ ናቸው፡፡ በመቅድሙ ላይ ለማብራራት እንደ ሞከርሁት፣ ከጥቂት ዓመታት በፊት በድሩ ዲ. ቀትራጋና እኔ በተዋስኦ (በውይይት) መልክ ያዘጋጀነው መጽሐፍ፣ በድሩ የሙስሊሙን ማኅበረሰብ እኔ ደግሞ የክርስቲያኖችን እማኝነት በመወከል የቀረበ ውይይት ነበር፡፡

በድሩ፣ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ንግግር ለማድረግ በተዘዋወረባቸው ዓለም ዐቀፋዊ ጉዞዎች ላይ ሁሉ፣ ይህ እኔና እርሱ የጻፍነውን መጽሐፍ ወደ ላይ ከፍ በማድረግ፣ ለጉባኤው ታዳሚ የሚከተለውን ቁም ነገር እንደ ነገራቸው አጫውቶኛል:—

> ዴቪድ ሼንክ በሉቲኒያ ክርስቲያን ዩኒቨርስቲ ሲያቋቁም ነው የቆየው፡፡ እኔ ደግሞ በዩጋንዳ ሙስሊም ዩኒቨርስቲ ሳቋቁም ቆይቻለሁ፡፡ እኔ ለእስልምና እምነት ምስክር በመሆኔ በአንጻሩ ደግሞ እርሱ ለቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የተሰጠ ሰው በመሆኑ ሁለታችንም ፉክክር ላይ እንዳለን እናውቃለን፡፡ ዳሩ ግን እኔና ዴቪድ ጥሩ ባልንጀሮች ነን፡፡ እርስ በእርስ ያለን ቀረቤታ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ሁሉ ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንኙነት ተምሳሌት መሆን የሚችል ነው፡፡

## ሚስዮናዊ የሆኑ ማኅበረሰቦች

የሚያሳዝነው ግን አብዛኛውን ጊዜ ሚስዮናዊ በሆኑት በእነዚህ ሁለት ማኅበረሰቦች መካከል ያለው ግንኙነት በድሩ እንዳስቀመጠው የመከባበርና ወንድማማችነት የሰፈነበት አይደለም፡፡ ዛሬ በእነዚህ ማኅበረሰቦች ላይ ለተጋረጠው የግንኙነት መሰናክል እንዲሁም ዓለም ዐቀፉ ሚስዮናዊ

እንቅስቃሴ በጥንታዊው የክርስቲያንና የሙስሊም ታሪካዊ እንቅስቃሴ ላይ ዘልቆ የተመሠረተ ነው።

እስልምና እንቅስቃሴውን በጀመረበት በአንድ ክፍለ ዘመን ውስጥ፣ ግማሽ የሚሆነው የክርስቲያኑ ዓለም በእስልምና ሃይማኖት አገዛዝ ሥር ወድቋል። ሙስሊሞች፣ ቀደምት የሆነው ይህ የሙስሊሞች ድል የተቀረው የክርስቲያን ክፍል በአጠቃላይ ሙስሊም እንደሚሆን የሚያመለክት ነው የሚል አቋም አላቸው።

## የመስፋፋት አቅጣጫዎች

ሰዎች ሙስሊም እንዲሆኑ የማያቋርጥ ግፊት ካለባቸው አካባቢዎች በስተቀር፣ ክርስቲያኖች ወደ እስልምና የተቀየሩበት ዓለም ዐቀፍ እንቅስቃሴ የለም። ግለሰቦች ወደ እስልምና ሃይማኖት የሚለወጡበት ሁኔታ ቢኖርም እንኳ፣ ከክርስትና ወደ እስልምና የሚደረግ መጠነ ሰፊ ለውጥ እየተካሄደ ያለው፣ ሙስሊሞች የፖለቲካ የበላይነት ባገኙባቸው አካባቢዎች ብቻ ነው። አስቀድሞ እንዳስተዋልነው በእስልምና አገዛዝ ሥር ጥበቃ የሚደረግላቸው ክርስቲያኖች (ዚሚ) ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ያለው ስምምነት ክርስቲያኖች ሙስሊም እንዲሆኑ ጫና የሚያደርግና እስልምናን እንዲቀበሉ የሚገፋፋ ነው። በእስልምና አገዛዝ ሥር ባሉ ክልሎች የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን የአባሎቿ ቍጥር ቀስ በቀስ ይመናመናል። ለዚህ ዋናው ምክንያት፣ እነዚህ ክርስቲያኖች በተለያየ ምክንያት እስልምናን እንዲቀበሉ ጫና ስለሚደረግባቸውና እስልምናን በግድም ሆነ በውድ ስለሚቀበሉ ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ሁሉም የእስልምና ዕድገት በፖለቲካ ሥልጣን (ኀይል) የተመሠረተ ነው ማለት ግን አይደለም። በቅርብ ዓመታት በአሜሪካን አገር በሺዎች የሚቈጠሩ ክርስቲያናዊ መሠረት ያላቸው አፍሪካ-አሜሪካውያን ከክርስትና ወደ እስልምና ሃይማኖት ተቀይረዋል። ለዚህ እንቅስቃሴ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረገው፣ በአሜሪካ የታየውና እየታየ ያለው የዘረኝነት እንቅስቃሴ ነው። በእርግጥ የኡማ (የሙስሊሙ ማኅበረሰብ) ተልእኮ ለክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ብቻ አይደለም። ሙስሊሞች ሃይማኖታቸውን የሚሰብኩት ለየትኛውም ሕዝብና በማንኛውም ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ላሉ ሰዎች ነው። ሙስሊም ነጋዴዎችና የሃይማኖቱ ሰባኪዎች እስልምናን፣ ክርስቲያን ወዳልሆነው ወደ እስያና አፍሪካ በማሠራጨት ረገድ ውጤታማ የሆኑት የፖለቲካ ኀይል በሌለበት ሁኔታ ነው።



ዕድሉን ባገኙባቸው ሁኔታዎች ሁሉ ግን፣ ሙስሊሞች የእስልምናውን ማኅበረሰብ (ኡማ) ተልእኮ ከዳር ለማድረስ የፖለቲካን ሥልጣን መሻታቸው አልቀረም። ይህም ዐልፎ ዐልፎ ወደ ጂሃዳዊ (ቅዱስ የሃይማኖት ጦርነት) ወደ ሆነ ወታደራዊ መስፋፋት (ዳር አል-ኢስላም) ሲወስዳቸው ታይቶአል። በዐሥራ ስምንተኛውና በዐሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የተካሄደው የምዕራብ አፍሪካው የጂሃድ እንቅስቃሴ ወታደራዊ ኀይልና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ሰፊ በሆነው ከሰሐራ በታች በሚገኘው ምዕራብ አፍሪካ ክልል ተስፋፍቶአል[1]። በእነዚህ አካባቢዎች በቅርቡ ቤተ ክርስቲያንም ሰፊ ዕድገት አሳይታለች። ለምሳሌ በሰባተኛውና በስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሙስሊሞች ሰሜን አፍሪካን ከተቈጣጠሩ በኋላ በ1975 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ የሙስሊሙና የክርስቲያኑ ቍጥር እኩል ሆኖአል። ከ25 ዓመት በኋላ ግን ከሙስሊሞች ቍጥር በላይ ሃምሣ አምስት ሚሊዮን ተጨማሪ ክርስቲያኖች ነበሩ (380 ሚሊዮን አፍሪካውያን የሆኑ ክርስቲያኖችና 325 ሚሊዮን አፍሪካዊ ሙስሊሞች)። በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ በአፍሪካ የሚገኘው የክርስቲያኖች ዓመታዊ ዕድገት 10.75 ሚሊዮን ሲሆን፣ የእስላሙ ማኅበረሰብ ደግሞ 8.25 ሚሊዮን ነበር[2]። የአፍሪካ ልምድ ለሙስሊሙና ለክርስቲያኑ እምነት መስፋፋት ዓለም ዐቀፍ ተምሳሌት ነው።

በዓለም ላይ የክርስቲያኖች ቍጥር የሙስሊሞችን ቍጥር በሁለት ዕጥፍ ይበልጣል። በ1900 ዓ.ም 200 ሚሊዮን ሙስሊሞች እንዲሁም 558 ሚሊዮን ክርስቲያኖች ነበሩ። በዚህን ወቅት ክርስትና ብዙ ተከታዮችን አግኝቶአል። የሙስሊሙም ኅብረተሰብ በከፍተኛ ፍጥነት አድጓል[3]። ሆኖም ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዕድገት ትልቅ ምክንያት የሆነው፣ በርካቶች የእስልምናን ሃይማኖት መቀበላቸው ሳይሆን፣ ሙስሊሞች በርካታ ልጆችን መውለዳቸው ነው። አንዳንድ ሙስሊሞች ዐማጺ ቡድኖችን በማደራጀትና ወታደራዊ ኀይልን በመጠቀም የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ለማደናቀፍ ከፍተኛ የሆነ ሙከራ ያደርጋሉ። በደቡብ ሱዳን እንደሚደረገው ዐይነት ማለት ነው።

---

[1] John Alembillah Azumah, *The Legacy of Arab-Islam in Africa* (Oxford: Oneworld Publications, 2001), 63-69.

[2] Patrick Johnstone and Jason Mandryk, *Operation World: When we Pray God Works* (Waynesboro, Ga.: Paternoster Publishing, 2001), 18-21.

[3] David B. Barrett and Todd M. Johnson, "Annual Statistical Table on global Mision," *International Bulletin* 25:1 (January 2002), 25.

## የሙስሊሞች ተልእኮ

የሙስሊሞች ተልእኮ ሁለት ገጽ ያለው ነው። ይኸውም ዳዋ እና ዳዋላ ናቸው። ዳዋ ምስክርነት እና ጉብኝት ነው። ይህ የሙስሊሞች ተልእኮ የሚገለጠው በቀን 5 ጊዜ በዓለም ላይ ያሉ በመቶ ሺዎች በሚቈጠሩ የጸሎት ማማዎች የጸሎት ጥሪ ሲደረግ:—

> አላህ እጅግ ታላቅ ነው።
> ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እኔ ምስክርነቴን እሰጣለሁ።
> መሐመድ የአላህ መልእክተኛ እንደ ሆኑ ምስክርነቴን እሰጣለሁ።
> ወደ ጸሎት ኑ።
> መልካም ወደ ሆነው ኑ።
> ከእንቅልፍ ጸሎት የተሻለ ነገር ነው።
> ወደ ተሻለ ተግባር ኑ።
> አላህ እጅግ ታላቅ ነው። አላህ እጅግ ታላቅ ነው።
> ከአላህ ሌላ አምላክ የለም[4]።

ይላሉ። በዚህ ተልእኮ ላይ ግዳጅ የለም። በግልጽና በትኅትና የሚደረግ ጥሪ ነው። ይህንን ምስክርነትና ጥሪ የሚሰማ በመምጣት ወይም በሩቅ ለመቆየት መወሰን አለበት።

ዳዋላ ሁለተኛው የእስላምና የተልእኮ ክፍል (ገጽታ) ነው። ይህ የኡማ (የሙስሊም ማኅበረሰብ) ፖለቲካዊ ዕገዛ ግዛታዊ ተልእኮ ነው። በምዕራፍ ዘጠኝ ይህ የእስልምና ፖለቲካዊ ተልእኮ ገጽታ ተብራርቶአል። እርሱም ዳር-አል-ኢስላምን (የእስልምና ግዛት) በአስፈላጊ ቦታና ስፍራ ለመመሥረት የሚደረግ ትጋት ነው። በሐሳብ ደረጃ ዳር አል-ኢስላም ሕዝብ ወደ እስልምና እንዲቀላቀል የሚያስገድድ አይደለም። ዳሩ ግን ፖለቲካዊ እስልምና የኡማው አንድነት መጠበቁን የሚያረጋግጥ ነው። ዳዋላ የፖለቲካ ሥልጣንን በመጠቀም ሁሉን የሕይወት ክልል በእስልምና ሥልጣን ሥር ለማስገዛት መትጋት ነው።

የዳዋላንም ሆነ የዳዋን እስላማዊ ተልእኮ ገጽታ ታሪካዊ እውነታዎች ተፈታትነውታል። ንጹሕ እስልምናን ለማራመድ የሚፈልጉ እንደ አፍጋኒስታኑ ታሊባን ያሉ እንቅስቃሴዎች በብዙ ዓለም እንዳይወደዱ አድርገዋቸዋል። ቤተክርስቲያን ለማደግ ስፍራ (ክፍተት) ስታገኝ ብዙ ጊዜ ታድጋለች። እስልምና የሚገዛባቸው ሰፊ ክልሎች በድኽነትና በመሃይምነት የተወረሩ

---

[4] Kenneth Cragg, *The Call of Minaret* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1985), 26.



ናቸው። (በአንዳንድ የላቲን አሜሪካና በአፍሪካ አካባቢ የሚኖሩ በብዙ መቶ ሚሊዮን የሚቈጠሩ ክርስቲያኖች በድኽነት እንደሚኖሩ የሚካድ አይደለም)።

ኡማው (የእስልምና ማኅበረሰብ) ዐላማውን ውጤታማ በማድረግ ለሕዝቦች መመሰከር ተልእኮው ቢሆንም፣ የተፈለገውን ያህል ግን ውጤታማ አይደለም። ሁኔታዎችን ለማስተካከል (ለመለወጥ) መንገድ መፈለግ አለበት። በእርግጥ ለሙስሊሙ ኅብረተሰብ የተልእኮውን እንድርድሮሽ መልሶ መያዣው መንገድ በጣም ቀርቦአል። ሙስሊም መልእክተኞች ዕቅድ ተስፋ ያለው ነው። በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ ሕዝቦች በዘይት እጅግ ብዙ ትርፍ እያገኙ ነው። ዓለም ዐቀፍ የሆነውንም የእስልምና ተልእኮ ተያይዘውታል።

የእስልምና ባህል ለነበራቸው ለቀድሞ የሶቭየት ኅብረት አገሮች በአሁኑ ጊዜ ልዩ ትኩረት ሰጥተዋል። በቀድሞ ኮሚኒስት ማኅበረሰብ ፍርስራሽ ውስጥ የእስልምና መልእክተኞች በትውፊት ሙስሊም የነበረውን ሕዝብ እስልምና ለሚያቀርበው አማራጭ እንዲነሣሣ እያደረጉ ናቸው። በእነዚህ ክልሎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያንና ኡማው ይህንኑ ክፍል በብርቱ ትጋት ወደ ራሳቸው እየሳቡ ይገኛሉ። በእነዚህ ቀድሞ የሙስሊም ማኅበረሰብ በነበሩ አካባቢዎች የእስልምና መልእክተኞች የማይናቅ አዎንታዊ ምላሽ እያገኙ ነው።

ዓለም ዐቀፍ የሆነው ኡማ በመስፋፋት ላይ ይገኛል። ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን እንደ ጀመረ በዓለም ዙሪያ ያለው የሙስሊሞች ቍጥር በየዓመቱ በሃያ ሰባት ሚሊዮን ዕያደገ ነው[5]።

## የክርስቲያኖች ተልእኮ

ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣ ከአርባ ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱን በኩረብታ ላይ አገኛቸው። እንዲህም አላቸው:—

> መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። (ሐዋርያት ሥራ 1፥8)

እንዲሁም ታላቁን ተልእኮ ሰጣቸው። እንዲህ ሲል:—

---

[5] Johnstone and Mandryk, *Operation World*, 2.

> ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ:: እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው:: እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ (ማቴ 28+19-20)::

እነዚህ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው ትእዛዛትና መመሪያዎች ናቸው:: ኢየሱስ ይህን ትእዛዝና መመሪያ ከሰጠበት ማግሥት ጀምሮ፣ ቤተ ክርስቲያን ይህን ትእዛዝና ተልእኮ ከዳር ለማድረስ በሰፊው ተንቀሳቀሳለች:: ምዕራፍ አንድ ላይ ለማየት እንደ ሞከርነው፣ ከቈስጠንጢኖስ ዘመን በኋላ፣ በምዕራቡ ዓለም የምትገኘዋ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች መንግሥት፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወኪሎች ነን የሚለውን ጉዳይ ታሳቢ በማድረጋቸው፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ እንዴት ይመሠረታል የሚለውን ጉዳይ አስመልክቶ በፖለቲካውም ሆነ በሃይማኖቱ ረገድ በርካታ ለውጦች ተካሂደዋል:: ይህም "የክርስቲያን መንግሥት" (Christendom) የሚባለው አስተሳሰብ እንዲዳብር ምክንያት ሆኖአል:: ይህ ሙስሊሞች ዳር አል-ኢስላም (በእስልምና አገዛዝ ሥር የሆኑ ግዛቶች) ከሚሉት ጋር ተመሳሳይ ነው::

ዳሩ ግን በምዕራብ በሚገኙት ክርስቲያኖች ዘንድ የነበረው ይህ ታላቅ ተልእኮና ራእይ ቀስ በቀስ እየተዳከመ መጥቶአል:: የአውሮፓ ክርስቲያኖች ይህን ራእይ በዓለም ሁሉ ከማቀጣጠል ይልቅ በእርስ በርስ ሽኩቻ ተወጥረው ይገኛሉ:: የቤተ ክርስቲያንን ምድራዊ ተልእኮ ክፉኛ ከተፈታተኑት ጉዳዮች መካል ከእስልምናው ወገን የሚቀርቡት ፈተናዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ እንደ ማርክሲዝም ያሉ ዓለማዊ ንቅናቄዎች ጭምር ናቸው:: እነዚህ ተግዳሮቶች በራሱ በወንጌልም ላይ ቀጥተኛ ተቃውሞ ሰንዝረዋል:: በማርክሲስት ማኅበረሰብ ውስጥ ክርስትና በከፍተኛ ታቃውሞ ውስጥ ስለወደቀ ብዙ ክርስቲያኖች ተሰደዋል፤ የሕይወት ዋጋም ከፍለዋል:: ክርስቲያናዊ በሆነው ምድር የናዚ ጀርመኖች የአይሁድን ዘር ለማጥፋት ያደረጉትን የዘር ጭፍጨፋ ከቶውንም የሚዘነጋ አይደለም:: ይህ ዐይነቱ እኩይ ተግባር በክርስቲያኑ ማኅበረሰብና ክርስቲያናዊ በሆነው ምዕራባዊ ሥልጣኔ ውስጥ እንዴት ሊከሠት ቻለ? ይህ ጉዳይ በምዕራብ የሚገኙትን የክርስቲያኖችን ራእይ ክፉኛ ያጨለመ የታሪክ ክሥተት ነው::

ሆኖም ይህ በምዕራብ አውሮፓ መታወክ የገጠመው የክርስቲያኖች እንቅስቃሴ፣ በብዙ የዓለም ክፍል የሚገኙትን ቤተ ክርስቲያን የሚወክል



አይደለም:: በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ሲታይ፣ ቤተ ክርስቲያን አስደናቂ የሆነ ተሐድሶና ዕድገት ተጐናጽፋለች:: ይህ ዐይነቱም እምነትና ተስፋ ዛሬም አለ:: ከኮሚኒዝም ውድቀት በኋላ በምሥራቅ አውሮፓና በቀድሞዋ ሶቭየት ኅብረት የተከሠተው አስደናቂ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት፣ ከየትኛውም የታሪክ ጊዜ ጋር የሚወዳደር አይደለም:: በቻይና የምትገኙትም አብያተ ክርስቲያናት ከዚህ ቀደም ታይቶም ሆነ ተሰምቶ የማይታወቅ ድል እየተቀዳጁ ነው:: በክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ በቻይና አንድ መቶ ሚሊዮን የሚደርሱ ክርስቲያኖች ነበሩ:: በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ግን በየዓመቱ ሰባት ሚሊዮን አዳዲስ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን ይቀላቀላሉ[6]::

በየዓመቱ በዐሥር ሺዎች የሚቈጠሩ የወንጌል መልእክተኞች በዓለም ዙሪያ የወንጌሉን ሥራ ይሠራሉ:: ባለጠጋ ናቸው ከሚባሉት ከምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም ላይ ካሉ ከየትኛውም አገር የወንጌል መልእክተኞች በተለያየ ስፍራ ወንጌልን እንዲሰብኩ ወደ ተለያዩ አገሮች ይላካሉ:: በሃያ አንደኛው ሞቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ፣ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ከዘጠና ስምንት ሺህ በላይ የሚሆኑ የወንጌል መልእክተኞች ከአገራቸው ውጪ የሚያገለግሉ ሲሆን፣ ከሁለት መቶ ሺህ በላይ የሚሆኑት ደግሞ በአገራቸው ውስጥ ባህል ዘለል የወንጌል መልእክተኛ በመሆኑ ከቀዬአቸው ርቀር ያገለግላሉ:: ኮርያ የወንጌል መልእክተኞችን በመላክ ግንባር ቀደሟ የዓለማችን አገር ሆናለች:: ዛሬ ኮርያ ዐሥራ አንድ ሺህ የወንጌል መልእክተኞች ወደ ተለያዩ የዓለማችን አገሮች በመሄድ የምሥራቹን ወንጌል በመስበክ ላይ ናቸው[7]::

## የታሪክ ግብ

ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች ሰዎች እስልምናን ወይም ወንጌልን እንዲቀበሉ ጥሪ የሚያቀርቡት ለምንድን ነው? የዚህ ንቅናቄ አራማጅ የሆኑ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች፤ መልእክተኞቻቸውን ወደ ተለያዩ የዓለማችን አገሮች የሚያሠማሩት ለምንድን ነው? በተለያየ አጋጣሚ ወደ ተለያዩ ስፍራዎች የሚሄዱ ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች እምነታቸውን ለሌሎች በመስበክ ሰዎች እስልምናን ወይም ወንጌልን እንዲቀበሉ ግብዣ የሚያቀርቡት ለምንድን ነው? ክርስቲያንም ሆኑ ሙስሊም ስደተኞች በምጻተኝነት በሚኖሩባቸው

---

[6] ዝኒ ከማሁ፤ 180::

[7] ዝኒ ከማሁ፤ 747:749::

አገሮች የሚገኙትን ጎረቤቶቻቸውን የእነርሱን ዱካ እንዲከተሉ የሚጋብዙበት ምክንያት ምንድን ነው?

በሙስሊሙ ማኅበረሰብም ሆነ በክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ያላቸው የዚህ ሚስዮናዊ ተልእኮና ራእይ መሠረቱ የታሪክ ዐላማና ግብ ምንድን ነው በሚለው ርእስ ጉዳይ ላይ ያላቸውን መረዳት መሠረት ያደረገ ነው:: የታሪክ ትርጉሙ ምንድን ነው? ሁለቱም ወገኖች ለዚህ ጥያቄ የሚሰጡት መልስ የተልእኮአቸውን ዐላማና ግብ ይወስነዋል:: ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች ለዚህ ጥያቄ የሚሰጡትን መልስ ወደ መመርመሩ እንዘለቅ::

## እስልምናና ታሪክ

በሙስሊሞች መረዳት ታሪክ ልክ እንደ ቅንፍ ሰብሰብ ነው:: በምዕራፍ 3 እንደ ተገለጸው ከጅምሩ አዳምና ሔዋን የተፈጠሩት በገነት እንጂ በምድር ለመኖር አልነበረም:: ነገር ግን አዳም በሰይጣን በመታለሉ ምክንያት እግዚአብሔር ወደ ምድር አባረረው:: እንደ ብዙ ሙስሊሞች እምነት ሰዎች በዚህች ምድር ያላቸው ቆይታ የፈተና ዘመን ነው[8]:: ይህ የፈተና ዘመን የሚጠናቀቀውም ታላቅ በሆነ ፍርድ ነው:: ከፍርዱም በኋላ በርካታ ሰዎች ዘላለማዊ ወደ ሆነው ገሃነመ እሳት ሲሄዱ ብዙዎች ደግሞ ወደ ገነት ይገባሉ:: የገነት ምጽአትና የሰብአውያን ታሪክ መጠናቀቂያ በሆነው ዘመን መካከል ላይ ያለን ሲሆን ከቀጣዩ ዘመን ደግሞ በገነት ወይም በገሃነም የሚጠናቀቅ የመጨረሻው ፍጻሜ ነው:: ስለዚህ ይህ የታሪክ ወቅት በሽግግር ላይ የምንገኝበትና በቅንፍ የሚመሰልበት ወቅት ነው:: ስለዚህ ይህ ዘመን በቅንፎቹ ዘመን መካከል የሚገኝ ታሪካዊ ወቅት ነው::

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ወደ ምድር ካባረራቸው በኋላ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ቤት ከሚገኝበት በካዕባ አካባቢ በአራፋት ሜዳ ላይ ይኖሩ ነበር:: በምድር ላይ በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ፣ እነርሱም ሆኑ ዘሮቻቸው እንደ እግዚአብሔር ከሊፋ (ጠባቂዎች) ሆነው የማገልገል ኀላፊነት ነበረባቸው:: የሰው ልጆች ኀላፊነት የሚሰማቸው አገልጋዮች እንዲሆኑ እግዚአብሔር በምሕረቱ መመሪያን ሰጥቶአል:: ይህም መመሪያ እስልምና ነው:: ይህ መመሪያ በነቢያት በኩል ሲመጣ አደም የመጀመሪያው ነቢይ ነበር:: ማንኛውም ሕዝብ የራሱ

[8] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 44.



የሆነ ነቢይ አለው ምናልባትም በሰብአውያን ታሪክ ውስጥ የታዩት አንድ መቶ ሃያ አራት ሺህ (124,000) የሚሆኑ የእግዚአብሔር ነቢያት ናቸው[9]::

ይህ የአምላክ ምሪት ባሕርይ ተለውጦ አያውቅም፤ ይኸውም እስልምና ነው:: ሰዎች ይህን ምሪት ረስተው ወይም ለመለወጥ ሙከራ አድርገው ይሆናል:: ነገር ግን ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም:: ምሪቱ ከሰማይ የተላከ ምሪት ስለሆነ ከታሪክ ሂደት የላቀ ነው:: ሊኩረጅም ሆነ ሊመሰል በፍጹም አይችልም፤ "በቅርጹ ከታሪካዊ ንባብ ጊዜያት ጋር ምንም ዐይነት ዝምድና የለውም:: ቃል በቃል ከሰማይ የወረደና አስቀድሞ በመለኮታዊ ሰሌዳ ላይ ተጽፎ የነበረ ነው"[10]::

እንግዲህ ይህ የማይመስልና የማይኩረጅ ባሕርዩ ነው ቁርአን ከዐረብኛ ቋንቋ ውጪ እንዳይተረጐም ያደረገው:: ባለፉት ዘመናት ብዙ ሕዝቦች ምሪቱ ከእግዚአብሔር ስለመላኩ ቸልተኛ ሆነው ነበር:: ቸል ከማለትም በላይ ረስተውት እንዲሁም ለመቀየር ፈልገው ነበር:: ሆኖም የሙስሊሙ ተልእኮ የመጨረሻ መገለጥ የሆነውን ቁርአንን ከማንኛውም ፈጠራ መጠበቅ ነው:: እያንዳንዱ ቃል በሰማይ ካለው ቅጅ ጋር አንድ ዐይነት የሆነ ፍጹም ግልባጭ ነው::

በዚህ ዐይነት በማያጠራጥር ሁኔታ መገልበጡን መረዳት ማለት የእስልምና መጽሐፍ ከታሪካዊ ክሥተቶች ጋር ዐቢይ ግንኙነት እንደሌላቸው ማጽናት ነው[11]:: ለምሳሌ አስቀድመን ለማየት እንደ ሞከርነው፣ ቁርአን መሲሑ አልተሰቀለም ካለ፣ በምንም ዐይነት መልኩ ይህን የሚቃረን ታሪካዊ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም:: በምንም ዐይነት መልኩ ታሪካዊ ክሥተቶች የቁርአንን ሥልጣንና ተአማኒነቱን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገቡ አይችሉም:: ታሪክም ሆነ የሰብአውያን ተሞክሮ ስለመጽሐፉ ይዘት መሠረት አልሆኑምና:: ራሱን ችሉ የሚቆመው ቁርአን ከሰው ልምምድ እጅግ የላቀ ነው::

ይህ መገለጥ ወደ ምድር ተልኳል የሚለው ግንዛቤ፣ ከታሪክና ከፍጥረት አንጻር በሰዎች ኀላፊነት ላይ እንዴት ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል? በታሪክ ትርጉም ላይስ ምን ተጽእኖ ይኖረዋል? የምናደርጋቸው ነገሮች እግዚአብሔርንም ሆነ

[9] ዝኒ ከማሁ፤ 64::

[10] Andrew Rippin, *Muslims: Their religious Beliefs and Practices* (New York: Routledge, 2001), 236.

[11] ዝኒ ከማሁ፤ 238-245::

መገለጡን የማይነኩ ከሆኑ፣ እኛ በታሪክ ውስጥ ያለን ድርሻም ሆነ ቀሎም ነገር ምን ምን ሊፈይድ ይችላል:: ስለዚህ በዚህ ረገድ ትልቅ ድርሻ ያለው እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ ምድር የላከው ምሪት ብቻ ነው:: ለዚህም ነው ሙስሊም በሆነው ማኅበረሰብ ውስጥ የእስልምና ሕግ ጥናት፣ ሌሎች የጥናት ዘርፎችን መተካቱ የማያስደንቀው[12]:: ሙስሊሞች የእግዚአብሔር ሕግ መልካም ዜና እንደ ሆነ እርግጠኛ ናቸው::

የታሪክ ሊቁ ዊልያም ካንትዌል ስሚዝ እንዳስተዋለው :—

> ለአንዴ እና ለመጨረሻ በግልጽ ቃል የአላህ እውነትና ፍትሕ ወደ ምድር ተልኳል:: መልእክቱን ያለምንም መዛነፍ ያደርስ፣ ይተረጉም፣ ይኖረው ዘንድ መልእክተኛ ተመርጧል:: በጥንቃቄ እና በታማኝነት መልእክቱን የሚጠብቀ ኅብረተሰብ እስከ ምድር ጫፍ መልእክቱን እንዲያውጅና ተግባራዊ አንድምታውን ሁሉ ባካተተ መልኩ እንዲታዘዙት ተጠርተዋል[13]::

ስለዚህ የታሪክ ዐላማ እያንዳንዱ ሰው ለእግዚአብሔር ሕግ የሚሰጠውን ምላሽ መፈተን ነው:: ይህ የፈተና ወቅት ከገነት የወጣንበት እና ወደ ገነት ተመልሰን በምንገባበት አልያም ፈተናውን የወደቀ ወደ ከሃነም የሚጣሉበት የሽግግር ወቅት (ቅንፍ) ነው:: የቁርአን ዐቢይ መልእክት ፍርድ ነው:: የፍርድ ሰዓት እየደረሰ ነው:: የሰው ልጅ ጊዜያዊ የምድር መኖሪያው ሲያበቃ ገነት ወይም ገሃነም ይጠብቀዋል::

የሰው ልጅ ከዚህ የፈተና ጊዜ ማምለጥ የሚችለው፣ ወደ መሓሪው አምላክ ለሚያደርሰው የእስልምና ሃይማኖት በመገዛት ነው:: የኡማ ተልእኮ ለዚህ ምሪት ምስክርነት መስጠትና በቁርአን እንደ ተገለጠው ፍጹም ለሆነው ለእግዚአብሔር ሕግና በሐዲስና በሸሪአ እንደ ተብራራው ሕዝቦች እንዲገዙ በየስፍራው ሁሉ ማብራታት ነው::

ነገር ግን ሙስሊሞች ሁሉ ለእስልምና በታማኝነት ይገዛሉን? በፍጹም በሁለት ሐሳብ የሚያነክሱ ብዙዎች ናቸው:: ይህንን ማስተካከል የተሐድሶአውያኑ ሙስሊሞች ተግባር ነው:: እነዚህ ግለሰቦች በጊዜያዊነት በዚህ ምድር በሚኖሩበት ወቅት ሙስሊሞች ለእስልምና ሃይማኖት ታማኝ እንዲሆኑ

[12] H. A. R. Gibb, *Mohammedanism* (New York: Oxford University Press, 1969), 9.

[13] Wilfred Cantwell Smith, *Islam in Modern History* (Princeton: Princeton University Press, 1957), 14.



ይረዷቸዋል:: የሙስሊሙ ታማኝነት በብዙ መልኩ ከዛሬው ይልቅ የቀድሞው የሚበልጥ ሆኖ ሳለ፣ ዛሬ ዓለም ዐቀፉ የሙስሊም ኡማ እስልምናን ወርቃማ ወደ ሆነው የቀድሞ ዘመን ለመመለስ በሚፈልጉ የተሐድሶ እንቅስቃሴዎች ተጋልጦ ይገኛል:: እነዚህ ተሐድሶዎች ሦስት መልክ አላቸው[14]:—

1. ፀማዕያንና ጅሃዳውያን:— ይህ እንቅስቃሴ አሁን ያለንበት ውጥንቅጥና አደገኛ ወቅት ሊስተካከል የሚችለው፣ እስላማዊ ያልሆኑ ክልሎችንና እስልምናን ለመቀየር በተነሡ ግብዝ ሙስሊሞች ላይ ሁከት በመፍጠር እንዲሁም እነዚህን ግለሰቦችና ተቋማት ፊት ለፊት በኀይል በመጋፈጥ ነው የሚል እምነት አለው:: የእስልምና ወርቃማ ዘመን ነው የሚባለው፣ በመዲና መሐመድ በመሠረቱት ተምሳሌት ሙስሊሞች ለማኅበረሰቡ ታማኝ ሲሆኑ ነው:: በዚያን ወቅት በመዲና እስልምናን ለመመሥረት፣ ለመቀደስና ለማስፋፋት ዐመፅ ጥቅም ላይ መዋሉ ለዛሬ ምሳሌ ሊሆነን እንዲሁም በዘመናችን ሁኔታ የግድ ልንተረጉመው የሚገባን ጉዳይ ነው የሚል ንቅናቄ ነው (ለምሳሌ አልቃይዳ)::
2. ሕግ አጥባቂ ተሐድሶዎች፣ የእስልምና ወርቃማ ዘመን የሚመጣው ኡማው በታማኝነት ሱናንና ቁርአንን ሲከተል እንዲሁም እነዚህን መመሪያዎች ታማኝ በሆነ ሸሪአዊ ልምምድ ሲተገብር ነው የሚል እምነት አላቸው (ለምሳሌ የዐረቡ ውሃቢያ)::
3. ተራማጆች ደግሞ የቁርአን መንፈስ ለዘመናዊ ሃይማኖታዊ ላልሆነ የሙስሊም ማኅበረሰብ ግንባታ መነሻ መሆን አለበት ይላሉ:: ሐዲስ፣ ሱናና ሸሪአ ኡማው በዘመናዊው ዓለም ውስጥ ጥሩ ተምሳሌት ሆኖ ኑሮውን እንዲኖር አጣብቂኝ ውስጥ አስገብቶታል ባይ ናቸው::

እነዚህ የተሃድሶ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ይስማማሉ:—

1. እስልምና የተጨቋኞችና የተጣሉ ሰዎች እምነት ነው:: በተቃራኒው ክርስትና ግን የጨቋኞች እምነት ነው (ሙስሊሞች የምዕራቡ ክርስቲያን ጨቋኝ ነው የሚለውን አስተሳሰብ እያደረባቸው የመጣው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው)[15]::
2. ሙስሊሞች የእስልምናን ሥልጣን በምድር ሁሉ ላይ ለማስፈን ጠንክረው መሥራት አለባቸው::

[14] Dudley Woodberry, "Justice and Peace," *Christian History* 21:2 (August 2002), 44.

[15] ዝኒ ከማሁ፣ 45::

3. ሙስሊሞች፣ የሙስሊሙን ሕዝብ ክብርና ሥልጣን ለማስመለስ ማዕከላዊ ወደ ሆነው የእስልምና እምነትና ተግባር መመለስ አለባቸው።

ተሐድሶአውያኖቹ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ የራሱ ዐይነተኛ መለያ ጠባዩን እንደያዘ ይኑር በሚለው ጉዳይ ላይ ትልቅ ትኩረት ያደርጋሉ። በተወሰነ ደረጃም ቢሆን፣ እስልምና ልዩነትን ይቀበል ነበር፤ እያንዳንዱ ሕዝብ የራሱ የሆነ ነቢይ እንደ ነበረው ያምን ነበርና። ሆኖም አሁን ቁርአን ተገልሟል። በመጨረሻው የፍርድ ጊዜ ገነት ለመግባት ተስፋ የሚያደርጉ ለእስልምና መገዛት ብቸኛው አማራጫቸው ነው። የተለያዩ የተሐድሶ ንቅናቄዎች ግን ልዩነትን በተለያየ መንገድ የማስተናገድ ዐላማ አላቸው። ነገር ግን ለእስልምና መገዛት ሙስሊሟን ምድራዊ ሕይወታቸውን እንዲሁም ወደ ፊት ገነትን ለመውረስ ብቸኛ ጉዳይ እንደ ሆነ ያምናሉ።

ስሚዝ የሚከተለውን አስተያየት ይሰጣል:—

> ቢጋራም ሆነ በተናጠል ሙስሊሞች ከዚህ ዓለም ባሻገር ገነትን ይፈልጓታል። ለገነት የግል ዝግጅት ለማድረግ አመቺ የሆነ ማኅበረሰብ ያስፈልጋል። ይህ ምድራዊ ሕይወት ጊዜያዊውን ጽድቅ ዘመን ከማይሽረው የመጪው ዘመን ድነት ጋር ለማዋሐድ የሚደረግ ትግል ነው። የታሪክ ትርጉም የሚወሰነው ይህ ምን ያህል እውነት ይሆናል በሚለው ጉዳይ ላይ ነው[16]።

ይህ ማንኛውም የሕይወት አቅጣጫ ለእስልምና መገዛት አለበት የሚለውን መሠረት ያደረገ ነው። ይህ ተግባር በሱኒ እስልምና የከሊፋዎች ድርሻ እንዲሁም በሺአ እስልምና የኢማሙ ድርሻ ነበር። የክርስትና ነገረ መለኮት እንዲሁም የእስልምና ሃይማኖት ምሁሩ ኬኔት ካሬግ ሲያብራራ:—

> እስልምና የአምልኮ መንገድ ብቻ ሳይሆን፣ የአገዛዝ ዐይነትም ነው። የእግዚአብሔር ግዛት ሰዎች ላይ እንዲሰፍን ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች ይህን ግዛት እንዲያሰፍኑት ይጠብቃል[17]።

ነፍስን ሁሉ በእስልምና ሥር ማስገዛት የሙስሊሙ ሕዝብ የመጨረሻ ተልእኮ ነው። በታሪክ ፍጻሜ የሚከናወነው የፍርድ ቀን መምጣት ተልእኮው እስከ

[16] Smith, *Islam in Modern History*, 22.

[17] Kenneth Cragg, *Sandals at the Mosque* (New York: Oxford University Press, 1959), 124.



ምን ድረስ ነው በሚለው ርእስ ጉዳይ ላይ የሙስሊም ምሁራን አይግባቡም። በድሩ ዲ. ቀትራጋ እንደሚናገረው የእስልምና ነገረ መለኮታውያን የሙስሊም ግዛት ከመጨረሻው ፍርድ በፊት የሚያትፈው ክልል ላይ አይስማሙም። አንዳንዶች ሙስሊሞች እንደ ጨው በየቦታው ተበትነው ይኖራሉ ሲሉ፣ አንዳንዶች ግን የሙስሊሙ ኡማ ዓለም ዐቀፋዊ ይሆናል ባይ ናቸው ሌሎቹ ደግሞ ከመጨረሻው ፍርድ በፊት ከእስልምና እምነት የማፈግፈግ ሁኔታ ይከሠታል የሚል እምነት አላቸው።

ጂ.ኢ. ግሩነባውም አስተውሎቱን በሚከተለው መንገድ ይገልጻል:—

> ሰዎች ለፖለቲካና ለመንፈሳዊ ሕይወት መታደስ ያላቸው ጉጉት ሰዎች መጻኢ ዘመናቸውን ለማሻሻል ያላቸውን ጽኑ ፍላጐት አመልካች ነው። ይህም ነገሮች መልካም ሆነው እንዲቀጥሉ በማድረጉ ረገድ ያለው ድርሻ ቀላል አይደለም። ይህ እምነት የእስልምና ትውፊት ታሪክን እያሽቈለቈለ ይሄዳል ብሎ ከሚያምነው የተለየ ነው። ትልግ ዕድገት የታየበት እስልምና በነቢዩ መሐመድ ዘመን የነበረው እስልምና ነው። ሁለተኛው ደግሞ በእርሳቸው ተተኪዎች ዘመን የነበረው እስልምና ነው። ዓለምም ሆነች እስልምና አብረው እያሽቈለቈሉ ነው[18]።

ይሁንና ይህ የታሪክ የሽግግር ወቅት ወደ ድምዳሜ ሲደርስ፣ መሲሑ ኢየሱስ ወደ ምድር ይመጣል። ለዚህ እምነት አስተዋጽኦ ያደረገ አንድ ግልጽ ያልሆነ ጥቅስ አለ (ሱራ 43፥61)። የነገረ መለኮት ሰዎች ኢየሱስ ካልተገኘ በስተቀር ኢየሱስ የፍርድ ምልክት ሊሆን እንደማይችል ያመለክታሉ። በተጨማሪ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት የሚያመለክተው ሐዲስ የተባለው መጽሐፍ ነው።

የተወሰኑ የሺአይት እስልምና ቡድኖች ኢየሱስ መድረሻው ካልታወቀው ከዐሥራ ሁለተኛው ኢማም ጋር ዳግም እንደሚመጣ ያምናሉ። ኢየሱስ ሲመጣ ምን ያደርጋል? እነዚህ ሺአይቶች ከዐሥራ ሁለተኛው ኢማም ጋር ኢየሱስ በኢየሩሳሌም እንደሚገለጥ የሰው ሁሉ ዐይኖች እንደሚያዩቸው ያምናሉ። ኢማሙና ኢየሱስ ሙስሊሙና ክርስቲያኑ በአንድነት ሆነው በሰላም እንዲኖሩ ያዛሉ።

[18] G. E. von Grunebaum, *Islam Essays in the Nature and Growth of a Culturl Tradition* (New York: Barnes and Noble, 1961), 227.

ኢየሱስ ዐማፆችንና መስቀልን በመደምሰስ የክርስቲያኖችን ስሕተት እንደሚያርም ብዙ የሱኒ ሙስሊሞች ያምናሉ። እስልምናን በማደስ ዓለምን ለፍርድ ያዘጋጃል። ኢየሱስም በሥጋው ይሞትና ከሌሎች ጋር ለመጨረሻው ፍርድ ይነሣል ባዮች ናቸው።

ከዚህ ሁሉ አንጻር ሲታይ፣ የእስልምና ተልእኮ ምንድን ነው? በቅርቡ ለሁለት የእስልምና ምሁራን ይህን ጥያቄ አቀረብሁላቸው። በመጀመሪያ አሁን በጀርመን የሚኖር ኢራናዊ የሺአይት ምሁር ይህንን አስተያየት ሰጠ፣ "ዳር አል-ሰላም (የሰላም ግዛት) ሙስሊሞች በሚከበሩበት ተቀባይነትን ባገኙበት ስፈራ ይሰፍናል። እኛ ሙስሊሞች በጀርመን ሰላምን እስካገኘን ድረስ የፖለቲካ ሥልጣን አያስፈልገንም። ተልእኮአችን የእስልምና ምስክሮች መሆን ነው። ሁሉም ሕዝብ የራሱ የሆኑ ነቢያት አሉት። ስለዚህ እግዚአብሔር የእምነት ልዩነትን ፈቅዷል። እያንዳንዱ ሰው ሙስሊም መሆን የለበትም። ይህ ቢሆን ያሰለች ነበር"።

ከሳምንት በኋላ የሱኒ ሙስሊም የሆነውን ሕንዳዊ፣ "በሰሜን አሜሪካ የሙስሊሞች ተልእኮ ምንድን ነው?" ብዬ ስጠይቀው እንዲህ መለሰልኝ፣ " ተልእኳችን በሰሜን አሜሪካ የእስልምናን እውነት መመስከር እና ሰዎች ለእስልምና እንዲገዙ ጥሪ ማቅረብ ነው። በአሁኑ ሰዓት ብዙ የፖለቲካ ሥልጣን እንዳናገኝ ማኅበረሰባችን በጣም ትንሽ ነው። ሆኖም ወደ በኋላ የፖለቲካ ሥልጣን ለማግኘት ወሳኝ የሆነ ብዛት ይኖረናል። ያኔም ዳር አል-ኢስላምን (በሙስሊም የምትተዳደር አካባቢ) በመላው ሰሜን አሜሪካ እንመሰርታለን" እነዚህ ሁለት አስተያየቶች በዓለም ዐቀፍ እስልምና ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉትን ልዩነቶች የሚያሳዩ መስኮቶች ናቸው። ሆኖም ዋናው ሐሳብ ለታማኝ ሙስሊሞች እውነቱ ሁሌም አንድ ነው። የሙስሊም ሕዝቦች ተልእኮ ከአላህ በቀር አምላክ እንደ ሌለና መሐመድ የአላህ ነቢይ እንደ ሆነ መመስከር ነው።

## ወንጌልና ታሪክ

በመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፣ የሰው ልጅ ታሪክ በኤደን ገነት እንደ ጀመረና በወደፊቱ የከበረች ከተማ እንደሚጠናቀቅ ይገልጻል። ከተማዋ ከሰማይ ወደ ምድር ትወርዳለች፤ የመሲሑ ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን ነች። ይህም ታሪክ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ሥራ መታያ ነው ለማለትና ሁሉም ታሪክ በምድርና በሰማይ ላለው የእግዚአብሔር መንግሥት ፍጻሜ ወደ ፊት እየገሠገሠ ነው። ለዚህም ነው የመጽሐፍ ቅዱስ ግልጠት ዋናው ፍሬ ነገር የእግዚአብሔር ተግባር በታሪክ ውስጥ የሆነው። ብዙው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ



የእስራኤል የጉዞ ታሪክና ጊዜ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለማከናወን በሚያደርጉት የወደፊት እርምጃና የሚገጥማቸውን መሰናክል ያሳያል።

ከኒውዮርክ እና በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ጥቃት ከተፈጸመ ከብዙ ሳምንታት በኋላ፣ እኔና ባለቤቴ በካዛኪስታን የካራጋንዳን አብያተ ክርስቲያናት እየጐበኘን ነበር። በአካባቢው ሬዲዮ ጣቢያ ቃለ መጠይቅ ተደርጉልኝ ነበር። ብዙዎቹ አድማጮች ዓለማዊ ሙስሊሞች ነበሩ።

ጠያቂዬ እንዲህ አለ፡— "እኛ እንደምናምነው አገራችሁ ለድኻ ሕዝቦች ደኅንነት (መልካምነት) አትጨነቅም። እንደ ክርስቲያን በአሜሪካ መራሽነት በአሸባሪዎች ላይ በሚደረገው ጦርነት ያንተ አመለካከት ምንድን ነው?"።

"መንግሥታት የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ይተጋሉ" ስለዚህ ወደ ጦርነት ቢሄዱ ምንም የሚያስደንቀኝ ነገር የለም። ሆኖም መንግሥታት የሚከተሉት ያለው መንገድ የእግዚአብሔርን መንግሥት መሲሑ ኢየሱስ ባስተዋወቀበት በታሪክ ድራማ ድምዳሜ በሚመጣበትና በሚፈጸምበት መንገድ አይደለም። ማዕከላዊው የእግዚአብሔር መንግሥት ሥነ ምግባር ኢየሱስ እንደ ወደደ ጠላትን እንኳን መውደድ ነው። እንደ ገናም ይህ ማኅበረሰብ ሆኖ የእግዚአብሔርን መንግሥት ኢየሱስ እንዳደረገ በፍቅርና ሌሎችን በማገልገል መግለጥ የቤተ ክርስቲያን ጥሪ ነው።

ለመንግሥቴ እጸልያለሁ ለሕዝቤና ለዓለም ሕዝቦች በአጠቃላይ ፍትሕና ጽድቅ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሆን እመሰክራለሁ። ሆኖም የመጀመሪያ ታማኝነቴ ለእግዚአብሔር መንግሥት ነው። ይህ መንግሠት ከተለያየ ጐሣ፣ ነገድና ቋንቋ የተሰበሰቡ የታረቁና ይቅር የተባሉ ሕዝቦች ስለሆነ አስደናቂ መንግሥት ነው።

አሳማ ቢን ላደንን አግኝቼ ዐቅፌው እርሱን የሚወደው የንጉሡ አምባሳደር መሆኔን ልነግረው እፈልግ ነበር። የንስሓ ይቅርታ እና የዕርቅ ጥሪ አቀርብለት ነበር።

የወንጌል ማዕከል እግዚአብሔር በመሲሑ ሆኖ በመስቀል ሞትና ትንሣኤ በተገለጠ ፍቅር እኛን ከራሱ ጋር ማስታረቁ ነው። እግዚአብሔር በሰዎች ታሪክ መጀመሪያ የቃል ኪዳን ዘር ተከለ። አዳምና ሔዋንም ከእግዚአብሔር ፊታቸውን ሲመልሱ ኀጢአተኛነትና ሞት የሰዎች ዕጣ ፈንታ ሆነ። ሆኖም እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ይኖሩበት ወደ ነበረው ስፍራ መጥቶ ፈለጋቸው፤ ጠራቸውም። ቍጥቋጦ ሥር ተደብቀው ሲያገኛቸው በጥልቅ ሐዘን ሆኖ ቃል

ኪዳን ገባላቸው:: እባብ (ክፉ ኀይላት) ከሴት የሚወለደውን ወንድ ልጅ ያቈስሉታል:— እርሱ ግን ጭንቅላታቸውን ይፈጠፍጠዋል::

ይህ በገነት የተደረገው ትዕይንት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን የታሪክ ትርጕምና ዐላማ ለመረዳት ዋና ነገር ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፣ እግዚአብሔር በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የሚያከብሩትንና ለሌሎች ሕዝቦች ብርሃን የሚሆኑትን የታደገበት ታሪክ ነው:: እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን በመግባት የመጀመሪያው ሕዝብ ነው:: ጥሪውም ለዓለም ሕዝብ በረከት እና ብርሃን እንዲሆኑ ነው::

በመሲሑ ሁሉም ሕዝቦች ለእግዚአብሔር ቤተሰብነት ተጠርተዋል:: ክርስቲያኖች እንደሚያምኑት ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም ጐሣ ቋንቋና ሕዝብ ያቀፈች እንዲሁም በወንጌል ሁሉንም የምትደርስ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ነች::

እስራኤል ብቻ ሳትሆን ሕዝቦች ሁሉ የተፈጠሩት እግዚአብሔርን ለማክበርና ከእርሱ ጋርም በኅብረት ለዘላለም በመደሰት ነው:: የእኛ ዐመፅና ኀጢአተኛነት አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ ይህንን ዐላማ አቃውሶታል:: ሆኖም እግዚአብሔር ለዘላለሙ አልጣለንም:: ይልቁንም በየግል ተገናኝቶን በታሪካችን ውስጥ እውናዊ ተሳትፎ አደረገ፤ "የቈሰለው ፈዋሻችን"[19] ሆኖ ራሱን ገለጠ:: በመሲሑ ሆኖ እግዚአብሔር ስለ እኛ ተሠቃየ፤ ለእኛ ሞቶ ተቤዠን:: በእርሱ መሥዋዕታዊ ሞት እኛ ይቅር ተባልን፤ ቤተ ክርስቲያንም ይቅር የተባሉ ኀጢአተኞች ኅብረት ነች::

የሚያምኑ ሁሉ አዲስ የእግዚአብሔር መቅደስ ይሆናሉ:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር መቅደስ እርሱ የሚኖርበት ሕዝቡ ነው:: ከእግዚአብሔር ሕዝብ ውጪ ሌላ የእግዚአብሔር ቤት የለም:: ከእንግዲህ ሌላ ቤተ መቅደስ አያስፈልግም:: የተቀደሰው ማዕከል ማለት ከሞት የተነሣው መሲሕ በመንፈሱ በሕዝቡ ውስጥና በስሙ በተሰበሰበበት ሕዝብ መኻል መገኘቱ ነው (ኤፌሶን 2፥19-22፤ ማቴዎስ 18፥20):: ይህ መንፈስ ቅዱስ የሚያድርባት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር በሥጋ ተገልጦ በምድር መኖር ማለት ነው::

እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ይኖራል:: ኢየሱስ ለፍትሕ የሚቶጋ ነበር:: በየትም ስፍራ የእርሱ መንግሥት ስትመጣ ለድኾችና ለተጨቈኑ ተስፋ አለ::

[19] Henri J. M. Mouwen, *The Wounded Healer* (New York: Image Books, 1979).



ቤተ ክርስቲያን በዙሪያችንና በዓለማችን የመሲሑ የፍትሕና ለሰላም መግዛት ተምሳሌት ተብላ መጠራት አለባት:: መሲሑ እየመሠረተ ያለው መንግሥት ዓለም ዐቀፍ እንዲሁም በፈቃደኝነት የሚከናወን ነው:: ሁከትም የሌለበት ነው:: በዚህ መንግሥት ጕልበት ስፍራ የለውም:: ይህ መንግሥት ለሚቀበሉ ሁሉ የሰላም መንግሥት ነው:: መስቀሉ ለእግዚአብሔር መንግሥት ግብረገባዊ መንገድ ነው፤ በተጨማም የመንግሥቱ ማኅበረሰብ የሆነች ታማኝ ቤተ ክርስቲያን ናት::

የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ጕዞ በኢየሱስ ስም መሰብሰብን ይጨምራል:: ለአምልኮ የሚሰበሰቡት ዐልፎ ዐልፎ አብሮ ዳቦ በመቍረስና ጽዋውን መጠጣት ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ ለተሰቀሉት ይቅርታን እንደ ጠየቀ እንዲሁም እንደ ሰጠ መቤዠነትና ይቅርታ ቃል ኪዳን ምልክቶች (ምሳሌነት) ይጠቀሙበታል:: የተቈረሰው ዳቦና የተጨመቀው በኢየሱስ የተመሠረተው ቃል ኪዳን ምልክት ነው:: የንስሓ ቃል ኪዳንና አንዱ ለአንዱ ለጠላቱ ጨምሮ መሥዋዕታዊ ፍቅር የሚገልጽበትና ራስን በመስጠት የሚያገለግልበት ቃል ኪዳን መልከት ነው::

መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን ይመሠርታል:: አዲስ ሕይወትንም ይሞላታል:: የብሉይ ኪዳን ነቢይ የሆነው ሕዝቅኤል ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ከመሠዊያው እየፈሰሰ ምድረ በዳን የሚያጠጣ ወንዝ በራእይ ተመለከተ (ሕዝቅኤል 47፥1-2):: በወንዙ ዳር ላይ ቅጠሉችና ፍሬ ያለው ለመድኀኒት የሚሆን ዛፍ ይበቅላል:: ከመሠዊያው ወደ ምድረ በዳ ይፈስ የነበረው፣ ሕዝቅኤል በራእይ ያየው ውሃ በዘይቤያዊ አነጋገር ከአብ እንዲሁም ከተሰቀለውና ከተነሣው መሲሕ የሚሠርጸው መንፈስ ቅዱስ ነው::

በራእይ የታየው መድረ በዳ ደግሞ ዓለም ነው:: የሕይወት ወንዝ ከመሠዊያውና ከመቅደሱ ወደ ምድረ በዳ ይፈሳል:: ከመሲሑ ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ፈሷል:: ይህ ሕይወት ሰጪ ወንዝ ነው ዛፎች በምድረ በዳ እንዲያድጉና ፍሬ እንዲያፈሩ የሚያደርገው:: እንደ እኔ ግምት ፈዋሽ ቅጠል ጻድቅ ሕዝቦች ሲሆኑ የዛፍ ፍሬ ደግሞ የመሲሑ መንፈስ ፍሬ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጐነት፣ ታማኝነት፣ ጭምትነት እና ራስን መግዛት ናቸው (ገላትያ 5፥22)::

የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ በምድር ላይ ያለው ምድረ በዳ ሁሉ በዚህ ሕይወት ወንዝ (መንፈስ ቅዱስ) እስኪነካ ድረስ ለሁሉም ማኅበረሰብ የወንዙ መተላለፊያ መሆን ነው:: ይህ የደስታ ተልእኮ ነው:: በየትም ስፍራ ላይ በኢየሱስ ስም

ሰዎች ሲገናኙና በእርሱ ጸጋ ሲደሰቱ ደስታ አለ። ይህ የመጻኢው ዓለም ባለተስፋ ማኅበረሰብ ነው። በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር የሚፈጸምበትን ዘመን የሚጠብቅ ነው። ቤተ ክርስቲያን በማኅበረሰብ ውስጥ የምትገኝ ማኅበረሰብ ነች። በምድር ትኖራለች፤ ነገር ግን ከምድር አይደለችም። "ጨው" እና "ብርሃንም" ተብላለች (ማቴዎስ 5፥3-16)። ይህም ተጽእኖ ማሳደርን እንጂ መቈጣጠርን የሚያመለክት አይደለም።

መሲሑ ለደቀ መዛሙርቱ መመሪያ ሲሰጥ፣ "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (ማቴዎስ 28፥19) ብሏል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ መልእክቱ በፍጥነት መዳረስ እንዳለበት በአጽንኦት ተነግሮአል። ሁሉም ሕዝቦች ወንጌልን መስማት አለባቸው፤ የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ይህንን መልካም ዜና ከሕዝብ ወደ ሕዝብ ማድረስ ነው። ታሪክ ፍጻሜ አግኝቶ የሚደመደመው ሁሉም ሕዝቦች ወንጌልን ሲሰሙ ነው። ይህንን ቀን በመጠበቅ ስለ ወደ ፊት፣ "ውሃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ ትሞላለች" (ዕንባቆም 2፥14)።

ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይሆናል" (ማቴዎስ 24፥14)። ክርስቲያኖች እንደሚያምኑት ወንጌልን መቀበልና መታመን በአንድ ሕዝብ መኖርና ከአንዱም ሕዝብ ወደ ሌላው በመተላለፍ የእግዚአብሔር መንግሥት ይስፋፋል። ይህም የሚሆነው ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረትና በእውነተኛ አማኞችና ደቀ መዛሙርት ስትሞላ ነው።

የቤተ ክርስቲያን ከሕዝብ ወደ ሕዝብ መንቀሳቀስ የእግዚአብሔር መንግሥት መስፋት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ብዙ ቤተ ክርስቲያናት እኔ አባል የሆንኩባትን የአናባፕቲስት አብያት ክርስቲያናት ጨምሮ፣ ሙስሊሞች ትኩረት ከሚሰጡት የእግዚአብሔርን አንድነት ፈቃዱን መግለጽ አለባቸው። ለሚለው የሙስሊም እምነት ተመሳሳይ አቋም አላቸው። በአዲስ ኪዳን አገላለጽ ቶውሂድ ማለት አማኙ ማኅበረሰብ የመሲሑ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሆኑ ማለት ነው። አማኞች በመሲሑ መንገድ ሲጓዙ በአንድነት በኅብረት ራስን በመስጠት በእግዚአብሔር ፍቅር ይኖራሉ። ከላይ እንደ ተገለጸው ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር መንግሥት መኖር እውነተኛ ምልክት ነች። ይህ ንስሓ የገባና ይቅር የተባለ፣ ለእግዚአብሔር የሚገዛ ማኅበረሰብ ነው። በጸጋው እና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የሚኖር ኅብረት ነው። የሚጸልይ ሕዝብ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድና



መንግሥት፣ "ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁም በምድር" (ማቴዎስ 6፥9-13) ባለበት ስፍራ መሆንን የሚጠማ ሕዝብ ነው።

በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር መንግሥት ፍጻሜ ሁል ጊዜ መንግሥቱን ከሚቃወሙ ኀይላትና ግለሰቦች በተቃርኖ ነው። በመጨረሻው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚገኘው አስደናቂው ራእይ፣ ድንቅ ስለሆነችው ዘላለማዊ ከተማ ብቻ ሳይሆን፣ መቤዠትን እምቢ ለሚሉም የፍርድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአል።

ንስሓ የማይገቡና ክፉዎች ከእግዚአብሔር ከተማ ውጪ ናቸው (ራእይ 21፥27፤ 22፥11:15)። ኢየሱስ፣ "ፍየሎች" የሆኑት ለደኻ፣ ለተራበ፣ ለታሰረና ለታመመ እክብካቤ የማያደርጉ ሁሉ ለዲያቢሎስ ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘላለም እሳት እንደሚጣሉ አስጠንቅቋል (ማቴዎስ 25፥31-46)። ይህ፣ እግዚአብሔር በመጨረሻው የፍርድ ሰዓት እንኳ የጽድቅን መንግሥት በማንም ላይ አስገድዶ እንደማይጭን የሚያስረዳ ነው። የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚቃወሙና የእርሱን የመታረቅና የመቤዠት ጸጉ ጥሪውን የሚቃወሙ ፍርድ ይጠብቃቸዋል።

2002 ዓ.ም በበልግ ወቅት በኢራን በሺአይቶች መስጊድ የዐሥራ ሁለተኛው ኢማም ልደት ሲያከብሩ ለብዙ መቶ ጉባኤዎች ንግግር አድርጌ ነበር። ከላይ እንደገለጽሁት እነዚህ ሺአይቶች ዐሥራ ሁለተኛው ኢማም በታሪክ ፍጻሜ ከኢየሱስ ጋር ይመጣል ብለው ያምናሉ። የአካባቢው መስጊድ ኢማም ስለመሲሑ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት እንድናገር ጋበዘኝ።

ይህንን ነበር ያካፈልኋቸው፣ "የመሲሑ አገልግሎት ለድኾችና ለጭቍኖች ተስፋ ነበር። ወደ እርሱ የመጡትን ሁሉ ፈውሷል። ሆኖም በምድር ላይ ፍትሕንና ሰላምን ለመመሥረት ተልእኮውን አልፈጸመም። ይህ ተልእኮ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ድርሻ ስለነበር ተልእኮውን የመቀጠል ኀላፊነት አለባቸው። ከእንስሳት ጋር የሚኖረን ግንኙነት እንኳን ለእግዚአብሔር ፍጥረት እና ለእያንዳንዳችን የምንሰጠው ትኩረት አመልካች መሆን አለበት"።

እነዚህ ጥረቶች ሁሉ ከንቱ እንዳይደሉ እምነት አለን፤ መሲሑ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለዘላለም ለመፈጸም አንድ ቀን ይመጣል፤ ሕዝቦች ሁሉም ያዩታል።
"ምንድን ነው የምናየው? የስቅለቱ ምልክት የሆኑትን የቈሰሉ እጆች ተዘርግተው እናያለን። ሁላችንን ሊያቅፈንና ሊቤዠን የሚፈልገውን የቈሰለውን መሲሕ ዐይኖች ሁሉ ያዩታል። ኀጢአታችን ኢየሱስን ምን እንዳደረገው ስናይ

ሁላችንም እንጸጸታለን (ራእይ 1፥7)። በእነዚህ በቈሰሉ እጆች እግዚአብሔር ምን ያህል እንደ ወደደን እናያለን። የእግዚአብሔር መንግሥት የሚመጣው በመቤዥታዊ ፍቅር ነው። ለተሰቀለውና ለተነሣው መሲሕ ታሪክን ወደ ትክክለኛ ፍጻሜ እንዲያመጣው ሥልጣንን ሰጥቶታል። መሲሑ ወደ ምድር ሲመለስ ፍጥረትን ሁሉ ይቤዥል ምክንያቱም አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይሆናልና። የጽድቅና የሰላም መንግሥቱን ለዘላለም ይመሠረታል። እርሱን የሚወዱ ሁሉ ከእርሱ ጋር ለዘላለም ይገዛሉ (ራእይ 5፥9-10፤ 21፥1-5፤ 22፥1-5)።

ሁሉም የሙስሊም ማኅበረሰብ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን የታሪክን ፍጻሜ በንቃት ይጠብቃሉ። በሁለቱም ማኅበረሰቦች መሲሑ ኢየሱስ ታሪክን ወደ ድምዳሜ ለማምጣት ታላቅ አስተዋጽኦ አለው።

ብዙ ጊዜ በክርስትናና በእስልምና ጉዞ ላይ ሳለን፣ ኢየሱስ ልዩ በሆነ መንገድ ለእርሱ መገኘት እንድንቀበል ጽኑ ፍላጐቱ ነው። ሆኖም በመጨረሻው ዘመን የኢየሱስ ተልእኮ የሙስሊምና የክርስቲያኖች ተስፋ ለየቅል ነው። እርሱ ያዋህዳል ያለያያልም። እርሱ ሥልጣኑን ሥራ ላይ የሚያውለው ክርስቲያኑንና ሙስሊሙን በሚያስደንቅ መንገድ ነው። የእርሱን የማያቋርጥ አብሮነት ወደ ዳር የሚያደርግ አንዳችም ነገር የለም። ይህ የሚሆነው ለምንድን ነው?

*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ*

ሕዝቅኤል 47፥1-12፤ ራእይ 22፥1-7

*የቁርአን ምንባብ*

ሱራ 50፥16-45

## <u>የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. የአዲስ ኪዳንንና የቁርአንን አማኒ ማኅበረሰብ የተልእኮ ግንዛቤ ያወዳድሩ።
2. ታሪክን በተመለከተ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ቅዱሳት መጻሕፍቶቻቸውን መሠረት በማድረግ የሚሰጡትን ትንታኔ ያወዳድሩ።
3. የመሲሑ የደግሞ ምጽአት ተልእኮ ከእስልምናና ከአዲስ ኪዳን አስተምህሮ አንጻር ያወዳድሩ።



4. ሰዎች "ከሥልጣኔ ጋር ስለሚደረግ ጦርነት" ሰፊ ሐሳብ አላቸው። የዚህ ሐሰብ መሠረቱ ምንድን ነው? ለዚህ ጒዳይ ቤተ ክርስቲያን ያላት መልስ ምን መሆን ይኖርበታል?
5. እያንዳንዱ ክርስቲያን ማኅበረሰብ ለተልእኮው አስተዋጽኦ የሚያደርግ ልዩ የሆነ የጸጋ ስጦታ አለው። የዳግም መጥምቃውያን ስጦታ ምንድን ነው? የካቶሊኮች ስጦታስ? የጰንጤቈስጤ እንቅስቃሴ ያለባቸው ቤተ ክርስቲያናትስ?
6. የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ለቤተ ክርስቲያን የሚያበረክተው ስጦታ አለ? ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ቤተ ክርስቲያን ይበልጥ ታማኝነቷን ጠብቃ እንድትኖር የሚጫወተው ሚና አለን?
7. ስለሙስሊሙ ማኅበረሰብ እርስዎን ያስደነቅዎት ነገር ምንድን ነው? በምን መንገድ ነው የእስልምናው አማራጭ የወንጌልን ትርጒም ለማብራራት የሚረዳን?
8. ስለ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ያስደነቅዎ ነገር ምንድን ነው?

## ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

# ማጠቃለያ ሐሳብ

የሙስሊሙ ማኅበረሰብም ሆነ ክርስቲያኖች፣ ቃለ እግዚአብሔርን በሕይወታቸውና በኑሮአቸው ተግባራዊ ለማድረግ ጽኑ ፍለጎት ያለቸው ሕዝቦች ናቸው:: ሁለቱም ክፍሎች የእግዚአብሔርን ቃል እውነት፣ ለሰው ልጆች ሁሉ ያማሳወቅ ኀላፊነት እንዳለባቸው ያምናሉ::

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ እግዚአብሔር ራሱን በሙላት የገለጠው፣ በዐረብኛ ቋንቋ ተጽፎ ከሰማይ ወደ ምድር በወረደው በእግዚአብሔር ቃል (በቁርአን) አማካይነት ነው የሚል አቋም ሲኖረው (ሱራ 12፥2)፣ ክርስቲያኖች ደግሞ፣ "ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ ዐደረ፤ አንድ ልጁም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን" (ዮሐንስ 1፥14) የሚለው አስተምህሮ የድነት ሁሉ ማዕከል ነው በዮች ናቸው::

የሙስሊሞች ቀዳማይ ዐላማ ሕዝቦች ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዐላማ በመገዛት ወደሚገኘው ሰላም እንዲመጡ እንዲሁም የእያንዳንዱን የሰው ልጆች የሕይወት ክፍል ለእግዚአብሔር ፈቃድ ይገዛ ዘንድ፣ ለሕዝቦች ሁሉ ታማኝ ምስክር መሆንና ሰዎች ሁሉ ለእስልምና ሃይማኖት እንዲገዙ ጥሪ ማድረግ ነው::

የክርስቲያኖች ቀዳማይ ዐላማ ደግሞ፣ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በሙላት መገለጡን ማወጅ ነው:: ይህም ኢየሱስ ሕፃን ሆኖ በቤተ ልሔም በበረት ውስጥ መወለዱን፣ በግብፅ ስደተኛ መሆኑን፣ በናዝሬት ይኖር የነበረ አናጢ መሆኑን፣ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ ማስተማሩን፣ በሁለት ሌቦች መካከል መሰቀሉን፣ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣ መሲሕ መሆኑን እንዲሁም ፈርተው ለነበሩት ደቀ መዛሙርቱ የሰላምን እስትንፋስ እፍ እንዳለባቸው መመስከር ነው:: የቤተ ክርስቲያንም ቀዳማይ ዐላማ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ ምክንያት የሆናትን ይህን መሲሕ ማክበር/ማወደስ ነው::

የዓለማችን በኹከት በምትናጥበት በዚህ ታሪካዊ ወቅት፣ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ በመገኘት፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በወታደራዊ ጡንቻ እንደማትመሠረት ወይም በግዴለሽነት እጅን አጣጥፎ በመቀመጥ እንደማትመጣ፣ ነገር ግን ጉልጉታ በመባል በሚታወቀው ኩረብታ ስፍራ ላይ

በተሰቀለው መሲሕ አማካይነት እውን መሆን እንደምትችል ማወጅ ይኖርባቸዋል፣ "እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን . . . የእግዚአብሔር ኀይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው" (1ቆሮንቶስ 1፥23-24)።

የተሰቀለውንና ሞትን ድል አድርጎ የተነሣውን መሲሕ እግዚአብሔር እንዳከበረው፣ "ከስም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም" (ፊልጵስዩስ 2፥9) እንደ ሰጠው የሚያምኑ ማኅበረሰቦች፣ በመከራ ውስጥ የሚገለጥ ፍቅር ክፉትን ድል የመንሣት ኀይል እንዳለው ማወቅ እንዲሁም ይህ እውነት በሕይወታቸው እውን እንዲሆን መፍቀድ ይኖርባቸዋል። ይህን እውነት ማዕከል ያደረገ ምስክርነት (እማኝነት) እጅግ አስደናቂ እንዲሁም ትልቅ ውጤት እንደሚያመጣ አምናለሁ። በመሲሑ በክርስቶስ መንፈስ ለማገልገል ፍለጎት ያላቸው አማኞች፣ ሙስሊሞችን ጨምሮ በሕዝቦች ሁሉ ዘንድ ዕርቀ ሰላምን የማውረድና ፈውስን የማምጣት ታላቅ የሆነ ክእሉት እንዳላቸው አልጠራጠርም።



# ሙዳየ ቃላት

## የዐረብኛ ቃላት

አባሲድ፡— የአባሲድ ካሊፋቶች ከስምንተኛው እስከ ዐሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን በሉት ጊዜያት ባግዳድን መናገሻ ከተማቸው በማድረግ ይመሩ ነበር። ይህ ወቅት የሙስሊሞች ወርቃማ ዘመን በመባል ይታወቃል።

አብዲ፡— የእግዚአብሔር ባሪያ ወይም አገልጋይ ማለት ነው።

አዛን፡— የጸሎት (የሰላት) ጥሪ ማለት ነው።

አህል አል-ኪታብ፡— የቃሉ ጥሬ ትርጉም፣ "የመጽሐፉ ሰዎች" ማለት ሲሆን፣ ይህም ክርስቲያኖችንና አይሁዶችን የሚያመለክት መጠሪያ ነው።

አላህ፡— በዐረብኛ እግዚአብሔር ማለት ነው (በዐረብኛ የእግዚአብሔር የተጸውዖ/የመጠሪያ ስም ነው)።

አያ/አያት፡— ምልክት/ምልክቶች ማለት ሲሆን፣ ፍጥረት ለእግዚአብሔር መኖር ምልክት እንደ ሆነ ሁሉ፣ እያንዳንዱም የቁርአን ጥቅስ ለእግዚአብሔር አልሆት/መኖር ምልክት ነው።

በረካ፡— ብረከት ማለት ነው።

ቢዳህ፡— የተከለከለ ለውጥ ወይም አዲስ አሠራር ማለት ነው።

ቡራቅ፡— መሐመድን በአንድ ምሽት ተአምራዊ በሆነ መንገድ ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ይዛቸው የሄደች ክንፍ ያላት ፈረስ ነች።

ዳር አል-ሐርብ፡— በእስልምና አስተዳደር ሥር ያልዋለ የጦርነት ቀጣና የሚጠራበት መጠሪያ ነው።

ዳር አል-ኢስላም፡— በእስልምና ቍጥጥር ሥር የዋለ እስላማዊ አካባቢ የሚጠራበት ስም ነው።

ዳዕዋህ፡— ሰዎች የእስልምናን ሃይማኖት እንዲቀበሉ የሚደረግ ጥሪ ነው።

ዳውላህ፡— በአንድ አካባቢ የሙስሊሞች የፖለቲካ የበላይነት እንዲሰፍን ማድረግ ወይም ማረጋገጥ ማለት ነው።

ዚክር፡— ትውስታ ማለት ነው። ሱፊ ሙስሊሞች በጸሎት ጊዜ የአላህን ስም ለማወደስ/ለማውሳት ዝማሬ ያቀርባሉ።

ዚሚ፡— በሙስሊም አስተዳደር ሥር የደኅንነት ከለላ የተሰጣቸው የማኅበረሰብ ክፍሎችን የሚያመለክት ስያሜ ሲሆን፣ የዚህ መብት ተጠቃሚዎች ክርስቲያኖችና አይሁዶች ናቸው፡፡

ዲን፡— ሃይማኖት ማለት ነው፡፡

ዱአ፡— መደበኛ በሆነው በሃይማኖታዊ ጸሎት (ሰላት) ውስጥ የማይመደብ፣ በዐረብኛም ሆነ በሌሎች ቋንቋዎች መቅረብ የሚችል፣ ሙስሊሞች እግዚአብሔርን ለመማጸን በእግዚአብሔር ፊት የሚያቀርቡት የጸሎት ዐይነት ነው፡፡

ፋናአ፡— ሱፊ ሙስሊሞች አምላክ ዘንድ ለመቅረብ ሲፈልጉ የሚያካሂዱት ጉዞ ነው፡፡

ፋቲሐ፡— የቁርአን የመክፈቻ ጸሎት ሲሆን፣ ሙስሊሞች ሰላት ሲሰግዱ በእያንዳንዱ ስግደት ይደጋግሙታል፤ ፋቲሐ የቁርአን የመጀመሪያው ምዕራፍ መጠሪያም ነው፡፡

ፋትዋ፡— ሕጋዊ በሆነ የሙስሊም ባለሥልጣን የሚወሰን ሕጋዊ ውሳኔ ነው፡፡

ፍቅህ፡— የእስልምና ሕግ ሳይንስ፡፡

ሐድ፡— በተግባር ላይ ካልዋሉ ቅጣት የሚያስከትሉ የተከለከሉ ገደቦች፡፡

ሐዲስ፡— የነቢዩ መሐመድን ንግግሮች፣ አባባሎችና የኑሮ ዘይቤ የያዙ መጻሕፍት መጠሪያ ነው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት ከቁርአን ቀጥሎ ለሃይማኖታዊ መመሪያነት ያገለግላሉ፡፡

ሐጅ፡— በዓመት አንድ ጊዜ ወደ መካ የሚደረግ ሃይማኖታዊ ጉዞ ነው፡፡ የሐጅ ጉዞ ከአምስቱ የእስልምና ሃይማኖታዊ መሠረቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

ሐሳበ፡— የተፈቀዱ ተግባራት፡፡

ሐኒፍ፡— ከእስልምና በፊት የአብርሃምን አምላክ ያመልኩ የነበሩ ዐረቦች መጠሪያ ነው፡፡

ሐራም፡— የተከለከሉ ተግባራት፡፡

ሒጅራ፡— መሐመድ በ622 ዓ.ም ከመካ ወደ መዲና ያደረጉት ጉዞ መጠ ሪያ ሲሆን፣ ይህም ለእስልምና የዘመን አቈጣጠር መጀመሪያ ነው፡፡

ኢብሊስ፡— የክፋት ሁሉ ምንጭ የሆነው የሰይጣን መጠሪያ ነው፡፡

ኢድ አል-አድሐ፡— በሐጅ ጉዞ ሥነ ሥርዐት ወቅት በመጨረሻዎቹ አራት ቀናት የሚከበር በዓል ነው፡፡ በዚህ በዓል ወቅት ሙስሊሙ አብርሃም



ልጁን እስማኤልን መሥዋዕት አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት በማቅረብ ላይ እያለ፣ እግዚአብሔር በእስማኤል ፈንታ የመሥዋዕቱን በግ አዘጋጀ የሚለውን ታሪክ የሚዘክር ክብረ በዓል ነው፡፡

ኢድ አል-ፈጥር፡— ሙስሊሞች በረመዳን ጾም ማብቂያ ጊዜ ለሦስት ቀናት የሚያከብሩት በዓል ሲሆን፣ ቁርአን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ ስጦታ መሆኑንም ያስባሉ፡፡

ኢህራም፡— የሐጂ ተጓዦች ራሳቸውን ለሐጂ ጉዞ መለየታቸው፡፡

ኢጃዝ፡— ቁርአን በተአምራዊ ሁኔታ የተገለጠ መለኮታዊ ቃል ስለሆነ፣ እርሱን የሚመስል ቁርአን ማንንም መጻፍ ወይም መፍጠር አይችልም፣ የሚል አስተምህሮ ነው፡፡

ኢጅማዕ፡— የእስልምናን ሥርዐተ አምልኮዎችና ሕጎችን በተመለከተ ስምምነት ላይ መድረስ ማለት ነው፡፡

ኢጅቲሐድ፡— የቁርአንን ትርጕም ለማብራራትና በሕይወት ተግባራዊ ለማድረግ የግል ጥረትንና ዕውቀትን መጠቀም ማለት ነው፡፡

ኢማም፡— የጸሎት መሪ ማለት ነው፡፡ በሺአ ሙስሊሞች ዘንድ የማኅበረሰቡም መሪ ኢማም ተብሎ ይጠራል፡፡

ኢማን፡— እምነት፡፡

ኢንጂል፡— ወንጌል ማለትም መልካም የምሥራች ማለት ነው፡፡ በመሲሑ በኢየሱስ በኩል የተገለጠው የወንጌል መልእክት ማለት ነው፡፡

ኢሳ፡— በቁርአን ለኢየሱስ የተሰጠ የመጠሪያ ስም፡፡

እስልምና፡— መሐመድ ያስተማረው ሃይማኖት መጠሪያ ሲሆን፣ የቃሉ ጥሬ ትርጕም ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት ወይም ሰላም ማለት ነው፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮች ደግሞ ሙስሊሞች ተብለው ይጠራሉ፡፡

ኢስማ፡— መሐመድ ኀጢአት የለባቸውም የሚለው አስተምህሮ መጠሪያ፡፡

ኢስናድ፡— በሐዲስ ውስጥ ከሚገኙ ሁለት ክፍሎች ውስጥ አንዱ ሲሆን፣ ነቢዩ መሐመድ የተናገሯቸው ንግግሮች በጽሑፍ እስከ ተዘጋጁበት ጊዜ ድረስ በአፈ ታሪክ መልክ ያስተላለፉትን የሰዎች ስም ዝርዝር የያዘው ክፍል ነው፡፡

ኢስራዕ፡— መሐመድ በአንድ ምሽት ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረጉት ተአምራዊ ጉዞ መጠሪያ ነው፡፡

ጃሂሊያ፡— ከእስልምና ሃይማኖት መጀመር በፊት በዐረብያ የነበረውን የጨለማ ዘመን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡

ጅሐድ:— የአላህን ፈቃድ በመከተል የእስልምናን እምነት ከጥቃት ለመጠበቅ የሚካሄደውን ትግል/ጦርነት የሚያመለክት ቃል ነው:: ትግሉ የእስልምናን ሃይማኖት ካልተቀበሉ ወይም ከሰይጣን ወይም ደግሞ ከራስ ነፍስ ጋር የሚደረግ ትግል ሊሆን ይችላል:: አንዳንዴም ጅሐድ እንደ ስድስተኛ የእስልምና ሃይማኖት መሠረታዊ ሕግ ተደርጎ ይቈጠራል::

ጂኒ:— መንፈስ ማለት ሲሆን፣ ርኩሳንንም ሆነ ቅዱሳን መናፍስትን የሚያመለክት ቃል ነው::

ካዕባ:— በመካ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቤት መጠሪያ ሲሆን፣ ቅዱስ የሆነው ጥቁር ድንጋይ ያለበትን ስፍራ ሁሉ ያካትታል::

ኸሊፋ:— ሁሉም ሕዝብ በምድር ላይ የእግዚአብሔር ወኪል/ኸሊፋ ሆኖ የማገልገል ኀላፊነት አለበት:: እንዲሁም ኸሊፋ ማለት ከመሐመድ ሞት በኋላ የሙስሊሙን ማኅበረሰብ የሚመራው መሪ የሚጠራበት ስም ሆኖ ያገለግላል::

ሚህራብ:— በመስጊድ ውስጥ የሰላት አቅጣጫን የሚያሳይ ቦታ ነው::

ሚዕራጅ:— መሐመድ ሙስሊሞች በቀን ምን ያህል ጊዜ መስገድ እንዳለባቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ መመሪያን ለመቀበል ወደ ሰማይ ያደረጉት ጉዞ ነው::

ሙስሊም:— የእስልምና እምነት ተከታይ እንዲሁም በአላህ የሚያምን ሰው መጠሪያ ነው::

ነቢይ:— ከእግዚአብሔር የተላከ ማለት ነው::

ቀድር:— የእግዚአብሔር ቅድመ ውሳኔ ማለት ነው::

ቃዲ:— የሙስሊማኑን ሕግ ማለትም ሸሪአን የሚተረጉም ዳኛ ማለት ነው::

ቂብላ:— ሙስሊሞች ጸሎት የሚያደርሱበት አቅጣጫ::

ቂያስ:— ስለ እስልምና ሕጎች ውሳኔ ለማሳለፍ ይረዳ ዘንድ በቁርአን ወይም በሐዲስ ውስጥ የተገለጡትን ምሳሌዎች በመጠቀም መወሰን ማለት ነው::

ረከአ:— በስግደት (በሰላት) ሰዓት ለስግደት መቆምን፣ መጐንበስንና መንበርከክን የሚያጠቃልል ሥርዐተ ስግደት ነው::

ረሱል:— የእግዚአብሔር መልእክተኛ/ነቢይ እንዲሁም ቅዱስ ቃሉን የሚገልጥ ሰው::

ሰላት:— በቀን አምስት ጊዜ የሚሰገድ ሃይማኖታዊ ጸሎት ነው:: እንዲሁም በስግደቱ ጊዜ የአማኙ ሕይወት አጠቃላይ ለአላህ መገዛቱን በአካላዊ እንቅስቃሴ ይገለጣል::



ሰውም:— በረመዳን ወር የሚጾም ጾም ነው::

ሸሀዳ:— ከአላህ በቀር አምላክ የለም፤ እንዲሁም መሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው በማለት መመስከር::

ሸሪአ:— በቁርአን፣ ከሐዲስ፣ ከኢጅማና ከቂያስ የተዘጋጀ የእስልምና እምነት መተዳደሪያ ሕግ::

ሺአ:— ከእስልምና ቡድኖች አንዱ ሲሆን፣ ሺአዎች የሙስሊሙን ማኅበረሰብ መምራት ያለባቸው የመሐመድ የአጐት ልጅ የሆነው አሊ ቢን አቡ ጣሊብና የእርሱ ዘሮች ናቸው የሚል እምነት አላቸው:: በዓለም ካለው የሙስሊም ቍጥር ከመቶ እጅ ዐሥር እጅ የሚሆኑት ሺአ ሙስሊሞች ሲሆኑ በብዛት የሚገኙትም በኢራን አገር ነው::

ሽርክ:— ለእግዚአብሔር አጋር በመፈለግ ለእግዚአብሔር እኩያ አለው ማለት ሲሆን፣ ይህ ዐይነቱን ኀጢአት የፈጸመ ሰው ለኀጢአቱ ሥርየት አያገኝም::

ሹራ:— ወደ ውሳኔ የሚያደርስ ምክክር

ሲሲላ:— የሱፊ የጸሎት ሰዎች መንፈሳዊ ምሥጢራት የሚያገኙበት የመንፈሳዊ ሥልጣን ቀለበት/ዑደት ነው::

ሱፊ:— ከእስልምና ቡድኖች መካል ከእግዚአብሔር ጋር መለኮታዊ ኅብረት ለማድረግ ፍላጎት ያላቸው ክፍሎች::

ሱና:— የነቢዩ መሐመድ መንገድ::

ሱኒ:— ከሺአ ሙስሊሞች ጋር ሲነጻጸሩ ከፍተኛ ቍጥር ያላቸው የኦርቶዶክስ እስላም ክፍሎች ናቸው::

ሱራ:— የቁርአን ምዕራፍ::

ተክቢር:— አላህ ትልቅ ነው (አላሁ አክበር) ብሎ መናገር::

ጣሪቃሪ:— የሱፊ ሙስሊሞች አንድ ክፍል::

ተውራት:— ለሙሴ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠው መልእክት (መጽሐፍ) ተውራት በመባል ይጠራል:: ሙስሊሞች ተውራት ክርስቲያኖች ቶራህ የሚሏቸው አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት (ብሔረ ኦሪት) ናቸው:: ቁርአን፣ ተውራት የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ያረጋግጣል::

ትውሂድ:— የእግዚአብሔር አንድነትና ፈቃድ ማለት ነው::

ኡስማ:— የእስልምና ሕግ ምሁራን::

ኡማያዶች:— የመጀመሪያዎቹ ካሊፋቶች ሲሆኑ ከ661-750 ዓ.ም የሙስሊሙን ማኅበረሰብ መርተዋል::

ኡማ:— የሙስሊም ማኅበረሰብ::

ወሐቢያ:— በ1787 ዓ.ም የሞተው የዐረብ ተሐድሶ መሪ የኢብን አብድ አል-ወሐብ ደቀ መዛሙርት መጠሪያ ነው:: ይህም የተሐድሶ እንቅስቃሴ በሳውዲ መንግሥት የሚደገፍና የሚደራጅ ነው:: በዚህ ዘመን ባለው በዓለም ዐቀፍ የእስልምና እንቅስቃሴ ላይ ጉልህ ስፍራ አለው::

ወሊ/አወሊያ:— የእግዚአብሔር ጓደኛ ወይም ባልንጀሮች ማለት ነው:: ቅዱሳን ሰዎች በዚህ ስም ይጠራሉ:: ይህ አመለካከት ለሱፊ ሙስሊሞች እምነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው::

ዘቡር:— ሙስሊሞች ለዳዊት የተሰጠ መልእክት ወይም መዝሙረ ዳዊት ነው ይላሉ::

ዘካት:— ምጽዋት መስጠት፤ ከእስልምና አምስቱ ሃይማኖታዊ ትእዛዛት መካከል አንዱ

ዘምዘም:— ከመካ መስጊድ አጠገብ የሚገኝ ጉድጓድ ሲሆን፣ አጋር ለተጠማው ልጅዋ ለእስማኤል ከዚህ ጉድጓድ ውሃ ቀድታ እንዳጠጣችው ይታመናል::

## የክርስትና ቃላቶች

አናባፕቲስት:— ከዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ አውሮፓ ክርስቲያኖች መካከል መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት የተጀመረ እንቅስቃሴ ነው:: መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን መለየት እንዳለባቸው እንዲሁም የውትድርናን አገልግሎት መስጠት ከክርስቶስ አስተምህሮ ጋር የሚቃረኑ ተግባራት እንደ ሆኑ ያምናሉ:: የሕፃናትን ጥምቀት ስለሚቃወሙ፣ ሰዎች የውሃ ጥምቀት መውሰድ ያለባቸው በክርስቶስ አምነው ሲለወጡና ለመለወጣቸው ምስክርነት ሲሰጡ ብቻ ነው የሚል አቋም አላቸው::

ሐዋርያዊ ተዋረድ:— በካቶሊክና በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የጳጳሳት ሥልጣን መሠረቱ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት በተዋረድ በመጣው መንፈሳዊ ሥልጣን እንደ ሆነ ይታመናል:: በኤፒስኮፓል ቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ የእምነት አቋም አለ::

ሐዋርያት:— የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሲሆኑ አብዛኞቹ በአካል ሥጋ ከክርስቶስ ጋር የነበሩ ናቸው::



ዕርገት:— ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ ከአርባ ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እያዩት ወደ ሰማይ ዐረገ:: ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ደቀ መዛሙርቱ ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱና ወንጌል እንዲሰብኩ አዞአቸዋል::

ሥርየት:—ለኀጢአት ይቅርታ የሚቀርብ መሥዋዕት

ጥምቀት:— አንድ ሰው ከክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ጋር መቀላቀሉን በውሃ በመጠመቅ የሚያሳየው ምልክት:: የዐዋቂዎችን ጥምቀት የሚቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት የሚያጠምቁት አንድ ሰው ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አምኖ ሲቀበል ብቻ ነው:: ነገር ግን በሕፃናት ጥምቀት የሚያምኑ አብያተ ክርስቲያናት፣ ጥምቀት የሰው ልጆች ይቅርታ የሚያገኙበትና ሕፃናትን ጨምሮ ሰዎችን ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት የሚጠራው የእግዚአብሔር ጸጋ ተምሳሌት እንደ ሆነ ያምናሉ::

ጳጳስ:— የቤተ ክርስቲያናት ኀላፊነት የተሰጠው የቤተ ክርስቲያን መሪ ማለት ነው::

ካቶሊክ:—የቃሉ ጥሬ ትርጉም ዓለም ዐቀፋዊ ቤተ ክርስቲያን ማለት ሲሆን፣ በዓለም ከአንድ ቢሊየን በላይ ምዕመን ያላት የታላቅዋ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መጠሪያም ነው::

ክርስቶስ:— ክርስቶስ ማለት መሲሕ ወይም የተቀባ ማለት ነው:: ክርስቶስ የሚለው ቃል ግሪክ ሲሆን ከአማርኛው ስያሜ ጋር አንድ ዐይነት ነው::

የክርስቲያናዊ ግዛት:— በምዕራቡ ዓለም ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት አንድነት ፈጥረው ነበር:: ይህም ዐይነቱ የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ጥምረት በእስልምናው ሃይማኖት ዳር አል-ኢስላም በመባል ከሚጠራው ሐሳብ ጋር የሚመሳሰል ነው::

ቤተ ክርስቲያን:— በኢየሱስ ክርስቶስ መሲሕነትና ጌትነት ያመኑ የክርስቲያኖች ኅብረት::

የኒቂያ ጉባኤ:— በ325 ዓ.ም ስለክርስቶስ ማንነት ክርስቲያኖች ምን ዐይነት እምነት ሊኖራቸው እንደሚገባና በሌሎች ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ለመምከር ኒቂያ በተባለ ስፍራ የተደረገ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ነው:: በስብሰባው ማጠቃለያ ላይ የእምነት አቋም በማውጣት የተጠናቀቀ ሲሆን የካቶሊክ፣ የኦርቶዶክስና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ይህን መሠረተ እምነት ከሙሉ ልባቸው ይቀበላሉ::

ቈስጠንጢኖስ:— የምዕራብ ሮማ ግዛት መሪና በ313 ዓ.ም ክርስትናን በሮም ግዛት ውስጥ ሕጋዊ ሃይማኖት እንዲሆን ያደረገ መሪ ነው:: መንግሥትና ቤተ ክርስቲያንን ለማጣመር የታገለ ሰው ነው::

ቃል ኪዳን፡— በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው። እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር የቃል ኪዳን ግንኙነት ለማድረግና ቃል ኪዳኑን የሚጠብቁትን ሰዎች ለመባረክ ተስፋ ይሰጣል።

ዲያቆን፡— ጳጳሱን ወይም ካህኑን የሚያግዝ አገልጋይ ነው።

ደቀ መዝሙር፡— ተከታይ ወይም ተማሪ ማለት ሲሆን፣ ኢየሱስን የሚከተሉና አብረውት የሚያገለግሉ ዐሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ነበሩት።

ኤል/ኤሎሂም፡— አብርሃም እግዚአብሔርን ይጠራበት የነበረ ስም ነው። አላህ የሚለው ዐረብኛ የእግዚአብሔር ስም፣ ከዕብራይስጡ ኤል/ኤሎሂም ከሚለው የእግዚአብሔር ስም ጋር ተመሳሳይ ነው።

ቅዱስ ቁርባን/የጌታ ራት፡— ከመሲሑ ከኢየሱስ ጋር ባለን ኅብረት በኩል ስለተገለጠልን የእግዚአብሔር ጸጋ ለእግዚአብሔር ክብር የምንሰጥበት ሃይማኖታዊ ሥርዐት ነው። አብዛኞቹ የክርስቲያን ጉባኤዎች በየጊዜው የክርስቶስን ሕይወት፣ ስቅለትና ትንሣኤ መታሰቢያ ዳቦና የወይን ጭማቂ በጋራ ይወስዳሉ።

ሽማግሌ፡—ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማኅበረ ምዕመን መሪ ወይም አገልጋይ።

መልእክቶች፡— የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ለቤተ ክርስቲያናት የጻፉዋቸው ደብዳቤዎች።

ምጽአት፡— ወደ ፊት ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ ወደዚህች ምድር ሲመጣ፣ የመጨረሻ ፍርድ የሚሰጥበትና፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ለዘላለም የሚመሠረትበት ጊዜ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች፡— ክርስቶስን በማመን አዲስ ፍጥረት የሆነው አማኝ በሕይወቱ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ይታያሉ። ለምሳሌ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ወዘተ።

ኤደን ገነት፡— አዳምና ሔዋን በኀጢአት ከመውደቃቸው በፊት ይኖሩበት የነበረ ስፍራ።

ወንጌል፡— ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወት፣ አገልግሎት፣ ትምህርት፣ ሞትና ትንሣኤ የሚተርክ መልካም የምሥራች ማለት ነው።

ወንጌላት፡— በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለመሲሑ ኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት የሚተርኩት አራቱ ወንጌላት ማለትም ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ወንጌልን የሚያመለክት ቃል ነው።

ታላቁ ተልእኮ፡— ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰብኩ የሰጣቸው የመጨረሻው ትእዛዝ።



መንፈስ ቅዱስ፡— የእግዚአብሔር መንፈስ ሲሆን፣ የመሲሑ ኢየሱስ አገልግሎት ቀጣይነት እንዲኖረው፣ የሰዎች ልብ ለእውነት ምላሽ እንዲሰጥ በማዘጋጀት እንዲሁም የክርስቶስን አስተምህሮ መሠረታቸው አድርገው ለመኖር የሚፈልጉትን ሰዎች ኀይል በመስጠት ይሠራል።

ያለና የሚኖር፡— እግዚአብሔር ለሙሴ በኮሬብ ተራራ በእሳት ነበልባል በእሾኽ ቍጥቋጦ ውስጥ ሲገለጥለት ራሱን ያሳወቀበት ስም ነው። የነገረ መለኮት ምሁራን ይህ ስም የዕብራይስጡ ያህዌህ የሚለውን የእግዚአብሔር ስም ይገልጻል ይላሉ።

አማኑኤል፡— እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ሲሆን፣ መልአኩ ገብርኤል ለድንግል ማርያም ስለኢየሱስ መወለድ ሲያበስርላት የኢየሱስ ስም አማኑኤል እንደሚባል ተናግሮአት ነበር።

ተሰግዎ (ምስጢረ ሥጋዌ)፡— ሥጋ መልበስ ማለት ነው። በድንግል ማርያም ልጅ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በሙላት ተገልጦአል የሚለውን መሠረተ እምነት ያመለክታል።

የኢየሩሳሌም ጉባኤ፡— የቀድሞ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከአሕዛብ ወገን የሆኑ አማኞች ከአይሁድ ባህል እና ከብሉይ ኪዳን ሥርዐቶች አንጻር እንዴት መኖር እንዳለባቸው ውሳኔ ያሳለፈ ስብሰባ ነው። በስብሰባው ፍጻሜ አሕዛብ የራሳቸውን ባህል ጠብቀው መኖር እንደሚችሉ ነገር ግን ከአንዳንድ መጥፎ ከሆኑ ተግባራት እንዲታቀቡ ውሳኔ አሳልፎአል። ስለስብሰባው አጠቃላይ ገጽታ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ላይ ተጠቅሶአል።

ኢየሱስ፡— የመሲሑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስም ነው። ትርጕሙም፣ "እግዚአብሔር ያድናል" ማለት ነው።

ዮሴፍ፡— የኢየሱስ እናት የሆነችውን ድንግል ማርያምን ያገባ ሰው ነው። ዮሴፍ አናጺ የነበረ ሲሆን፣ ኢየሱስም በመጀመሪያዎቹ ዘመናት የአናጺነት ሥራ ሳይሠራ አይቀርም።

የእግዚአብሔር መንግሥት፡— የእግዚአብሔር አስተዳደር ያለበት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። ክርስቲያኖች ክርስቶስ በሰው ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት በሙላት ተገልጦአል ብለው ያምናሉ። የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን ተጀምሮአል ነገር ግን የሚፈጸመው በክርስቶስ ምጽአት ነው።

የእግዚአብሔር በግ፡— ከመሲሑ ከኢየሱስ ስሞች ውስጥ አንዱ ነው። ይህም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለሰዎች ሁሉ ኀጢአት መሥዋዕት ሆኖ መሞቱን የሚያመለክት ሲሆን፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ ነው

ከሚለው ትርጓሜ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ሥርዐቶች በብዙ ሃይማኖቶች ውስጥ አሉ። ምክንያቱም ለአብርሃም ልጅ ምትክ እንዲሆን የመሥዋዕቱ በግ እንደ ተሰጠ ሁሉ፣ ለሰዎች ምትክ ይሆኑ ዘንድ እንስሳት መሥዋዕት ይደረጋሉ። ክርስቲያኖች ሰው ሁሉ ኀጢአተኛ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች እንደ ሆነ፣ ነገር ግን ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ በእኛ ፈንታ ስለታረደ ከፍርድ ነጻ ሆኖ ምሕረትን እንደሚያገኝ ያምናሉ።

መሲሕ:— በእግዚአብሔር የተቀባ ማለት ነው። ኢየሱስ መሲሕ ነው።

የሲና ተራራ:— እግዚአብሔር ዐሥርቱን ትእዛዛት ለእስራኤል የገለጠበትና የቃል ኪዳን ሕዝቡ እንዲሆኑ ጥሪ ያደረገበት ተራራ ነው።

ናዝሬት:— ክርስቶስ የልጅነት ዘመኑን የኖረበት ስፍራ ነው።

አዲስ ኪዳን:— የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛው ግማሽ ክፍልና ከመሲሑ ኢየሱስ መወለድ በኋላ የተጻፈ መጽሐፍ ነው።

ብሉይ ኪዳን:— የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ግማሽና ከመሲሑ ከኢየሱስ ልደት በፊት የተጻፈ መጽሐፍ ነው።

ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን:— ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር በብዙ መልክ የምትመሳሰል ቤተ ክርስቲያን ስትሆን፣ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበራትን ኅብረት ያቆመችው በ1054 ዓ.ም ነው። አብዛኛዎቹ የምሥራቁ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያናትና የምዕራብ አውሮፓ ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናት ተብለው ይጠራሉ።

ፋሲካ:— በፈርዖን ዘመን እግዚአብሔር በጽኑ ክንዱ እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነጻ ያወጣበትን ታሪክ ለማሰብ አይሁዶች የሚያከብሩት በዓል ነው። ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ እየመራ ከግብፅ ምድር ሲወጣ እግዚአብሔር ተአምራትን እየሠራ ሕዝቡን ነጻ አውጥቶአል። እስራኤላውያን ነጻ የወጡበት ምሽት ፋሲካ ተብሎ ይጠራል። ምክንያቱም በዚያች ምሽት የሞት መልአክ የግብፃውያንን የበኩር ልጆች ሁሉ ሲገድል፣ የበግ ደም በመቃኑ ላይ የተቀባው የእስራኤላውያኖቹ ቤት ግን ከዚህ ሞት ማምለጥ ችሏል።

ጳውሎስ:— የትንሣኤው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገናኘው ድረስ ክርስቲያኖችን የሚያሳድድ ሰው ነበር። በክርስቶስ ኢየሱስ ከአመነ በኋላ የቤተ ክርስቲያን መሪና ከአይሁድ ወገን ያልሆኑ ሰዎች የመሲሑን መንገድ እንዲከተሉ በብርቱ ይፈልግ የነበረ ሐዋርያ ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉት በርካታ መልእክቶች ጳውሎስ የጻፋቸው ናቸው።



ጴንጤቈስጤ:— እህል በሚሰበሰብበት ጊዜ የሚከበር የአይሁድ በዓል ሲሆን፣ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ በዚሁ በዓል ቀን መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኀይል በክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ላይ ወረደ፤ ቤተ ክርስቲያንም በዚያች ቀን ተመሠረተች።

ጴጥሮስ:— የክርስቶስ ደቀ መዝሙርና ቍልፍ ከሆኑት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውስጥ አንዱ ነው። ቤተ ክርስቲያንን አይሁድ ወዳልሆኑት ሕዝቦች በማስፋፋቱ ሂደት ውስጥ ትልቅ ሚና ተጫውቶአል።

የእስራኤል ሕዝብ:— በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ እነርሱም የአብርሃምና የይስሐቅ ዘሮች ናቸው።

ሊቀ ጳጳስ:— የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪ።

ነቢይ:— የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገርና ሕዝቡን ወደ ንስሓ የሚጠራ በእግዚአብሔር የተላከ ሰው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን እግዚአብሔር ነቢያትን ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲጽፉ በማነሣሣት መገለጥን ይሰጣቸው ነበር።

ፕሮቴስታንት:— በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተለይቶ የወጣ የክርስቲያኖች ቡድን ነው። ፕሮቴስታንቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣንና ድነት በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ በነጻ/በጸጋ የተሰጠ ስጦታ ነው በሚሉት ርእሰ ጒዳዮች ላይ ትኩረት ይሰጣሉ።

መዝሙራት:— ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መካከል በግጥም የቀረበ መጽሐፍ ነው። ዳዊት እነዚህን ግጥሞች ከጻፉት ሰዎች ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።

ነጻ መውጣት:— አንድን ሰው ከአደጋ፣ ከጥፋት ወይም ከእስር ቤት ዋጋ ከፍሎ ማዳን ማለት ነው። ኀጢአትና ሰይጣን በእኛ ላይ ካመጡብን ጥፋት ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ድነት የሚያስፈልገውን ዋጋ ሁሉ በመክፈል አዳነን።

ንስሐ:— አቅጣጫን መቀየር ወይም ከራስ ወዳድነትና ከኀጢአት መንገድ መሲሑን ለመከተል መወሰን ማለት ነው።

መሥዋዕት:— ብዙ ሃይማኖቶች ኀጢአታቸው ይቅር እንዲባልላቸው እንስሳ ወይም የእህል መሥዋዕት ለአምላኮቻቸው ያቀርባሉ። በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ እንደ ተሰዋ ተጽፎአል።

ድነት:— የኀጢአት ይቅርታና የዘላለም ሕይወት ነው:: ደኅንነት ዕረፍትና ሰላም ነው::

ሰይጣን:— ኢብሊስ ከሚለው የዐረብኛ ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው:: ሰይጣን ውሸታም ነው::

አዳኝ:—የኢየሱስ ስም ነው:: አዳኙ እኛን ከኀጢአታችን የሚያድነን፣ ይቅርታን የሚያደርግልን፣ አሁን ሰላማዊ የሆነ እንዲሁም በሰማይ የዘላለምን ሕይወት የሚሰጠን ነው::

ዳግም ምጽአት:— ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻው ፍርድ ጊዜ ሙታን ሲነሡና የእግዚአብሔርን መንግሥት ለዘላለም ፍጹም ለማድረግ ዳግም እንደሚመለስ ቃል ገብቶአል:: በዚያ ጊዜ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይመሠረታሉ::

የተራራው ስብከት:— ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በተራራ ላይ ስለ ጽድቅ ኑሮ ያስተማረው ትምህርት ነው::

የእግዚአብሔር ልጅ:— በመሲሑ ውስጥ እግዚአብሔር በሙላት ተገልጦአል ከእግዚአብሔር ጋርም ፍጹም የሆነ ኅብረት አለው::

ቤተ መቅደስ:— ለመጀመሪያ ጊዜ በንጉሥ ሰሎሞን የተገነባው የአይሁድ የአምልኮ ስፍራ ስም ነው::

ዐሥርቱ ትእዛዛት:— እግዚአብሔር ለሙሴ በሲና ተራራ ላይ ሰዎች ትክክለኛ ሥነ ምግባር እንዲኖራቸው አስቦ የሰጠው ሕግ ነው::

ኪዳን:— ስምምነት ማለት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ኪዳንንና ብሉይ ኪዳንን የያዘ መጽሐፍ ነው::

ቶራህ:— የመጀመሪያዎቹ አምስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ናቸው::

ሥላሴ:— ክርስቲያኖች ፈጣሪ፣ አዳኝና መንፈስ (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) በሆነው አንድ አምላክ ውስጥ ባሉት ሦስት አካላት መካከል ያለውን የፍቅር ግንኙነት ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ቃል ነው::

ድንግል ማርያም:— የኢየሱስ ክርስቶስ እናት::

ያህዌ:— እግዚአብሔር ለሙሴ በእሳት አምሳል በእሾኽ ቍጥቋጦ ውስጥ "ያለና የሚኖር እኔ ነኝ" ብሎ ስሙን ለሙሴ ሲናገር የተናገረውን ሐሳብ ለመግለጥ ጥቅም ላይ የዋለው የእግዚአብሔር ስም ነው::



# ዋቢ መጻሕፍት
## ከአጫጭር ማብራሪያዎች ጋር

**<u>የቅኝት/አሰሳ መጻሕፍት</u>**


Abdalati, Hammaudah. *Islam in Focus.* Indianapolis, Ind.: American Trust Publications, 1975. Reprinted. ሙስሊሞች እስላማዊውን አስተምህሮና ሕይወት ጠንቅቀው እንዲረዱ የሚያግዝ መሠረታዊ መጽሐፍ ነው::

Chittick, William C., and Sachiko Murata. *The Vision of Islam.* St. Paul: Paragon House, 1994. የእስልምናን ሃይማኖት ከሱፊዎች አስተምህሮ አንጻር የሚመረምር መጽሐፍ ነው::

Denny, Frederick Mathewson. *An Introduction to Islam.* 2nd ed. New York: Macmillan, 1994. በብዛት በኮሌጅ ደረጃ በመማሪያ መጽሐፍነት የሚያገለግል ሲሆን በርካታ ርእሰ ጉዳዮችን ይዳስሳል::

Endress, Gerhard. *An Introduction to Islam.* New York: Columbia University, 1987. ከነገረ መለኮት ይልቅ ለታሪክ ትኩረት ይሰጣል::

Esposito, John L. *Islam: The Straight Path.* 3rd ed. New York: Oxford University Press, 1998. ሙስሊም ባልሆነ ሰው የተጻፈ የቅኝት/የአሰሳ መጽሐፍ ነው::

Hamidullah, Muhammad. *Introduction to Islam.* Kuwait: International Islamic Book Center, n.d. ከላይ ከተጠቀሰው ከሃሙዳህ መጽሐፍ ይልቅ ሰፊ ማብራሪያ ይሰጣል::

Jomier, Jacques. *How to Understand Islam.* Trans. From French by John Bowden. London: SCM Press, 1989. መጽሐፉ በመጀመሪያ በፈረንሳይኛ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን፣ ክርስቲያኖች ከእስልምና ሃይማኖት ጋር እንዲተዋወቁ የሚረዳ የቅኝት መጽሐፍ ነው::

Miller, Roland E. *Muslim Friends, Their Faith and Feeling: An Introduction to Islam.* St. Louis: Concordia, 1996. እስልምናን ከክርስቲያኖች አንጻር የሚመለከት መጽሐፍ ነው::

Rahman, Fazlur. *Islam.* 2nd ed. Chicago: University of Chicago Press, 1979. ወደ ዘመነኝነት ባጋደለ ፓኪስታናዊ ምሁር የቀረበ ዘገባ ነው::

Renard, John. *Seven Doors to Islam: Spirituality and the Religious Life of Muslims*. Berkeley: University of California Press, 1996, and the companion volume *Windows on the House of Islam: Muslim Sources on Spirituality and Religious Life*. Berkeley: University of California Press, 1998.

Rappin, Andrew. *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices*. 2nd ed. London: Routledge ለማስተዋል በሚረዳ መልክ የቀረበ ሲሆን፣ እስላማዊ የትመጣሁን (origin) በስፋት ይመረምራል::

Robinson, Neal. *Islam: A Concise Introduction*. Washington, D.C.: Georgetown University, 1999. ክርስቲያኖች መጠየቅ ለሚገባቸው ጥያቄ ትኩረት ይሰጣል::

Schimmel, Annemarie. *Deciphering the Signs of God: A Phenomenological Approach to Islam*. Edinburgh: Edinburgh University Press, 1994

Waines, David, *An Introduction to Islam*. Cambridge: Cambridge University Press, 1995. እጅግ ጠቃሚ የሆነ ታሪካዊ ቅኝት ያቀርባል::

## የመሐመድ ሕይወት

Guillaume, A. *The Life of Muhammad: A Translation of Ishaq's Sirat Rasul Allaa*. Karachi: Oxford University, 1955. (13th Printing in 1998). በመሐመድ ሕይወት ላይ የቀረበ ዐረባዊ ሥራ ነው::

Haykal, Muhammad Husayn. *The Life of Muhammad*. Trans. I. F. al-faruqi from the Arabic. London: Shorouk International, 1983. በመጀመሪያ በ1985 ዓ.ም የታተመ ሲሆን፣ ዘመናዊ በሆነ ግብፃዊ ሙስሊም የተጻፈ መጽሐፍ ነው::

Lings, Martin. *Muhammad: His Life Based on the Earliest Sources*. Cambridge: The Islamic Texts Society, 2001. ሙስሊሞች ታሪክን በሚተርኩበት መንገድ የሚተርክ ጥሩ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ነው::

Rodinson, Maxime. *Mohammed*. Trans. Anne Carter from the French. London: Penguin, 1971.

Watt, W. Montgomery. *Muhammad, Prophet and Statesman*. London: Oxford University Press, 1961.



## የእንግሊዝኛና የአማርኛ ቁርአን

Ali, Abdullah Yusuf. *The Holy Qur'an*. Lahore 1937. በቆየው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ለበርካታ ጊዜያት የታተመ እንዲሁም ሙስሊሞች በስፋት የሚጠቀሙበት ቅጅ ነው::

Arberry, A. J. *The Koran Interpreted*. London: 1955. በቋንቋ ጥራቱ የእስልምናን ሃይማኖት በሚያጠኑ ሊቃውንት ዘንድ በእጅጉ የሚወደድ መጽሐፍ ቢሆንም፣ የቍጥሮቹ አቀማመጥ በአሁኑ ጊዜ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ ከሚገኘው ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም::

Dawood, N. J. *The Koran*. London: Penguin, 1956. ዘመናዊውን እንግሊዝኛ የሚጠቀም፣ ለማንበብ ቀላል የሆነ፣ በተደጋጋሚነት ለረጅም ጊዜ የታተመ እንዲሁም ሙስሊም ባልሆነ ሰው የተተረጐመ ቅጅ ነው::

Fakhry, Majid. *The Qur'an: A Modern English Version*. Reading, UK: Garnet Press, 1997. ዘመናዊ በሆነ እንግሊዝኛ የተተረጐመ ጥሩ ቅጅ ነው::

Pickthall, Mohammed Marmaduke. *The Meaning of the Holy Qur'an*. እንግሊዛዊ በሆነ ሙስሊም፣ ዘመናዊ ባልሆነ እንግሊዝኛ የተተረጐመ ቅጅ ነው::

ሸኽ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅና ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ፤ ቅዱስ ቁርአን በአማርኛ ትርጕም፤ ሁለተኛ ዕትም፤ አዲስ አበባ፤ ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፤ 1997::

## ቁርአናዊ ጥናት

Cragg, Kenneth. *The Event of the Qur'an: Islam in Its Scripture*. Oxford, UK: Oneworld, 1994.

Cragg, Kenneth. *The Mind of the Qur'an*. London, 1973.

Gätje, Helmut. *The Qur'an and Its Exegesis*. Trans. By Alford T. Welch. Oxford, UK: Oneworld, 1996. የተውጣጡ ጽሑፎችን በአንድ ላይ ያካተተ የቁርአን ማብራሪያ/አንድምታ ነው::

Hawting, G. R., and Abdul-Kadar A. Shereef, eds. Approaches to the Qur'an. London and New York, Routledge, 1993.

Muslim-Christian Research Group (GRIC). *The Challenge of the Scriptures*. Maryknoll, N.Y.: Orbis, 1989. ከሙስሊሞች ጋር ለሚደረግ ውይይት ጥሩ ትምህርት ይሰጣል::

Nelson, Kristina. *The Art of Reciting the Qur'an*. University of Texas, Austin, 1985. የቁርአንን መሠረታዊ ነጥቦች የሚያስተምርና ለመከከለኛ ሙስሊሞች የሚሆን መጽሐፍ ነው።

Parrinder, Geoffrey. *Jesus in the Qur'an*. Oxford, UK: Oneworld Publications, 1995. ቁርአን ስለ ማርያም፣ ስለ ኢየሱስ፣ ስለ ክርስቲያኖችና ስለ ክርስትና የሚያስተምራቸውን ምንባባት ሁሉ የሚመረምር መጽሐፍ ነው።

Rahman, Fazlur. *Major Themes of the Qur'an*. Chicago: Bibliotheca Islamica, 1980. ቁርአናዊ አስተምህሮዎችን የሚያስተምር ጥሩ መጽሐፍ ነው።

Rippen, A., ed. *Approaches to the History of the Interpretation of the Qur'an*. Oxford, UK: Clarendon Press, 1988.

Sherif, Faruq. *A Guide to the Contents of the Qur'an*. Reading, UK: Garnet Publishing, 1995.

Sells, Michael. *Approaching the Qur'an: The Early Revelations*. Ashland. Ore.: White Cloud, 1999. ጥሩ ነገር ግን ያልተሟላ የቁርአን ማጥኛ መጽሐፍ ሲሆን፣ CD-ROM ያካተተ ነው።

Watt, W. Montgomery. *Introduction to the Qur'an*. Edinburgh: University of Edinburgh Press, 1970. በምሁራን ዘንድ ያሉትን ሙያዊ የሆኑ የነገሬ መለኮት ርእስ ጉዳዮችን በአሰሳ መልክ የሚያቀርብ ጥሩ መጽሐፍ ነው።

## ትውፊት(ሐዲስ)

Ali, Maulana Muhammad. *A Manual of Hadith*. London: Curzon Press 1977. በእንግሊዝኛ ቋንቋ የቀረቡት ሐዲሶች ከሃይማኖታዊው ሕግ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው።

Burton, John. *An Introduction to the Hadith*. Edinburgh: Edinburgh: Edinburgh U.P., 1994. የሐዲስን ታሪክና አስተምህሮ በአሰሳ መልክ የሚያቀርብ ሙስሊም ባልሆነ ጸሐፊ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው።

Graham, William. *Divine Word and Prophetic Word in Early Islam*. The Hague: Mouton, 1977.

Siddiqi, M. Z. *Hadith Literature: Its Origin, Development, and Special Features*. Cambridge: Islamic Texts Society, 1993. ሙስሊም በሆነ



ጸሐፊ የተዘጋጀ ጥሩ አሰሳዊ ጥናት ነው። መጽሐፉ ሐዲስን በተመለከተ ለምዕራባውያን ሒስ መልስ ለመስጠት ይሞክራል።

## እስላማዊ ሕግ

Al-Misri, Ahmad ibn Naqib. *Reliance of the Traveller: A Classic Manual of Islamic Sacred Law*. Rev. ed. Trans. And ed. Nuh Ha Mim Keller. Beltsville, Md.: Amana, 1994. በዐሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፉ የሱኒ ምንባባትን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተርጉሞ ያቀረበ መጽሐፍ ነው። እስላማዊ ሕጎች በታሪክ ውስጥ እንዴት ይታዩ እንደ ነበር እንዲሁም አሁንም እንኳ አብዛኛውም ሕዝብ እንዴት እንደሚረዳቸው ለማወቅ ይህን መጽሐፍ ማንበብ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

An-Na'im, Abdullahi A., ed. *Islamic Family Law in a Changing World: A Global Resource Book*. London: Zed Books, 2002. የተለያዩ አገሮችን እስላማዊ ሕግ በአሰሳ መልክ የሚቃኝ መጽሐፍ ነው።

Cook, Michael. *Commanding the Right and Forbidding the Wrong in Islamic Thought*. Cambridge: Cambridge U.P., 2000. በእስላማዊ ሕግ ውስጥ አንድ ሰው ለሌላው ሰው ያለበት ኃላፊነት ምን እንደሚመስል የሚተነትን እንዲሁም እጅግ በርካታ ታሪካዊ ዘገባዎች የቀረቡበት መጽሐፍ ነው።

Coulson, N. J. *A History of Islamic Law*. Edinburgh: U. P., 1964.

Esposito, John L. *Women in Muslim Family Law*. Syracuse, N.Y.: Syracuse U.P., 1982.

Hallaq, Wael B. *A History of Islamic Legal Theories: An Introduction to Sunni Usûl al-Fiqh*. Cambridge: Cambridge U.P., 1997.

Kamali, M. H. *Principles of Islamic Jurisprudence*. 2nd ed. Cambridge: Islamic Texts Society, 1991.

Masud, Muhammad Khalid, Brinkley Messick, and David S. Powers. *Islamic Legal Interpretation: Muftis and Their Fatwas*. Cambridge, Mass.: Harvard University, 1996. ፋትዋን አስመልክቶ ጥሩ ማብራሪያ ይሰጣል።

Omrun, Abdel Rahim. *Family Planning in the Legacy of Islam*. London: Routledge, 1992. ርእስ ጉዳዩ ላይ ሰፊ ማብራሪያ የሚሰጥ መጽሐፍ ነው።

Pearl, David. *A Textbook on Muslim Personal Law*. London: Croom Helm, 1987. በእንግሊዞችና በደቡብ እስያውያን ዐውድ የቀረበ መጽሐፍ ነው።

Schacht, Joseph. *An Introduction to Islamic Law*. Oxford: Oxford U. P., 1964.

Weiss, Bernard G. *The Spirit of Islamic Law*. Athens, Ga.: The University of Georgeia, 1998. እስላማዊ ሕግን በቀላል አቀራረብ የሚያብራራ መጽሐፍ ነው::

## <u>በጦርነት፣ በሰላምና በሰብአዊ መብት ዙሪያ የእስላማዊ ሕግ እይታ</u>

Abu Sulayman, Abdul Hamid A. *Towards on Islamic Theory of International Relations*. Rev. ed. Herndon, Va.: The International Institute of Islamic Thought, 1993.

'Alwani, Taha Jabir al-. *The Ethics of Disagreement in Islam;* Herndon, Val.: The International Institute of Islamic Though, 1994.

Johnson, James Turner, and John Kelsay. *Cross, Crescent, and Sward: The Justification and Limitation of War in Western and Islamic tradition*. New York: Greenwood Press, 1990.

Kelsay, John and James Turner Johnson, ed. *Just War and Jihad: Historical and Theoretical Perspectives on War and Peace in Western and Islamic Traditions*. New York: Greenwood Press, 1991.

Kelsay, John. *Islam and War: The Gulf War and Beyond*. Louisville, Ky.: Westminster/John Knox, 1993.

Khadduri, Majid. *War and Peace in the Law of Islam*. New York: AMS, 1979.

Mawdudi, Abul A'la. *Human Rights in Islam*. Nairobi: The Islamic Foundation, 1976.

Mitri, Tarek, ed. *Religion, Law and Society*. Geneva: WCC Publications, 1995.

Peters, Rudolph. *Jihad in Classical and Modern Islam*. Princeton: Markus Wiener, 1996. መሠረታዊ ምንባባትን ተርጉሞ እንዲሁም አጫጭር የትንታኔ ጽሑፎችን እንዲሁም ጠቃሚ የዋቢ መጻሕፍት ዝርዝሮችን ያካተተ መጽሐፍ ነው::

Peters, Rudolph. *The Doctrine of Jihad in Modern History*. Gravenhage: Mouton, 1979.



Qutb, Sayed. *Islam and Universal Peace*. Riyadh: International Islamic Publishing House, 1991.

Watt, W. Montgomery. *Islamic Political Thought*. Edinburgh U.P.: 1968.

## <u>ሴቶች በእስልምና ውስጥ ያላቸው ቦታ (እንዲሁም ከላይ እስላማዊ ሕግ የሚለውን ይመለከቷል)</u>

Abu-Lughod, Lila. Veiled Sentiments: Honor and Poetry in a Bedouin Society. Berkeley: University of California Press, 1986.

Afkhami, Mahnaz. *Faith and Freedom, Women's Human Rights in the Muslim World*. London: I. B. Tauris Publishers, 1995.

Ahmed, Leila. *Women and Gender in Islam: Historical Roots of a Modern Debate*. New haven, Conn.: Yale U.P. Publications, 1975.

El Saadawi, Nawal. *The Hidden Face of Eve: Women in the Arab World*. London: Zed Books, 1980.

Glaser, Ida, and Napoleon John. *Partners or Prisoners? Christians Thinking About Women and Islam*. Cumbria, UK: Solway, 1998.

Jawad, Haifaa A. *The Rights of Women in Islam: An Authentic Approach*. London: Macmillian Press, 1998.

Khan, Maulana Wahiduddin. *Women in Islamic Shari'ah*. New Delhi: Al-Risala Books, 1995.

Macleod, Arlene, Elowe. *Accommodating Protest: Working Women, the New Veiling, and Change in Cairo*. New York: Columbia U. P., 1991.

Mernissi, Fatima. *Beyond the Veil: Male-Female Dynamics in Muslim Society*. Rev. ed. Indianapolis: Indiana U.P., 1987.

Mernissi, Fatima. *The Harem Within: Tales of a Moroccan Girlhood*. London: Doubleday, 1994.

Nazlee, Sajda. *Feminism and Muslim Women*. London: Ta-Ha, 1996. እስልምና በሴቶች ላይ ያለውን ቀደምት አስተሳሰብ ክሒስ የሚከላከል መጽሐፍ ነው::

Sachiko, Murata. *The Tao of Islam: A Sourcebook on Gender Relationships in Islamic Thought*. Albany, N.Y.: State University of New Yourk Press, 1992.

Shaltut, Mahmoud. *The Qur'an and Women*. Cairo: International Islamic Centre for Population Studies and Research, n.d.

Stowasser, Barbara Freyer. *Women in the Qur'an, Traditions, and Interpretation*. New York: Oxford U.P., 1994.

Wadud-Muhsin, Amina. *Qur'an and Woman*. Kuala Lumpur: Penerbit Fjar Bakti, 1992.

Yamani, Mai. *Feminism & Islam: Legal and Literary Perspectives*. Reading, UK: Ithaca Press, 1996.

## እስላማዊ የሃይማኖት መግለጫ፣ ነገረ መለኮትና ፍልስፍና

Abduh, Muhammad. *The Theology of Unity*. Translated from Arabic by Ishaq Musa'ad and Kenneth Cragg. London: George Allen & Unwin, 1966. አብዱ የግብፅ ዘመናዊ አስተሳሰብን ያራምዱ የነበሩ አንጋፋ ሰው ናቸው::

Caspar, R. *A Historical Introduction to Islamic Theology: Muhammad and the Classical Period*. Rome: Pontificio Istituto di Studi Arabi eIslamici, 1998. ከፈረንሳይኛ ቋንቋ የተተረጐመ መጽሐፍ ነው::

Fakhry, Majid. *A History of Islamic Philosophy*. 2nd ed. New York: Columbia U.P., 1983.

Fakhry, Majid. *A Short Introduction to Islamic Philosophy, Theology and Mysticism*. Oxford: Oneworld, 1997. ርእሰ ጉዳዩን ለማጥናት ጥሩ የጅማር መጽሐፍ ነው::

Goodman, L. E. *Avicenna*. London: Routledge, 1992. በእስልምና ታሪክ ውስጥ እጅግ ስመ ጥር የሆኑትን ፈላስፎች የሚያስተዋውቅ መጽሐፍ ነው::

Leaman, Oliver. *A Brief Introduction to Islamic Philosophy*. Cambridge: Polity, 1999.

Martin, Richard C. and Mark R. Woodward with Dwi S. Atmaja. *Defenders of Reason in Islam: Mu'tazilism from Medieval School to Modern Symbol*. Oxford: Oneworld, 1997.

Watt, W. Montgomery. *Islamic Creeds*: A Selection. Edinburgh: Edinburgh U.P., 1994.

Watt, W. Montgomery. *Islamic Philosophy and Theology*. *2nd ed*. Edinburgh: Edinburgh U.P., 1985.



## ሱፊይዝም እስላም

Andrae, Tor. *In the Garden of Myrtles: Studies in Early Islamic Mysticism*. Trans. Birgitta Sharpe from the Swedish. Albany, N.Y.: State University of New York Press, 1987.

Awn, Peter J. *Satan's Tragedy and Redemption: Iblîs in Sufi Psychology*. Leiden: E. J. Brill, 1983.

Baldick, Julian. *Mystical Islam: An Introduction to Sufism*. London: I. B. Tauris, 1989.

Chittick, William C. *Imaginal Worlds: Ibn 'Arabî and the Problem of Religious Diversity*. Albany, N.Y.: State University of New York Press 1994. በእስልምና ታሪክ ውስጥ እንዲሁም በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ ባለው ዕውቀት አንቱ በተባለ ምሁር የቀረበ ዳሰሳዊ ጥናት ነው::

Haeri, Fadhlalla. *The Elements of Sufism*. Shaftesbury, Dorset, UK: Element, 1990. በሱፊ ሼኽ የቀረበ ግልጽ ጥናት የሱፊይዝም ነው::

MacCarthv, R. J., trans. *Al-Ghazali's Path to Sufism*. Louisville, KY.: Fons Vitae, 2000. አል-ጋዛሊ እንዴት ወደ ሱፊይዝም እንደ ተቀየረ የገለጸበትና ታዋቂ የሆነው ግለ ታሪኩ ተተርጉሞ የቀረበበት መጽሐፍ ነው::

Nasr, Seyyed Hossein, ed. *Islamic Spirituality: Foundations*. New York: Crossroad, 1985, and *Islamic Spirituality: Manifestations*. New York: Crossroad, 1991. and Islamic Spirituality: Manifestations. New York: Crossroad, 1991. የመጀመሪያው ቅጽ በቁርአን፣ በሐዲስ እንዲሁም በቀደምት ሱፊይዝም ወዘተ ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ ሁለተኛው ቅጽ ደግሞ በሱፊ አስተሳሰብ፣ ሥነ ጽሑፍ እንዲሁም ሥዕል ላይ ያጠነጥናል::

Nicholson, Reynold A. *Studies in Islamic Mysticism*. Surrey, UK: Curzon Press, 1994. እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የሱፊ ጽሑፎች ተተርጉመው የቀረቡበት መጽሐፍ ነው::

Padwick, Constance. *Muslim Devotions: A Study of Prayer-Manuals in Common Use*. Oxford: Oneworld Publications, 1996. ዋና ዋና የሚባሉ የእስልምና ጸሎቶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉመው የቀረቡበት መጽሐፍ ነው::

Schimmel, Annemarie. *And Muhammad Is His Messenger: The Veneration of the Prophet in Islamic Piety*. Chapel Hill, N.C.: The University of North Carolina Press, 1985.

Schimmel, Annemarie. *Mystical Dimensions of Islam*. Chapel Hill, N.C.: The University of North Carolina Press, 1975.

Smith Margaret. *Readings from the Mystics of Islam*. London: Luzac, 1950. በርእሰ ጉዳዩ ላይ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ብቸኛ መጽሐፍ ነው::

Trimingham, J. Spencer. *The Sufi Order in Islam*. Oxford, Clarendon, 1971; reprint 1998.

## ሻይዝም

Daftary, P. *The Isma'ilis: Their history and Doctrine. London: C.U.P., 1990.*

Halm, Heinz. Shiism. *Trans. Janet Watson from the German*. Edinburgh: Edinburgh U.P., 1991

Monmen, Moojan. *An Introduction to Shi'I Islam: The History and the Doctrines of Twelver Shi'ism*. New Haven, Conn.: Yale, 1985.

## የእስልምና ታሪክ

Al-Faruqi, R. Isma'il, and Lois Lamya' al-Faruqi. *The Cultural Atlas of Islam*. New York: Macmillan, 1986. የእስልምናን አስተምህሮ ከጥቃት ለመከላከል ታስቦ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው::

Esposito, John, ed. *The Oxford History of Islam*. Oxford, UK: Oxford U.P., 2000.

Holt, P. M., Lambton, A. K. S., and Lewis, B., eds. *The Cambridge History of Islam*. 2 vol. Cambridge: Cambridge U.P., 1970.

Hourani, Albert H. *A History of the Arab Peoples*. London: Faber, 1991. እጅግ ጠቃሚ የሆነ በተለይ ደግሞ አሁን ላለው ነባራዊ ሁኔታ የሚጠቅም አሰሳዊ ጥናት ነው::

Lapidus, Ira M. *A History of Islamic Societies*. 2nd ed. Cambridge: Cambridge U.P., 2002. ስለ እስልምናው ዓለም በአጠቃላይ ጠቃሚ መረጃ የሚሰጥ መጽሐፍ ነው::



Riley-Smith, Jonathan, ed. *The Atlas of the Crusades*. London: Times Books, 1991.

Robinson, Francis, ed. *The Cambridge Illustrated history of the Islamic World*. Cambridge: Cambridge U.P., 1999.

Robinson, F. *Atlas of the Islamic World Since 1500*. New York: Facts on File, 1982.

Smart, Ninian. *Atlas of the World's Religions*. Oxford, UK: Oxford U.P., 1999. በኅብረ ቀለማት ያሸበረቁ ካርታዎችን የያዘ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው::

## እስልምና በአሜሪካ

Haddad, Yvonne Yazbeck, and John L. Esposito. *Muslims on the Americanization Path?* Oxford UK: Oxford University, 2000.

Smith, Jane I. *Islam in America*. New York: Columbia University, 1999. ሚዛናዊ የሆነ እጅግ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው::

## እስልምና በአፍሪካ

Haynes, J. *Religion and Politics in Africa*. London: Zed Books, 1996.

Hisket, Mervin. *The Course of Islam in Africa*. Edinburgh: Edinburgh U.P., 1994.

Hisket, Mervin. *The Development of Islam in West Africa*. London: Longman, 1984.

Kritzeck, J., and W. H. Lewis, eds. *Islam in Africa*. New York: Van Nostrand, 1969.

Levzion, Nehemia, and Randall L. Pouwels, eds. *The History of Islam in Africa*. Athens, Ohio: Ohio U.P., 2000. ትንንሽ የሆኑ በርካታ ጽሑፎችን የያዘ መጽሐፍ ነው::

Rasmussen, L. *Christian-Muslim relations in Africa*. London: I. B. Tauris, 1993.

Sanneh, Lamin. *The Crown and the Turban: Muslims and West African Pluralism*. Boulder: Westview Press, 1997.

Stamer, P. Josef. *Islam in Sub-Saharan Africa*. Königstein, Germany: Aid to the Church in Need, 1995. ግልጽና አጫጭር የሆኑ ክርስቲያናዊ መልሶችን ያካተተ መጽሐፍ ነው።

## እስልምና በዘመናዊው ዓለም

Abu Rabi, Ibrahim M. *Intellectual Origins of Islamic Resurgence in the Modern Arab World*. Ithaca, N.Y.: State University of New York Press, 1995.

Ahmed, Akbar S. *Postmodernism and Islam. Predicament and Promise*. London: Routledge, 1992. በዘመናዊው ዓለም ውስጥ የእስልምና ዐይነተኛ ባሕርያት ናቸው የሚባሉትን ማንነቶች የሚያፈላልግ መጽሐፍ ነው።

Algar, Hamid. *Islam and Revolution: Writings and Declarations of Imam Khomeini*. Berkeley, Calif.: Mizan Press, 1981.

Arkoun, Mohammed. *Rethinking Islam: Common Questions, Uncommon Answers*. Trans. And ed. By Robert D. Lee from the French. Boulder, Colo.: Westview Press, 1994. ግልጽ እንዲሁም በእስልምና ሃይማኖት ላይ ለዘብተኛ አቋም ያለው መጽሐፍ ነው።

Choueiri, Youssef M. *Islamic Fundamentalism*. London: Pinter, 1997.

Cole, Juan. R. I., and Nikki R. Keddie, eds. *Shi'ism and Social Protest*. New Haven: Yale U.P., 1986.

Donohue, John J., and John L. Esposito, eds. *Islam in Transition: Muslim Perspectives*. New York: Oxford U.P., 1982. ዘመነኛ የሆኑ 50 የሙስሊም ምሁራንን ጽሑፍ ያካተተ መጽሐፍ ነው።

Eshtashtami, Anoushiravan. *After Khomeini: The Iranian Second Republic*. London: Routledge, 1995.

Esposito, John L., and Azzam Tammimi. *Islam and Secularism in the Middle East*. New York: New York U.P., 2000.

Esposito, John L., and John Voll. *Islam and Democracy*. Oxford: Oxford U.P., 1996.

Hourani, Albert. *Arabic Thought in the Liberal Age, 1798-1939*. London, 1962. Kepel, Giller. Muslim Extremism in Egypt: The Prophet and Pharaoh. Berkeley: University of California Press, 1992.



Kurzman, Charles. *Liberal Islam: A Sourcebook*. New York: Oxford U.P., 1998.

Kramer, Martin. *Arab Awakening & Islamic Revival*. New Brunswick: Transaction Publishers, 1996.

Lewis, Bernard. *The Shaping of the Modern Middle East*. New York: Oxford U.P., 1994.

Moussalli, Ahmad S., ed. *Islamic Fundamentalism: Myths and Realities*. Reading, UK: Garnet Publishing, 1998.

Moussalli, Ahmad S., *Moderate and Radical Islamic Fundamentalism: The Quest for Modernity, Legitimacy, and the Islamic State*. Jacksonville: University of Florida Press. 1999.

Mitchell, Richard P. *The Society of the Muslim Brothers*. New York: Oxford U.P., 1993. በመጀመሪያ በ1969 ዓ.ም የታተመ መጽሐፍ ሲሆን፣ በግብፅ አገር ባለው የሙስሊም ወንድማማቾች ዕድገት ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው።

Voll, John O. *Islam: Continuity and Change in the Modern World*. 2nd ed. Syracuse, N.Y.: Syracuse U. P., 1994.

Zeberi, Kate. *Mahmud Shaltut and Islamic Modernism*. Oxford: Clarendon Press, 1993. መሐመድ ሳሉት በ1963 ዓ.ም የሞቱ በአል-አዛር ዩኒቨርስቲ ያስተምሩ የነበሩ ስመ ጥር ምሁር ናቸው።

Ziad, Abu-Amr. *Islamic Fundamentalism in the West Bank: Muslim Brotherhood and Islamic Jihad*. Bloomington: Indiana U.P., 1994.

## የክርስቲያኖችና የሙስሊሞች ግንኙነት—ታሪክ

Daniel, Norman. *Islam and the West: The Making of an Image*. Oxford: Oneworld Publications, 1993. መጀመሪያ የታተመው በ1960 ዓ.ም ሲሆን፣ አዲሱ ዕትም በርካታ ርእሶችን ጨምሮ ቀርቦአል።

Gaudeul, Jean-Marie. *Encounters and Clashes: Islam and Christianity in History*. 2 vol. Rome: Pontificio Istituto di Studi Arabi e Islamici, 2000. የመጀመሪያው ቅጽ በታሪክ ሁለተኛው ቅጽ ደግሞ ነገረ መለኮት ርእስ ጉዳይ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው።

Goddard, Hugh. *A History of Christian-Muslim Relations*. Edinburgh: Edinburgh U.P., 2000. ከእስልምና በፊትም ሆነ በኋላ እንዲሁም እስከ ዛሬ ድረስ ያለውን ታሪክ የሚዘግብ ጥሩ መጽሐፍ ነው።

Southern, R. W. *Western Views of Islam in the Middle Ages*. Cambridge, Mass.: Harvard U.P., 1962; reprint, 1978.

Watt, W. Montgomery. *Muslim-Christian Encounters: Perceptions and Misperceptions*. London: Routledge, 1991.

## የክርስቲያኖችና የሙስሊሞች ግንኙነት—ዘመናዊ ዕይታ

Anees, Munawar Ahmad, et al. *Christian-Muslim Relation: Yesterday, Today, Tomorrow*. London: Grey Seal, 1991. በሙስሊም አተያይ የቀረበ ጥሩ መጽሐፍ ነው::

Azumah, John Alembillah. *The Legacy of Arab-Islam in Africa: A Quest for Inter-Religious Dialogue*. Oxford: Oneworld, 2001. ከሰሐራ በታች ያሉ አገሮችን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ አሰቸጋሪ በሚባሉ ጥያቄዎች ላይ የሚያጠነጥን መጽሐፍ ነው::

Borrmans, Maurice. *Guidelines for Dialogue Between Christians and Muslims*. Trans. R. Marston Speight from the French. Mahwah, N.J.: Paulist, 1990. የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ መሠረት ባደረገ መልኩ፣ ከሙስሊሞች ጋር ለሚደረገው ውይይት ጠቃሚ መረጃ የሚሰጥ በጣም ጥሩ መጽሐፍ ነው::

Brown, Stuart E. *Meeting in Faith: Twenty Years of Christian-Muslim Conversations Sponsored by the World Council of Churches*. Geneva: World Council of Churches, 1989. ጠቃሚ የሆኑ እንዲሁም ሁለቱ ወገኖች በየትኞቹ ርእስ ጉዳዮች ላይ እንደ ተወያዩ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው::

Caspar, Robert. *Trying to Answer Questions*. Rome: Pontificio Instituto di Studi Arabi e Islamici, 1989. የሙስሊሞችን ጥያቄ ከሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ አንጻር የሚመልስ መጽሐፍ ነው::

Chapman, Colin. *Islam and the West*. Carlisle, UK: Paternoster, 1998. በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ያለውን የግንኙነት ታሪክ በትክክል የሚያቀርብ፣ በሰብአዊ መብትና በትምህርት ረገድ ያሉትን ወቅታዊ ርእስ ጉዳዮች የሚመለከት መጽሐፍ ነው::

Cragg, Kenneth. *The Call of the Minaret*. 3rd ed. Oxford: Oneworld, 2000. በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ የተጻፈ እንዲሁም እስልምናን በትክክል ተረድቶ ክርስቲያናዊ መልስ የሚያቀርብ አስደናቂ መጽሐፍ ነው::



Cragg, Kenneth. *Jesus and the Muslim: An Exploration*. Oxford: Oneworld, 1999. ለሙስሊሞች የክርስቶስን ማንነት የሚተነትን መጽሐፍ ነው::

Cragg, Kenneth. *Muhammad and the Christian: A Question of Response*. Oxford: OneWorld 1999. ክርስቲያኖች መሐመድን እንዴት ባለ መልክ መመልከት እንዳለባቸው የሚገልጽ ነው::

Goddard, Hugh. *Christian and Muslims: From Double Standards to Mutual Understanding*. Surrey, UK: Curzon Press, 1995. እስልምናንና ክርስትናን ከታሪክና ከማኅበራዊ መስተጋብር አንጻር የሚያወዳድር በአሰሳ መልክ የቀረበ መጽሐፍ ነው::

Goddard, Hugh. *Muslim Perceptions of Christianity*. London: Grey Seal, 1996. በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን በግብፅ የነበሩ ሙስሊሞች ስለ ክርስትና ያላቸውን አተያይ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው::

Kateregga, Badru D., and David W. Shenk. *Islam and Christianity: a Muslim and Christian in Dialogue*. Scottdale, Pa.: herald Press 1997. ሙስሊም እንዲሁም ክርስቲያን በሆኑ ጸሐፍያን የቀረበ፣ እያንዳንዳቸው ባቀረቡት ዘገባ ላይ አንዱ ለሌላው የሚሰጠውን ምላሽ ያካተተ መጽሐፍ ነው::

Kirkwood, Neville A. *Pastoral Care to Muslims*. Binghamton, N.Y.: The Haworth Pastoral Press, 2001. ሙስሊሞችን እንዴት መንከባከብ እንችላለን በሚለው ርእስ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥንና በሆስፒታሎች አካባቢ ወንጌልን በሚሰብክ ሰባኪ የቀረበ መጽሐፍ ነው::

Nickel, Gordon. *Peaceable Witness Among Muslims*. Scottdale, P.: Herald Press, 1999. በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍንም ሆነ ውትድርናን የማይደግፍ፣ በሜኖናይት ምሁር የቀረበ መጽሐፍ ነው::

Tingle, Donald S. *Islam and Christianity*. Madison, Wisc.: InterVarsity Press, 1985. ክርስትናንና እስልምናን የሚያነጻጽር 32 ገጽ ያለው መለስተኛ መጽሐፍ ነው::

Zebiri, Kate. *Muslims and Christians Face to Face*. Oxford: Oneworld, 1997.

## በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ ክርስቲያን ማኅበረሰቦች

Cragg, Kenneth. *The Arab Christian: A History in the Middle East*. Louisville, KY.: Westminster/John Knox Press, 1991. ነገረ መለኮትን አስመልክቶ የቀረበው ማብራሪያ ጥሩ ቢሆንም፣ በመጀመሪያ የእስልምና ዘመናት የነበረውን የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ በጥሩ ሁኔታ ያላመላከረ ነው::

Horner, Norman A. *A Guide to Christian Churches in the Middle East.* Elkhart, Ind.: Mission Focus, 1989. በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ያለውን መሠረታዊ ሁኔታ የሚዘግብና ጠቃሚ መረጃዎችን ያካተተ መጽሐፍ ነው::

Pacini, Andrea, ed. *Christian Communities in the Arab Middle East: The Challenge of the Future.* Oxford: Clarendon Press, 1998. በተለያዩ ምሁራን የቀረበ ዘገባ ሲሆን፣ ነባራዊውን ሁኔታ በትክክል ያመሳከረ ነው::

Partick, Theodore Hall. *Traditional Egyptian Christianity: A History of the Coptic Orthodox Church.* Greensborn, N.C.: Fisher Park Press, 1996.

Van-Doorn-Harder, Nelly, and Kari Vogt, eds. *Between Desert and City: The Coptic Orthodox Church Today.* Oslo, Intituttet for Sammenlignende Kulturforskning, 1997. የበርካታ ምሁራንን ጽሑፍ ያካተተ መጽሐፍ ሲሆን፣ ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካ ውስጥ ሊኖራት ስለሚገባት ሚና የሚያትት ነው::

Wessels, Antonie. *Arab and Christian? Christians in the Middle East.* Kampen, The Netherlands: Kok Pharos Publishing House, 1995. ወቅታዊውን ሁኔታ ታሪክና ትንተና ያካተተ መጽሐፍ ነው::



# ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር

የሚከተሉትን መጻሕፍት ገዝተው እንዲያነቡ ያበረታታል

## *በቅርቡ ለንባብ የሚበቃ*

1. **መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት (ቅጽ 1 እና ቅጽ 2)** —ከአማረ መስፍንና ከተስፋዬ ሮበሌ
2. **የትንሣኤው ማኅበረሰብ**—ከተስፋዬ ሮበሌ
3. **የሙግት ጥበብ**—ከተስፋዬ ሮበሌ
4. **የሐዳስያን ማኒፌስቶ**—ከአማረ መስፍንና ከተስፋዬ ሮበሌ
5. **ድኅረ ዘመናዊነት**—ከተስፋዬ ሮበሌ
6. **የፖለቲካና የሃይማኖት ፍልስፍና**—ከተስፋዬ ሮበሌ
7. **የብሉይ ኪዳን መክፈቻ**— ከአማረ መስፍንና ከተስፋዬ ሮበሌ
8. **የእምነት እንቅስቃሴ፣ አዲስ መገለጥ ወይስ አሮጌ ኑፋቄ** —ከተስፋዬ ሮበሌ
9. **የሥነ ምግባር ታሪክ**—ከተስፋዬ ሮበሌ
10. **የሐዲስ ኪዳን መክፈቻ**—ከተስፋዬ ሮበሌና ከአማረ መስፍን
11. **የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ**—ከተስፋዬ ሮበሌ
12. **የመጽሐፍ ቅዱስ ጠንካራ ምንባባት** —ከአማረ መስፍን ከተስፋዬ ሮበሌና ከዮናስ አስፋው
13. **ዐቃቤ እምነት ዘክርስትና**—ከተስፋዬ ሮበሌ
14. **የሥነ ምግባር መርሖ** (ሁለተኛ ዕትም)—ከተስፋዬ ሮበሌ
15. **በቅዱሳት መጻሕፍት ዘገባ በርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?**— ከተስፋዬ ሮበሌ
16. **የሥነ ምግባር ርእሰ ጉዳዮች**—ከተስፋዬ ሮበሌ
17. **የነገረ መለኮትና የፍልስፍና መዝገበ ቃላት**—ከተስፋዬ ሮበሌና ከአማረ መስፍን